# ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን

ጥቅምት ፲፱፻፶፫ ዓ.ም



ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

www.ethiopianorthodox.org

# ለግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ
# ፍልሰተ አፅም በዓል

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
## የተዘጋጀ ሥርዓተ ጸሎት

፩ኛ. ከጥቅምት ፳፫ እስከ ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ድረስ በመላ ኢትዮጵያ አህጉረ ስብከት በሚገኙት ገዳማት፣ አድባራትና አብያተ ክርስቲያናት ስብሐተ እግዚአብሔር ሲደረስና ጸሎተ ፍትሐት ሲደረግ ሰንብቷል።

፪ኛ. በተለይም ቅዳሜ ጥቅምት ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ለ፳፮ አጥቢያ የንጉሠ ነገሥቱ አፅም አርፎበት በቆየው በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ቤት ታዕካ ነገሥት በዓታ ለማርያም ገዳም ከምሽቱ ፫ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፲ ሰዓት ድረስ የማኅሌቱ ሥነ ሥርዓትና ጸሎተ ፍትሐቱ ሲካሄድ አድሯል። የሰዓታቱም ጸሎት በዚሁ ሰዓት ተፈጽሟል።

፫ኛ. ከሌሊቱ በ፲ ሰዓት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ጋር ሆነው ከገዳሙ እንደ ደረሱ የገዳሙ የበላይ ኃላፊ ሊቀ ጳጳስ፣ ሊቀ ሊቃውንቱና ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ካህናት፣ ጥላ መስቀል የያዙ ዲያቆናት፣ ጥንግ ድርብ የለበሱ መዘምራን፣ የሰንበት ት/ቤት ወጣት ዘማርያን እየዘመሩ አቀባበል አድርገውላቸዋል።

፬ኛ. የንጉሠ ነገሥቱ አፅም ከሌሊቱ ፲፩ ሰዓት ከነበረበት ምድር ቤት በክብር ተነስቶ በቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት እንዲያርፍ ከተደረገ በኋላ በ፲፩ ሰዓት ተኩል በቅዱስ ፓትርያርኩና በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት የጸሎተ ፍትሐቱ ሥነ ሥርዓት ተጀምሮ ጸሎተ አኰቴት ደርሷል። ጸሎተ ፍትሐቱ እንዳተፈጸመም ከንጋቱ በ፲፪ ሰዓት ጸሎተ ቅዳሴው በቅዱስ ፓትርያርኩ መሪነት በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ተካሄዶ በ፪ ሰዓት ተፈጽሟል።

፭ኛ. ከጠዋቱ በሁለት ሰዓት ከሩብ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አፅም ወጥቶ በዐውደ ምሕረቱ እንደ አረፈ ያሬዳውያን መዘምራን ለበዓሉ የተዘጋቸውን ግሥ «ጊዜ ሠለስቱ ሰዓት ጸለየ ኃይለ ሥላሴ ወአርኃወ ኃዋኅወ ቤቱ ታዕካ ነገሥት በዓታ ለማርያም ዘይኤጽር መንገለ ገጸ መንበረ ጽባዖት ወሰምዐ ጸሎቶ ለኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት» የሚለውን ቃኝተው ዘምረዋል። የሰንበት ትምህርት ቤት ዘማርያንም «ዳግመ እምዝ፣ ዳግመ እምዝ ኢይረክቦ ሞት ለኃይለ ሥላሴ» የሚለውን መዝሙር ዘምረዋል።

፮ኛ. የተፈቀደላቸው ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ፍልሰተ አፅሙን አስመልክተው ልዩ ልዩ ቅኔዎችን አቅርበዋል።

፯ኛ. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ስለ ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ መንፈሳዊ ሕይወትና ታላቅ መሪነት አባታዊ ትምህርት ሰጥተው ጸሎተ ቡራኬ አድርገዋል።

፰ኛ. ለሦስት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን የግርማዊነታቸው አፅም በሰረገላ ሆኖ ከታዕካ ነገሥት በዓታ ገዳም ተነስቶ ወደ መስቀል አደባባይ ጉዞ አድርጓል በዚህ ጊዜ ጽናሕ፣ መስቀልና ጥላ የያዙ መነኮሳት ቀሳውስትና ዲያቆናት እንደዚሁም ጥንግ ድርብ የለበሱ መዘምራን የሰንበት ት/ቤት ወጣት ዘማርያን ሰረገላውን በግራና በቀኝ አጅበው በሰልፍ ወደ መስቀል አደባባይ አምርተዋል።

፱ኛ. በመስቀል አደባባይ አጭር ጸሎት ከተደረገ በኋላ ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ጽና መስቀል የያዙ መነኮሳት ቀሳውስትና ዲያቆናት አፅሙን የያዘውን ሠረገላ በክብር በማጀብ ጉዞው ወደ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ቀጥሏል።

### በመናገሻ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን የተደረገ ሥርዓተ ጸሎት፣

ሀ. «እግዚአ ሕያዋን» የሚለው ጸሎት ተጸልይዋል

ለ. ያሬዳውያን መዘምራን በመርሐ ግብሩ መሠረት የተዘጋጀውን መዝሙር ዘምረዋል።

ሐ. የሰንበት ት/ቤት ወጣት ዘማርያንም «አብርሀ ገጸከ ላዕለ ገብርከ ኃይለ ሥላሴ፣ እግዚኦ ለኃይለ ሥላሴ ያስምዕ ቃለ ሕዝብከ» የሚለውን መዝሙር ዘምረዋል

፲ኛ. ከዚያም የንጉሠ ነገሥቱን አፅም የያዘው ሰረገላ ከገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተነስቶ ወደ ራስ መኰንን ድልድይ በሚወስደው መንገድ አልፎ ከምክር ቤቱ በስተጀርባ በሚገኘው የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል መግቢያ እንደደረሰ

ሀ. መዘምራኑ «ወእሙን ትእዛዙ ለኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ወሠናይ ሥርዓተ መንግሥቱ ለኃይለ ሥላሴ ጠቢብ ወማዕምር ዘመጠወ ነፍሶ ወአቅትለ ርዕሶ በአንተ ሀገሪትነ» የሚለውን ግሥ ቃኝተው ዘምረዋል።

ለ. የሰንበት ት/ቤት ወጣት ዘማርያንም «ኃይለ ሥላሴ ይቤ ዛቲ ይዕቲ ምዕራፍዩ ለዓለም ዝየ አሐድር እስመ ኀረይክዋ ለመንበረ ጸባዖት» የሚለውን መዝሙር ዘምረዋል።

ሐ. የተፈቀደላቸው ሊቃውንት መወድስ ቅኔዎችን አበርክተዋል።

መ. የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ፍልሰተ አፅም በዓልን አስመልክቶ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተዘጋጀው ታሪካዊ መጽሔት ታድሏል።

፲፩ኛ. በቅዱስነታቸው የተፈቀደላቸው ሊቀ ጳጳስ የፍልሰተ አፅሙን በዓል አስመልክተው ትምህርት ሰጥተዋል።

፲፪ኛ. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት ቃለ ምዕዳንና ጸሎተ ቡራኬ ከሰጡ በኋላ የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ አፅም በተዘጋጀው መካነ መቃብር በክብር አርፏል።

በዚህም የበዓሉ ፍጻሜ ሆኗል።

በዚሁ ዕለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንደ ታዕካ ነገሥት በዓታ፣ እንደ መንደበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴና እንደ መናገሻ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ በመሳሰሉት አብያተ ክርስቲያናት በንጉሠ ነገሥቱ ስም ለነዳያን ምጽዋት አድርጋለች።

www.ethiopianorthodox.org



ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

www.ethiopianorthodox.org

# ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን

ይህ መጽሔት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ልዩ ትእዛዝ፣ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ፣ ለግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ፍልሰተ አፅም በዓል፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ለመዘክርነት ተዘጋጀ።

ጥቅምት ፲፱፻፺፫ ዓ.ም አዲስ አበባ

## ማውጫ


የቅዱስነታቸው መልእክት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፬
የግርማዊነታቸው መንፈሳዊ ሕይወት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፭
«እስመ በጻሕኮ በበረከት ሠናይ» (በመልካም በረከት ደረስህለት) . . . . . . . . . ፱
ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዕድገት ያደረጉት ጥረት
ሀ. በዘመናዊ አስተዳደር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፩
ለ. መንፈሳዊ መብትን በማስጠበቅ . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፬
ሐ. አብያተ ክርስቲያናትን በማሳነፅ . . . . . . . . . . . . . . . . ፳፪
መ. ቅዱሳት መጻሕፍትን በማሳተም . . . . . . . . . . . . . . . . . ፳፫
ሠ. መንፈሳዊ ትምህርትንና ት/ቤቶችን በማስፋፋት . . . . . . . . . . . ፴፩
ረ. ስብከተ ወንጌልን በማጠናከር . . . . . . . . . . . . . . . . . ፴፭
ሰ. የውጭ ግንኙነትን በማሳደግ . . . . . . . . . . . . . . . . . ፴፮
«እግዚአብሔር የዐቅብ ኵሎ አዕፅምቲሆሙ» (እግዚአብሔር አፅማቸውን ይጠብቃል) . . . ፴፱
«ስምከ ሕያው ዘኢይመውት» (ስምህ የማይሞት ሕያው ነው) . . . . . . . . . . ፵፩
«ዝክረ ጻድቅ ለዓለም ይኄሉ» (የጻድቅ መታሰቢያ ለዘለዓለም ይኖራል) . . . . . . . ፵፫
ልዩ ልዩ ቅኔያት
ሀ. ፍልሰተ አፅማቸውንና ታላቅ መሪነታቸውን በተመለከተ
በአሁኑ ጊዜ ካሉት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የተበረከቱ ቅኔያት . . . . . . . . ፵፭
ለ. ለቤተ ክርስቲያን ስለ አስገኙት መንፈሳዊ ነፃነት
በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ከቀድሞ ሊቃውንት የተበረከቱ ቅኔያት . . . . . . . . ፵፯
ለግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ፍልሰተ አፅም የተዘጋጀ ሥርዓተ ጸሎት (የሽፋኑ የውስጥ ገጽ)


www.ethiopianorthodox.org

# የቅዱስነታቸው መልእክት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!!

" አመ ይሔውጸክሙ እግዚአብሐር አውፁኡ አዕፅምትየ "

እግዚአብሐር በሚጎበኛችሁ ጊዜ አፅሜን አውጡ " (ዘፍ. 50:25)

እስራኤላውያን እግዚአብሐር በቸርነቱ በጎበኛቸው ጊዜ የዮሴፍን አፅም ከግብፅ አውጥተው ወደ ከነዓን ወሰዱት:: አባታቸው ያዕቆብ በሰጣቸው ርስት በክብር አሳረፉት::

እንደዚሁም ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር ነውና በእግዚአብሔር ፈቃድና በመንግሥት ትብብር ጊዜው ሲደርስ የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት አፅም በግፍ ከተጣለበት አስባሲ ቦታ ወጥቶ እነሆ በተቀደሰ ቦታ እንዲያርፍ እየተደረገ ነው::

በዚህ ታሪካዊ ወቅት ወደ ኋላ መለስ ብለን ብንመለከት እኒህ ታላቅ ንጉሠ ነገሥት በሕይወት ዘመናቸው ለኢትዮጵያ፣ ለቤተ ክርስቲያን፣ ለአፍሪካና ለመላው ዓለም ያበረከቱትን አስተዋጽኦ በዓይነ ኅሊናችን ለንቃኘ እንችላለን::

ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ለኢትዮጵያ ዕድገትና ሥልጣኔ፣ ለሕዝባም ማኅበራዊ ሕይወት መሻሻል ከማንም የላቀ አስተዋጽኦ አድርገዋል:: በመንፈሳዊውም ረገድ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መብቷ የሚጠበቅበትን ሕግና ሥርዓት በማውጣት ለዕድገቷ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል:: ይልቁንም ከአንድ ሺህ ስድስት መቶ ዓመት በኋላ ከራስዋ ልጆች መርጣ ኤጲስ ቆጶሳት፣ ሊቃነ ጳጳሳትና ፓትርያርክ ለመሾም የምትችልበትን መብትና ክብር በማጎናጸፍ ራስዋን እንድትችል አድርገዋል::

ግርማዊነታቸው ሃይማኖተ ጽኑ፣ አርቆ አስተዋይ ታላቅ የሰላም አባት ነበሩ:: የመንፈሳዊ ሕይወታቸው ጽናት ምእመናንና ምእመናት በሃይማኖታቸው እንዲጠናከሩ ከማድረጉም በላይ በአኀት ኦሪየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ " የሃይማኖት ጋሻ፣ ብቸኛ ኦርቶዶክሳዊ ንጉሠ ነገሥት " እየተባሉ እንዲጠሩ አስችሏል:: የሀገርንና የታሪክን ኃላፊነት በብቃት በመወጣት ኢትዮጵያ ለደረሰችበት ዘመናዊ ሥልጣኔ የእድገት ምዕራፍ ከፋችና መሥራች ሆነዋል:: ማንም እንደሚረዳው በዓይን የሚታዩ፣ በእጅ የሚዳሰሱ ታላላቅ ሥራዎችን አከናውነዋል:: ኢትዮጵያ ሀገራችን፣ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችንና ተዋሕዶ እምነታችን በመላው ዓለም በበለጠ እውቅና እንዲያገኙና ተገቢውን የክብር ሥፍራ እንዲይዙ ያልተቆጠበ ጥረት አድርገዋል:: የሁሉንም ድካም በከንቱ የማያስቀር እግዚአብሔር በበጎ ሥራቸው ዋጋቸውን እንደሚከፍላቸው እናምናለን:: ሁሉም ክርስቲያኖች በጸሎት ያስቧቸዋል:: በተለይም ቤተ ክርስቲያናችን ዘወትር በጸሎት ስታስባቸው ትኖራለች::

ስለዚህ አፅማቸው በተቀደሰ ቦታ በክብር እንዲያርፍ ያደረገ እግዚአብሔር አምላክ ነፍሳቸውን በገነት እንዲያሳርፍ ዘወትር እንጸልያለን::

አባ ጳውሎስ

ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም

ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት



www.ethiopianorthodox.org

# የግርማዊነታቸው መንፈሳዊ ሕይወት

የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ታሪከ ልደት በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል መልአካዊ አንደበት ነቢየ ልዑል፣ ዐርከ መርዓዊ ተብሎ ከተሠየመው ከታሪከ ልደተ ዮሐንስ ጋር በብዙ መልክ ይመሳሰላል።

የእሥራኤል ልጆችንም ወደ ሕገ እግዚአብሔ
እንደሚመልስ፤ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆ
የከሀድያንንም ኅሊና ወደ ጻድቃን አእምሮ ይመልስ ዘንደ
ጉዞውን በመንፈስ ቅዱስና በኃይለ ኤልያ
እንደሚያደርግ፤ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ሕ



ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ቡራኬ ሲቀበሉ

የነቢየ ልዑል ዮሐንስ እናትና አባት ኤልሳቤጥና ዘካርያስ በአምልኮተ እግዚአብሔር የጸኑ፣ በጾምና በጸሎት፣ በምጽዋትና በስግደት የተወሰኑ በጠቅላላውም መንገዳቸውን ሁሉ በእግዚአብሔር ሕግና ትእዛዝ ያደረጉ ከኃጢአት የራቁ ጻድቃን ወይም ደጋግ ሰዎች እንደ ነበሩ ሁሉ የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ወላጆች ልዑል ራስ መኰንን ወልደ ሚካኤልና ወ/ሮ የሺ እመቤትም በሕገ እግዚአብሔር የጸኑ፣ በጾምና በጸሎት፣ በምጽዋትና በስግደት ተወስነው የእግዚአብሔርን ሕግና ትእዛዝ ጠብቀው የሚኖሩ ደጋግ ክርስቲያኖች ነበሩ።

የነቢየ ልዑል ዮሐንስ አባት ካህን ኦሪት ዘካርያስ በቤተ መቅደስ በጸሎት ላይ እንዳለ ጸሎቱ ተሰምቶለት ሚስቱ ኤልሳቤጥ ዮሐንስን እንደምትወልድለት፤ በተወለደውም ሕፃን ልደት እናትና አባቱም ሆኑ ብዙዎች እንደሚደሰቱ፣ በእግዚአብሔርም ፊት ትልቅ ሰው እንደሚሆን ከእናቱ ማኅጸንም ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ እንደሚሞላበት፣ ብዙ

እንደሚሠራና ሕዝቦችንም እግዚአብሔርን ለመቀበል እንደሚያዘጋጅ ብሥራታዊው መልአከ ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ታዞ በትንቢታዊ ቃል ነግሮት ነበር። (ሉቃ.፩፥፲፮–፲፯)

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በመዋዕ
ትምህርቱ «እሱ ከነቢያት ሁሉ ይበልጣል፣ እነሆ እ
መንገድህን በፊትህ የሚጠርግ መልእክተኛዬን እልካለሁ፣
ተብሎ የተጻፈለት እሱ ነውና በእውነት እላችኋለሁ
ከሴቶች ከተወለዱ ልጆች ከዮሐንስ መጥምቅ የሚበልጥ
አልተነሣም፤ ከመጥምቁ ዮሐንስ መነሣት ጀምሮ እስ
አሁን ድረስ መንግሥተ ሰማያት ትገፋለች፤ የተገፉ
ይቀማሟታል (ይቀራመቷታል)፤ ኦሪትም ነቢያትም ሁሉ
እስከዮሐንስ ድረስ ተንብየዋልና፤ ልትቀበሉት
ከፈቀዳችሁስ (ከወደዳችሁስ) ይመጣ ዘንድ ያለው ኤልያስ
እሱ ነውና» (ማቴ.፲፩፥፱–፲፬) በማለት ተናግሮለታል።

ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴም ሀገራቸው
ኢትዮጵያ በፋሽስት ኢጣሊያ በተወረረችበት ወቅት ጄኔቫ
ላይ በዓለም መንግሥታት ፊት ባሰሙት ታሪካዊ ንግግ



www.ethiopianorthodox.org


«ዛሬ በኢትዮጵያ ላይ የተጫረው ክብሪት (የነደደው እሳት) በዓለም ላይ ሳይጫር (ሳይነድ) አይቀርም፤ ታሪክና እግዚአብሔር ፍርዳችሁን ይጠብቁታል፤» በማለት የተናገሩት ንጉሣዊ ቃለ ትንቢት በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተፈጽሟል፤ ግርማዊነታቸው በሁሉም መስክ ለኢትዮጵያ እድገትና ልማት መንገድ ጠራጊ በመሆን ከእግዚአብሔር የተላኩ ነበሩ ለማለት ያስደፍራል፤ በዘመነ መንግሥታቸው ሀገራችን ኢትዮጵያ በሁለንተናዊ የሥልጣኔ ጎዳና ያሳየችው እመርታም ለአባባሉ ጉልህ አስረጅ ነው።

ኢትዮጵያ በኢትዮጵያነቷ ከታወቀችበት ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያን ለማልማት በተደረገው ታሪካዊ ጉዞ ከግርማዊ ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የሚበልጥ እንዳልተነሣ ታሪክ ይመሰክራል፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ እስከ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ መነሣት ድረስ በጦርነት፣ በድህነት፣ በድንቁርና በአጠቃላይም በየፈርጁ በነበረው ኋላ ቀርነት ስትገፋ ኑራለች፤ በመንፈሳዊውም ሆነ በሥጋዊው ማንኛውም የሀገሪቱ ዕድገትና ልማት ሁሉ እስከ ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ድረስ የተገደበ ነበርና። ስለዮሐንስ ታላቅ ነቢይነትና መንገድ ጠራጊነት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደመሰከረለት ሁሉ ስለ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ ብርሃን መሆንና የታሪክ ሰውነትም የውጭም የውስጥም ታሪክ ጸሓፊዎች በእውነት መስክረውላቸዋል፡

በአጠቃላይም ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ለሀገራችን ለኢትዮጵያ በተለይም ለጥንታዊቷ፣ ለታሪካዊቷና ለብሔራዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሁለተኛ ከሣቴ ብርሃን ሰላማ ነበሩ ብለን ብንናገር በፈቃደ እግዚአብሔር ተመርጠውና ተቀብተው ከነገሡበት ወይም ቅዱም እግዚአብሔር ተብለው በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ዙፋን ከተቀመጡበት ጊዜ ጀምሮ በመንፈሳዊውም ሆነ በሥጋዊው በየዘርፉ ያከናወኑት ተግባር ዋቢ ሁኖ ሊቀርብልን ይችላል፡

ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በሕፃንነታቸው ወራት ይታይባቸው የነበረው ብሩህ ተስፋ በነገሥታቱ፣ በመሣፍንቱና በመኳንንቱ፣ በቤተ ክርስቲያን አባቶችና በዘመኑ በነበሩ ታላላቅ ሰዎችም ጭምር ስለ ኢትዮጵያና ስለ ሕዝቦቿ የወደፊት አለኝታነታቸው ብዙ ተብሏል፣ ብዙም ተነግሯል።

የግርማዊ ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዕድል በእግዚአብሔር እጅ ስለመሆኑና ስለወደፊቱ ታላቅነታቸውም በአካልም በማዕረግም ያሳደጓቸው አባታቸው ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ምኒልክ በሕፃንነታቸው ወራት እንዲህ ሲሉ ተንብየውላቸው ነበር።



ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በተቀጸል ጽጌ በዓል ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የአበባ ጉንጉን ሲቀበሉ



www.ethiopianorthodox.org

«እንደንስር አሞራ ከፍ ያለ መንፈስ ይዘህ የምትገኝ አንተ ነህ» የሚለውን ቃለ ትንቢት በሕፃንነታቸው ወራት በአንድ ወቅት የተናገሩላቸው ሲሆን በሌላ ወቅት ደግሞ በ፲፫ ዓመት ዕድሜያቸው ደጃዝማች ብለው በሾሙአቸው ጊዜ መኳንንቶቻቸውንና መሳፍንቶቻቸውን ሰብስበው እንዲህ ብለውላቸዋል።

«ሁላችሁም ያሳደግኋችሁና የምወዳችሁ አሽከሮቼ ናችሁ፣ ልጄን ተፈሪን ከእግዚአብሔር ጋር አደራ ብዬአችኋለሁ፤ አደራም የምላችሁ ለዓይናችሁ እንዳትጠሉት ነው እንጂ ዕድሉ በፈጣሪ እጅ ነው» በማለት ግርማዊነታቸው ከሕፃንነታቸው ጀምሮ አምላካዊ ጸጋን የተጎናጸፉ መሆናቸውንና የወደፊት ብሩህ ተስፋቸውን ተናግረዋል።

አንድ የውጭ ጸሓፊም ቴሌስታር ፖርሌም በተባለ ጋዜጣ «ንጉሠ ነገሥቱ በፎቶ ግራፍ ላይ እንደሚታዩት ሳይሆን ጠጋ ብሎ ለተመለከታቸው በጣም ረቂቅ ሁነው ይታያሉ» ብሏል። ይህም አባባል የሚገልጸው የግርማዊነታቸው ሰውነት ከሕፃንነታቸው ጀምሮ በጾምና በጸሎት የተገሠጸ መሆኑንና አሳቢነታቸውን፣ ተመራማሪነታቸውን፣ አርቆ አስተዋይነታቸውንና በአእምሮ በሳልነታቸውን ነው። በሀገራችን በታሪክ ተመራማሪነት ብዙ ጊዜ የቆየው ሀንስ ዌል ኸልም ሎከትም ስለ ግርማዊነታቸው የቋንቋ ችሎታ በአድናቆት ሲገልፅ «ንጉሠ ነገሥቱ አያሌ ዓለም አቀፍ ቋንቋዎችን እንደሚችሉ ጠቅሶ አፋቸውን የፈቱት በአማርኛ ቋንቋ ነው፣ በተለይ በጥንታዊው የግእዝ ቋንቋ በቂ ዕውቀት አላቸው» ብሎ ጽፏል።

ለአስረጅ ያህል ከረጅሙ በአጭሩ ይህን ጠቀስነው እንጂ ስለ ንጉሠ ነገሥቱ መንፈሳዊ ሕይወት ብዙዎችም የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ጸሓፊዎችና ተናጋሪዎች ብዙ ብለውላቸዋል።

ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ እናታቸው ወ/ሮ የሺ እመቤት በተወለዱ በሁለት ዓመት ዕድሜያቸው፣ አባታቸው ልዑል ራስ መኰንንም በተወለዱ በ፲፫ ዓመት ዕድሜያቸው ሙተውባቸው ምንም እንኳ በሰው ሰው ያደጉ የሙት ለጅ ቢሆኑም ከእርሳቸው በፊት እናታቸው ወ/ሮ የሺእመቤት የወለዷቸው ፰ ልጆች በተከታታይ ስለሞቱባቸው ግርማዊነታቸው የሞት ማክተሚያ ናቸው። በዮሐንስ ልደት ወላጆቹም ሆኑ ብዙዎች እንደተደሰቱ ሁሉ የግርማዊነታቸውም ልደት ለወላጆቻቸውና ለብዙዎች ታላቅ ደስታ ስለነበረ በተወለዱ ጊዜ ከንጉሠ ነገሥት ዐፄ ምኒልክ ጀምሮ ከየመኳንንቱና ከየመሳፍንቱ እንዲሁም ከአካባቢው ባላባቶችና ነዋሪዎች ብዙ እጅ መንሻ ቀርቦላቸዋል።

ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ሀብተ ወልድና ስመ ክርስትና ከተቀበሉበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዕለተ ዕረፍታቸው ድረስ ከመንፈሳዊ ሕይወት ተለይተው አያውቁም። መከራም ሆነ ደስታ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን አቋርጦባቸው አያውቅም። በተወለዱ በ፯ ዓመት ዕድሜያቸው እነ አለቃ ገብረ መድኅንን የመሳሰሉ መንፈሳውያን መምህራን ተመድበውላቸው ትምህርት በጀመሩ በ፫ ዓመታቸው፣ በተወለዱ በ፲ ዓመታቸው የቃል ትምህርትን፣ የሥነ ጽሕፈት ዕውቀትን፣ የአማርኛን የግዕዝ ትምህርትን አጠናቀው ተምረዋል።

ንጉሠ ነገሥት ከሆኑ በኋላም እነ አለቃ ገብረ መድኅን የመሳሰሉ ዓይናማዎቹን የአብነት መምህራን በቤተ መንግሥታቸው በማሰባሰብ ሠርከ ኅብስት በመፍቀድ ወይም ልብስና ጉርስ በመስጠት የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜንና የቅኔን ትምህርት በሚገባ ተምረዋል። የግርማዊነታቸው ረቂቅ ሰውነት ከልጅነት እስከ ዕውቀት በዚህ ዓይነቱ መንፈሳዊ ሕይወት የተገነባ ስለሆነ የዕለታ ሥራቸው ሁሉ መጀመሪያ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሔ ጸሎት ማቅረብ ነበር፤ በአዲስ አበባና በአካባቢዋ በሚገ አብያተ ክርስቲያናት ዓመታዊ በዓለ ንግሥ የሚከበረ ብዙውን ጊዜ ግርማዊነታቸው በሚገኙበት ነበር በዓመታዊው በዓለ ንግሥ ብቻ ሳይሆን በየወር በዓላቱ በአዘቦቱም ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሔዱ ማስቀደስ መጸለይ፣ ትምህርተ ወንጌልም መስማት፣ ልዑላኑ ልዕልታቱ፣ መኳንንቱና መሳፍንቱ አብረው እየሔ እንዲያስቀድሱና እንዲጸልዩ፣ ትምህርተ ወንጌል እንዲሰሙ ማድረግ ወይም መንፈሳዊ ግዴታቸው እንዲወጡ ማድረግ ከንጉሠ ነገሥት የዕለት ተግባራቸ አንዱ ነበር።

ይህም ብቻ አይደለም በየዓመቱ በጾመ ፍልሰታ ሱባ ወቅት ድሬድዋ እየወረዱ የውዳሴ ማርያምና የቅ ማርያም ትርጓሜ መስማትም አስታጉለው አያውቁ ነበር። ለስብሰባና ለሥራ ጉብኝት ወደ ልዩ ልዩ ክፍ ዓለማት በሚሔዱበትም ጊዜ በቅድሚያ ወደ ኢትዮጵ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በመሔ ቡራኬ ተቀብለውና ወደ ቤተ ክርስቲያን በመድረ የአትርሱኝ ጸሎት አጸልየው ነበር ጉዞአቸው የሚጀምሩት፤ ሲመለሱም በቤተ ክርስቲያን ተገኝተ የምስጋና ጸሎት ያቀርቡ ነበር።

ግርማዊ ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ጾ ጸሎትን፣ ምጽዋትንና ስግደትን የሚወዱ በጠቅላላው ሳይጸልዩ እህል ውሀ የማይቀምሱ ቅዱሳት መጻሕ በሚያዙት ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን የሚያከብሩ ለድሆ



www.ethiopianorthodox.org

ለእንስሳት አራዊትም ጭምር የሚራሩ፣ ሕገ እግዚአብሔርን አክብረው የሚያስከብሩ፣ ለድሃ የሚፈርዱ፣ ከሥጋዊው ነገር ይልቅ መንፈሳዊውን ነገር አጥብቀው የሚወዱ ታላቅ ክርስቲያን ንጉሠ ነገሥት ነበሩ። ይህም በመሆኑ እንጂ በሌላ ጉልበትና ኃይል አልነበረም ፶፱ ዓመት የሥልጣን ዕድሜ ሊያገኙና አብዛኛውን ጊዜ በሰላም ሊኖሩ የቻሉት። በመጨረሻ ጊዜም የሰማዕትነትን ዕረፍት ሊያገኙ የቻሉትና ለንስሓ ሞት የበቁት በዚህ ምክንያት መሆኑ ጥርጥር የለውም። ግርማዊነታቸው ገና ከሕፃንነታቸው ዕድሜ ጀምሮ ቅዱሳት መጻሕፍትንና ጥንታውያን የታሪክ መጻሕፍትን አዘውትረው ማንበብ እንደሚወዱ፣ የዓለም ታሪክንና ፍልስፍናን ያዘሉ ልዩ ልዩ መጻሕፍትንም ማንበብ እንደሚያዘወትሩና እነዚህን ለመሳሰሉት ቅዱሳት መጻሕፍትና የታሪክና የምርምር መጻሕፍትና የግል ቤተ መጻሕፍት እንደነበሩዋቸው የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ጸሐፊዎች መስክረውላቸዋል።

በተለይም እምነትንና ታሪክን አዋሕደው የያዙት የጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታውያን የብራና መጻሕፍት ደብዛቸው እንዳይጠፋና ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፉ ያደርጉት በነበረው ከፍተኛ ጥረት ከአልጋ ወራሽነታቸው ዘመን ጀምሮ መጻሕፍትን ከየቦታው በማሰባሰብ በዘመናዊ ሕትመት እንዲባዙ ያደርጉ እንደ ነበርና አያሌ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናትንም እንዳሳነፁ፣ በዘመን ርዝመት ጉስቁልና የደረሰባቸውንም አብያተ ክርስቲያናት እንዳሳደሱና አብዛኛው አብያተ ክርስቲያናት የታነፁት በግርማዊነታቸው የመሠረት ደንጊያ አስቀማጭነት እንደነበር ዝርዝሩ በዚሁ ታሪካዊ መጽሔት በየሚመለከተው አርእስት የቀረበ ስለሆነ ከዚህ ላይ መዘርዘሩ የሚያሻ መስሎ አይታይም።

ሌላውና ከሁሉም የሚበልጠው የግርማዊ ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴ መንፈሳዊ ሕይወት ምስክር ከልጅነታቸው ጊዜ ጀምሮ መከራና ፈተና በሚገጥማቸው ጊዜ ቀንም ሆነ ሌሊት ወደ ፈጣሪያቸው የሚማጸኑበት ታቦተ ሕግ በየቤተ መንግሥታቸው ከግል ጸሎት ቤታቸው ተለይቶ አያውቅም፤ ለዚህም ጉልህ ማስረጃው ፋሺሽት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረች ጊዜ በእንግሊዝ ሀገር በስደት ላይ ሳሉ ታቦተ መድኃኔዓለምን ከኢየሩሳሌም አስወስደው ባዝ (ባት) ላይ በነበራቸው የጸሎት ቤት ሲጸልዩበት መኖራቸውና ፋሽሽት ኢጣሊያ ድል ሁና ወደ ሀገራቸው በተመለሱበት ወቅት አዲስ አበባ ላይ ምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ብለው በመሠየም ያሳነፁት ቤተ ክርስቲያን ነው።

የግርማዊ ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴ መንፈሳዊ ሕይወት ሌላው ተጨማሪ ምስክር ምንም እንኳ ንጉሠ ነገሥት ቢሆኑም ሥጋ ለባሽ ናቸውና «መሬት ነህና ወደ መሬት ትመለሳለህ» ተብሎ በተነገረው አምላካዊ ቃል መሠረት ለርሳቸውም ሞት እንደማይቀርላቸው ተገንዝበው እግዚአብሔር የፈቀደው ጊዜ ሲደርስ ዛሬ ንጉሣዊ አፅማቸው በንጉሣዊ ክብር በሚያርፍበት ራሳቸው ባሳነፁት በታላቁ የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በሕይወታቸው መቃብራቸውን (መካነ ዕረፍታቸውን) ማሠራታቸው ነው።

«በኦርቶዶክሱ ዓለም የሃይማኖት ጋሻ» የተባሉት የታላቁ ክርስቲያን የግርማዊ ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴ መንፈሳዊ ሕይወት የማጠቃለያ ምስክር ይሆነን ዘንድ በዘመነ ብሉይ ኢየሩሳሌም በአሕዛብ ነገሥታት እጅ በወደቀችና በተማረከች ጊዜ ስለ ሕዝበ እስራኤል ደኅንነትና ስለ ኢየሩሳሌም ሰላም በዘመኑ የነበሩት ፍጹማን አባቶች አቤሜሌክና ባሮክ ባቀረቡት ጸሎት አንጻር የዛሬ ፷፬ ዓመት እንግሊዝ ሀገር በስደት ላይ ሳሉ በባዝ ቤተ ጸሎት ስለኢትዮጵያ ነፃነትና ሰላም፣ ስለ ሕዝቦቿም ደኅንነት በራሳቸው አንደበት ለፈጣሪያቸው ያቀረቡትን ጸሎተ ተማሕፅኖ የዚህ ጽሑፍ መደምደሚያና ማሳረጊያ አድርገን አቅርበነዋል።

«አቤቱ ድካም የሌለብህ ኃያል፣ ኀልፈት የሌለብህ ዘላለማዊ ሆይ የምትሠራውን ሥራህንና ፍርድህን በማድነቅ ከመወሰን በቀር ፍጡር መርምሮ ሊደርስበት አይችልም።

በዚህ ባለፈውና በአሁኑ ዘመን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከተራው ሰው አንስቶ እስከ ንጉሠ ነገሥቱ ለጊዜው በኃዘን ባሕር እንዲሰጥም፣ የኢጣሊያ ሕዝብ እስከ ንጉሡ ለጊዜው በደስታ ባሕር እንዲዋኝ ያደረግህበትን ምክንያት አንተ ብቻ ታውቀዋለህ እንጂ ፍጡር ተመራምሮ ለማወቅ የማይችለው ረቂቅ ምሥጢር ነው።

በአርአያህና በምሳሌህ ከተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ነፍሱን ከሥጋው እስከምትለይበት ቀን ድረስ ከአንተ የሚለምነውን ሁሉ፣ አይደረግልኝም ብሎ ተስፋ የሚቆርጥ ስለሌለ፣ ኢትዮጵያም ነፃነትዋ እንደጠፋና (እንደታወከና) በባዕድ ገዢ እጅ እንደወደቀች እንዳትቀር ሕዝቦቿም የባዕድ ገዢን በመፍራት አፋቸው እንደተዘጋ በቀላል ቀንበርና በደስታ ወደ ሥልጣኔ የሚመራቸውን ኢትዮጵያዊ ገዢያቸውን በማጣት ልባቸው እንደተጨነቀ እንዳይኖሩ የቸርነትህን ሥራ ሠርተህ ታድናቸው ዘንድ እንለምንሃለን።

አቤቱ የስደተኞች ሀገር፣ የዕውሮች ብርሃን ሆይ፤ እውነትና ፍርድ ዙፋኖችህ ናቸው፤ ስለነፃነታችን ከሀገራችን በግፍ ወጥተን የተሰደድነውን እኛንም ተቀበለን። እንደዚህም ብለን እንለምንሃለን። ስለብዙ ምሕረትህ ነው እንጂ ስለጽድቃችን አይደለም...» የሚል ጸሎት ነበር።

ይህም የሚያመለክተው የንጉሠ ነገሥቱ ረቂቅ ሰውነት ከልጅነት እስከ እውቀት በፍጹም መንፈሳዊ ሕይወት ተመላና እምነታቸው በጽኑዕ ዐለት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ነው።

www.ethiopianorthodox.org

# «እስመ በጸሕኮ በበረከት ሠናይ» በመልካም በረከት ደረስህለት

ነቢዩ ዳዊት ይህን የተናገረው ለጊዜው መፍቀሬ እግዚአብሔር ለነበረው ለይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስ ቢሆንም እግዚአብሔርን ለሚወዱ ለግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴም ተፈጽሞላቸዋል።

ንጉሥ ሕዝቅያስ ከእግዚአብሔር ባገኘው ኃይል የይሁዳ ጠላት የነበረውን እስራኤልን ለማጥቃት የመጣውን ሰናክሬምንና እጅግ ብዙ የሆነ ሠራዊቱን ድል አድርጓል። ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴም ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ኃይል ኢትዮጵያን ከውጭ ጠላቶቿ እየተከላከሉ በነፃነትና በሃይማኖት ጠብቀዋታል።



ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በንጉሠ ነገሥትነት ሥርዓት ንግሥ ጊዜ

«በማዳንህ ብዙ ደስ ይለዋል ዕድሜ ለመነህ ሰጠኸው» እንደተባለው ሙሴንና እስራኤልን በባሕረ ኤርትራ ከመስጠም ያዳነ እግዚአብሔር ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴንም ከልዩ ልዩ አደጋና ፈተና ጠብቆ ከሰማንያ ዓመት በላይ ዕድሜ ሰጥቶ ለኢትዮጵያ ቤዛ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

«የሰውነቱን ፍላጎት ሰጠኸው በአንደበ‍ የለመነውንም አላስቀረህበትም» እንደተባለው የጃንሆይ ዋናው ፍላጎትና ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርቡት ጸሎ‍ ሀገርን በሥልጣኔ ጎዳና ማራመድንና የኢትዮጵያ ቤ‍ ክርስቲያን ሥልጣን ወደ ፓትርያርክነት ደረጃ ከ‍ ማድረግ ስለነበረ በዘመነ መንግሥታቸው በግርማዊነታቸው ከፍተኛ ጥረትና ትግል ይህ ሁ‍ ሊፈጸም ችሏል።

«እስመ በጸሕኮ በበረከት ሠናይ፣ በመልካም በረከ‍ ደረስህለት» እንዳለው ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላ‍ ከእግዚአብሔር የታደሉት በረከት ብዙ ነው።

እስከ ንጉሠ ነገሥት በመድረስና ታሪክ በመሥራ‍ ከታሪክ ለመወለድ በቅተዋል። ይህ የእግዚአብሔ‍ ረድኤትና በረከት ነው። በአውሮፓውያን ቅኝ ግዛ‍ ወድቀው ነፃነትን አጥተው ለብዙ ዓመታት በባርነት ይገ‍ የነበሩትን የአፍሪቃን አህጉር በዓለም ሸንጎ በዋናነ‍ እየተሟገቱ ለነፃነት አብቅተዋል። የሰላም ሐዋር‍ ሆነዋል። በዚህም «የአፍሪካ አባት» ተብለዋል። ይህም የእግዚአብሔር በረከት ነው።

በዘመነ መንግሥታቸው ከሠሩዋቸው የታሪካቸ‍ ፍሬዎች ተብለው ሊጠቀሱ ከሚገባቸው ዋና ዋናዎ‍ አዲሲቱ ኢትዮጵያ፣ አዲሲቱ አፍሪቃ፣ የኢትዮጵ‍ ሙሉ ዕድገትና የአፍሪካ አንድነት ድርጅት፣ የኦሬንታ‍ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ፣ የኢትዮጵ‍ መንፈሳዊ መብት ፍጹምነት ናቸው። በእነዚህ ሁ‍ ምክንያቶች ጃንሆይ ባለታሪክ ናቸው። ይህ ሁሉ የሥራ‍ የድካም ውጤት የተገኘው በእግዚአብሔር ረድኤት‍ በረከት ነው። በግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ደ‍ ሥራ ፍጹም ኩራት ከሚሰማቸው አንዷ በመንፈስ ቅዱ‍ እናታቸው የሆነችውና በመንፈሳዊ ትምህርት በአእምሮ‍ እግዚአብሔር ኮትኩታ ያሳደገቻቸው፣ በሥራቸ‍ ከፍተኛ ውለታ ያደረጉላት በጸሎተ ሃይማኖ‍ ስታስጠብቃቸው የኖረችው ክርስቶስን «አንተ ውእ‍ ወልዱ ለእግዚአብሔር በማለት በተዋሕዶ ሃይማኖ‍ የጸናችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ናት።

ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ሕዝባቸው ትምህር‍ ሃይማኖቱን ጠንቅቆ እንዲያውቅ በቃሉ ያጠናው‍ ከመጽሐፍ እንዲያመሳክር፣ ከመጻሕፍት የሚገኘ‍



www.ethiopianorthodox.org

የጥበብ ምንጭ እንዲጠጣና እንዲረካ፣ መጻሕፍትን ለማሳተም ማተሚያ ቤት ለማቋቋም በገንዘባቸው፣ በአስተዋይነታቸውና በብልህ አመራራቸው ቀን ከሌት የሠሩ ሕዝባቸውን ከድንቁርና ወደ ዕውቀት ያሸጋገሩ ታላቅ መሪ ነበሩ። ይህ ሁሉ ዕውቀት፣ ይህ ሁሉ ጥበብ፣ ይህ ሁሉ ትጋት፣ ይህ ሁሉ ብርታት ለንጉሠ ነገሥቱ የተሰጣቸው በእግዚአብሔር ረድኤትና በረከት ነው።

ጃንሆይ አብያተ ክርስቲያናትን ማሳነፅ የጀመሩት ገና በ፲፰ ዓመታቸው መስፍነ ሐረር ከነበሩበት ጊዜ አንሥቶ ነው፤ እግዚአብሔር ለሀገርና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የመረጣቸው ከልጅነታቸው ጀምሮ ስለሆነ ነው።

ባለ ቅኔው ሊቅ አለቃ አርአያ ወሮታ ይህን ተመልክተው «ኃይለ ሥላሴ ኢታንክር አመ እቢለከ፣ ርኢኩከ አንሰ ታሕተዕፀ ሐረር ዓባይ፣ እስመ ሀለወከ ትዕርግ መንበረ ምኒልክ ሰማይ» ብለው በቅኔያቸው ትንቢት ተናግረዋል። ይህም ማለት ኃይለ ሥላሴ በታላቋ በሐረር ዛፍ ሥር አየሁህ ስለ አልሁህ አታድንቅ ገና በምኒልክ ዙፋን ሰማይ ላይ ትወጣለህና» ማለት ነው።

ልዑል እግዚአብሔር ከሕዝቤ የመረጥሁትን አላቅሁ፣ አገልጋዬን የበቃ ሆኖ አገኘሁት የተቀደሰውን ቅብዐ መንግሥት ቀባሁት» አለ።

ስለዚህም የእግዚአብሔር በረከት ተሰጥቶአቸው ንጉሥ ተፈሪ በ፲፱፻፳፫ ዓ.ም ጥቅምት ፳፫ ቀን በዚሁ በመናገሻ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ንጉሠ ነገሥት ተብለው ሲነግሡ የሚከተለው ሥርዓተ ንግሥ ተፈጽሞላቸዋል።

ኢትዮጵያ ሕገ ኦሪትን ከመቀበልዋ በፊት በሕገ ልቡና ሳለች ነገሥታቱ ልብሰ ፀሐይ ወይም አርዕድ አንቀጥቅጥ የሚባለውን ልብሰ መንግሥታቸውን ለብሰው ዘውድ ተቀዳጅተው በትረ መንግሥት ይዘው፣ ሉል ጨብጠው ይነግሡ ነበር። ከጦር መሣሪያዎቻቸውም ጎልተው የሚታዩት ጦርና ቀስት ናቸው፤ ልብሰ መንግሥቱ የግዛታቸውን ስፋትና ግርማቸውን፣ ገናናነታቸውን፣ በትረ መንግሥቱ ተከላካይነታቸውን፣ ጥበቃቸውን፣ ሉሉ በአንድ አምላክ ማመናቸውን፣ ጦሩ የጦር መሪ መሆናቸውን ያሳያል።

እንዲሁም ልብሰ መንግሥታቸው ልብሰ ፀሐይ መባሉ የፀሐይ ብርሃን ለሁሉ እንደሆነ ሥልጣነ መንግሥቱም በሁሉ ላይ የተዘረጋ፣ ሁሉን ለመጠበቅ የቆመ ከመሆኑም በላይ በሕገ ልቡና የነበሩ አማኞች አምላክን ለመፈለግ ፀሐይን ከፍተኛ ምትክ ያደርጉ ነበር። ይህንንም የአብርሃም ታሪክ ያስረዳል።

ኢትዮጵያ በዚያ ጊዜ ከአበው ቃል በቃል በተቀበለችው ትምህርት ሰማይን ከነግሡ ምድርን ከነልብሱ የፈጠረውን አምላክ ታመልክ ነበርና በዚህ ምክንያት ነው።

የንጉሥ ሥልጣን ለሁሉ መሆኑንም ሲያስረዳ «የንጉሥ ሞት፣ የፀሐይ ዕርበት አንድ ነው፤ ፀሐዩን ንጉሥ አሰንብትልን» እያለ ሕዝቡ ይጸልይ ነበር። ይህም ከአበው የወረደ ትምህርት ነው።

ኢትዮጵያ ሃይማኖተ ኦሪትን ከተቀበለች በኋላ ነገሥታቱም የቀድሞውን የክብር ምልክት አሳይተው በሕገ መጽሐፍ የሚነግሡ ሆነዋል። በዚህም ጊዜ ባለ አልማዝ ቀለበት አድርገው፣ ሰይፍ ታጥቀው፣ ቅብዐ መንግሥት ተቀብተው፣ ዳግም ሕግ ተነብቦላቸው ሃይማኖትንና ሀገርን ሊጠብቁ በእግዚአብሔር ስም እየማሉ የሚነግሡ ሆነዋል።

ሰይፍ፣ ሥልጣናቸው ሥጋዊና መንፈሳዊ ኃይል ያለበት መሆኑን፣ ቀለበቱ ሃይማኖታቸውን፣ ቅብዐ መንግሥቱ፣ መንፈስ ረድኤት የሚሰጣቸው መሆኑን ያመለክታል። የንጉሡ ሥርዓት የመንግሥተ እስራኤልን ባህል ስለያዘ ነቢዩ ሳሙኤል ሳዖል በመንግሥቱ የሚፈጽመውን ሁሉ አስቀድሞ ለሕዝቡ እንደ አወጀላቸው፣ በዚህም ንጉሠ ነገሥቱ ሕዝቡን ሊያስተዳድርበት ያሰበው ዓዋጅ ይገለጥበታል። እንዲሁም ነቢዩ ሳሙኤል ዳዊትን በወንድሞቹ መካከል ቅብዐ መንግሥት እንደ ቀባው፣ ሊቀ ካህናቱ ንጉሠ ነገሥቱን በሕዝቡ መካከል ቀብቶ ያነግሠው ነበር። ንጉሠ ነገሥቱም እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝ ሕዝቡን እንዲመራ፣ ሥራውን እንዲሠራ በኦሪት ዘዳግም ም.፲፯ ቁ.፲፬–፳ ያለውን የእግዚአብሔር ትእዛዝ ካህኑ አንብቦ በእግዚአብሔር ስም ያምለው ነበር። ከዚህ በኋላ መዘምራኑ ከዳዊት መዝሙር ዓርባ አራተኛውን መዝሙር እየዘመሩ ሥርዓተ ንግሡ ሲፈጸም ዘመናት አልፈዋል።

ኢትዮጵያ ሃይማኖተ ወንጌልን ከተቀበለች በኋላም ሥርዓተ ንግሡ የክርስትና ሠርዓት ተጨምሮበታል በኦሪት ሌዋውያን ካህናት ፈንታ ወንጌላውያን ካህናት፣ በሊቀ ካህናቱ ፈንታ ሊቀ ጳጳሳት፣ በቤተ መቅደስ ፋንታ ቤተ ክርስቲያን፣ በመሥዋዕተ ኦሪት ፈንታ መሥዋዕተ ወንጌል ተተክተዋል። ጸሎቱ ብሉይ ኪዳንን ያስተባበረ፣ ምክሩ በትንቢተ ነቢያት ላይ ስብከተ ሐዋርያትን ያጣመረ ስለሆነ በመዝሙረ ዳዊት ላይ መልእክታተ ሐዋርያት፣ ግብረ ሐዋርያት ወንጌል ይነበቡ ነበር። በእነዚህም መጻሕፍት ምክር ይሰጥ ነበር። በዚህ ዓይነት ሥርዓቱ ሲፈጸም እንደኖረ ሁሉ ይህ ሥርዓተ ንግሥ በበለጠና በተሻለ ለግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በአዲስ አበባ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሞ ዘውድ ተቀዳጅተው ንጉሠ ነገሥት ተብለው ነግሠዋል። ይህ ሁሉ ክብር ለግርማዊነታቸው የተፈጸመ እግዚአብሔር በረድኤትና በበረከት ስለ ጎበኛቸው ነው፤ ዛሬም አፅማቸው በግፈኞች ተጥሎና ተደብቆ ሳይቀር ተገኝቶ በክብር በቤተ ክርስቲያን እንዲያርፍ መደረጉ ከእግዚአብሔር አስቀድሞ የተሰጣቸው መልካም በረከት ያልተለያቸው መሆኑን ያሳያል። ✣




www.ethiopianorthodox.org

# ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዕድገት ያደረጉት ጥረት

## ሀ. በዘመናዊ አስተዳደር

ኢትዮጵያ ክርስትናን በ፫፻ ዓ.ም ተቀብላ አቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን አብርሃ ወአጽብሐን በ፫፻፴ ዓ.ም ካጠመቁበት ዘመን አንስቶ እስከ ፲፱፻፷፯ ዓ.ም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ ድረስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብሔራዊ የመንግሥት ሃይማኖት ሆና ኖሯል። በእነዚህ ዘመናት በኢትዮጵያ የነበረው አስተዳደር መንፈሳዊና ሥጋዊ አስተዳደርን ያጣመረ ነበር።



ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ የዘመናዊ አስተዳደር ሥርዓት የተዘረጋው በ፲፱ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ቢሆንም አሁን ባለው መልኩ የተደራጀው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ነው። ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያን ሥልጣኔ ለማፋጠን በነበራቸው ጽኑ ዓላማ ልዩ ልዩ መንግሥታዊ ድርጅቶችን ሲመሠርቱና በየዘርፉ
ሲያስፋፉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ
ክርስቲያንም በዘመናዊ አስተዳደር እንድትመ
አድርገዋል።

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በዘመና
የአስተዳዳር ስልት ለመምራት የመጀመሪያው እር
ጃቸው ለ፲፮ መቶ ዓመታት በበላይነት ጳጳሳት እየሾመ
ከኖረችው ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን ነፃ ማውጣት ነበር
የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከግብጽ ቤ
ክርስቲያን ነፃ ለማውጣት የተነሣሡት ኢትዮጵያው
ሊቃውንት ቤተ ክርስቲያናቸውን በጵጵስና መምራ
እንዳለባቸው በማመናቸውና ዘመናዊ አስተዳደር
ተግባራዊ ለማድረግ የነበራቸው እቅድ ነው።

ስለዚህ ገና የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽና ባለሙ
ሥልጣን እንደራሴ እንደሆኑ የግብጽ ቤተክርስቲ
ኢትዮጵያውያን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትን በጳጳስነ
እንድትሾም ጠየቁ። በዚህም መሠረት በኢትዮጵያ ታሪ
ለመጀመሪያ ጊዜ አምስት ኢትዮጵያውያን ሊቃውን
ግንቦት ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ.ም በግብጽ ጵጵስና ተሾሙ
በዚህ መልክ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲ
በስድስት አህጉረ ስብከት ተከፋፍላ መንፈሳ
አገልግሎቷንና ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋት ላይ እያለ
በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም ኢጣልያ ኢትዮጵያን ወረረች። ከተሾሙ
ጳጳሳት መካከል ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ በአዲስ አበባ፣ ብፁ
አቡነ ሚካኤል በኢሊባቦር ለሀገራቸውና ለቤተ
ርስቲያናቸው ነፃነት ሲሉ በጣሊያን ወራሪዎች ተገደሉ
ግብጻዊው አቡነ ቄርሎስ ግን ከኢትዮጵያ ሸሽተው ወጡ

ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አዲስ ክሥተ
አስከተለ። ይኸውም የጣሊያን ወራሪዎች የኢትዮ
ቤተክርስቲያን ከግብጽ ቤተክርስቲያን ነፃ መውጣ
አወጁ። ቀደም ሲል ተሹመው የነበሩትን አቡነ አብርሃ
ሊቀ ጳጳስ አድርገው ሾሙ። በዚህ ዘመን ብዙ ኢት
ጵያውያን ሊቃውንት በጳጳስነት እንዲሾሙ አደረጉ።

ከጣልያን ወረራ በኋላ ፈርሶ የነበረውን ዘመ
መንግሥታዊ አስተዳዳር ንጉሠ ነገሥቱ መልሰ
ሲያቋቁሙ፣ ጀምረውት የነበረውን የቤተ ክርስቲ
ዘመናዊ አስተዳደርም እንዲያንሠራራ አደረጉ። በጣሊ
ወረራ ዘመን ተቋርጦ የነበረው የኢትዮጵያ ኦርቶዶ
ቤተክርስቲያንና የግብጽ ቤተክርስቲያን ግንኙ



www.ethiopianorthodox.org

እንዲታደስ ለማድረግ የመልእክትና የሐሳብ ልውውጥ ሲያደርጉ ቆየተው በመጨረሻ በ፲፱፻፵ ዓ.ም በካይሮ ስምምነት ተፈረመ።

ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በዚህ መልክ ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት ይልቅ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት እንዲሾሙ በማድረግ ለዘመናዊ አስተዳደር ምቹ ሁኔታ ፈጥረዋል።

ንጉሠ ነገሥቱ ቤተክርስቲያናችን ከሥጋዊ አስተዳደር ጋር ሥራዋን እኩል እንድትመራ ለማድረግ ከግብጽ ቤተክርስቲያን ነፃ እስክትወጣ አልጠበቁም። «ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ» በሚለው የሕይወት ታሪካቸው መጽሐፍ እንደገለፁት ከሊቃውንቱና ከመምህራኑ ጋር እየተገናኙ የቤተ ክህነት ሥራ ጥቂት በጥቂት እየተሻሻለ እንዲሄድ ማድረጋቸውን ያብራራሉ። ይኸውም በታላላቅ ገዳማትና አድባራት አስተዳዳሪዎችና በካህናት መካከል የሚፈጠረውን ያለመግባባት ለማስወገድ የሚያስችሉ ደንቦች ማውጣታቸውን፣ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ስም በግለሰቦች የተያዙት መሬቶች በቀጥታ በየአብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ይዞታ ሥር ውለው ከእነዚህ መሬቶች የሚገኘው ገቢ ከአብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት አገልግሎት የሚተርፈው ገንዘብ ለትምህርት ቤቶች፣ ለሆስፒታሎች፣ ለሽማግሎች መጦሪያና ለድሆች ልጆች ማሳደጊያ እንዲውል ማድረጋቸውን መረዳት የቻላል።

ይህንንም ዓላማቸውን ሥራ ላይ ለማዋልና ለሌሎችም አርአያ ለመሆን ሲሉ ከአድባራትና ከገዳማት መሬት የተገኘው ገቢ ለአገልግሎት ክፍያ ውሎ በተረፈው ገንዘብ በዝቋላ ደብረ ከዋክብት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም፣ በአዲስ ዓለም ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም፣ በአሰቦት በደብረ ወገግ የቅድስት ሥላሴና የጻድቁ አቡነ ሣሙኤል ገዳም፣ በአዲስ አበባም በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ታዕካ ነገሥት በአታ ለማርያም ልዩ ልዩ የማኅበራዊ አገልግሎቶች እንዲቋቋሙ አድርገዋል።

በሌላ ክፍል በዝርዝር እንደተገለጸው ለቤተክርስቲያን ነፃነት የታገሉትን ያህል አስተዳደሯም ዘመናዊ መልክ እንዲይዝ ልዩ ለዩ መምሪያዎችን፣ ትእዛዞችንና ደንቦችን አውጥተዋል።

፩. ገና የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ እያሉ በወቅቱ ራስ ተፈሪ መኰንን መጋቢት ፩ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ.ም በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያን ገዳም አስተዳደር የሚመለከት ፲፰ ክፍሎች ያሉት ዝርዝር ደንብ መንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ እና በራሳቸው ስም አውጥተው ሥራ ላይ እንዲውል አድርገዋል። መመሪያው የሚያጠቃልለው የገዳሙን መምህር መንግሥት እንደሚሾም፣ ስለገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም፣ ስለመነኮሳቱ መንፈሳዊ ሕይወትና አገልግሎት፣ ስለ፲፪ የገዳሙ አማካሪዎች ተግባር፣ ስለሥራ ክፍፍል እና እነዚህን ስለመሳሰሉት ነው።

፪. በመጀመሪያ ለተሾሙት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት አህጉረ ስብከት ካደላደሉ በኋላ በመሠረታዊ አስተዳደር ተግባር አለማምደዋቸዋል። ዝርዝር አስተዳደራዊ የሥራ መመሪያዎችን በመስጠት ሥራ ላይ እንዲያውሉት አድርገዋል። ንጉሠ ነገሥቱ ባወጡት ደንብ መሠረት ጳጳሳቱ በዓመት እየተሰበሰቡ ስለሥራቸው እየተወያዩ ምእመናንን በተሻለ መንገድ የሚያገለግሉበትን መንገድ እንዲፈልጉ፣ ምእመናኑን በየቦታው እየተዘዋወሩ እንዲያስተምሩ፣ ስለገንዘብ ምንጭና አጠቃቀም፣ በይዞታቸው ስር ስለነበሩት ጉዳዮች የነበራቸው የዳኝነት ሥልጣንና ስለመንፈሳዊ አገልግሎታቸው መመሪያ ሰጥተዋል።

፫. ለእያንዳንዱ ገዳምና ደብር የሚያገለግል ልዩ ልዩ አስተዳደራዊ ሕጎችን ደንግገዋል። ነሐሴ ፴ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ.ም «ለተከለሉ አድባራት የተሰጠ ደንብ» በሚል ርእስ ባወጡት ባለ ፲፬ ነጥብ ደንብ እያንዳንዱ ደብር በይዞታው ሥር ስላለው ንብረት አያያዝና አጠቃቀም፣ በንብረቱ ላይ በሚገኙት ሰዎች መካከል ክርክር ሲነሳ በጉዳዩ ላይ ስላላቸው የመወሰን ሥልጣን ዝርዝር ድንጋጌ አውጥተዋል። ከዚህም ሌላ መጋቢት ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ.ም ስለዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ቤት ያወጡት የአስተዳደር መመሪያ ፵፮ አንቀጾችን የያዘ ሲሆን ዝርዝሩ ስለበአታ ሊቀ ሊቃውንት ሹመት፣ ሥልጣንና ኃላፊነት፣ በስሩ ስለሚገኙ የቤተክርስቲያን ሠራተኞችና የተቋሞች የሥራ ድርሻ፣ ስለንብረት አያያዝና አጠቃቀም በዝርዝር ያስርዳል።

፬. መጋቢት ፩ ቀን ፲፱፻፴፬ ዓ.ም ያወጡት ደንብ ፲፪ አንቀጽ ያለው ሲሆን ስለቤተክርስቲያን የመሬት ይዞታ፣ ስለካህናት አስተዳደር፣ ስለደመወዝ ክፍያና ስለሹመት ይዘረዝራል።

፭. አጠቃላይ አስተዳደራዊ ትእዛዝ የወጣው ሚያዝያ ፳ ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ.ም ሲሆን ንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዙን ያወጡት አዲሱን የኢትዮጵያ ትውልድ መንፈሳዊ ፍላጎት ለማርካት፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ኃላፊነቷ እያደገ በመሄዱ አማንያንን በሚገባ ለማገልገል እንድትችል ተጨማሪ ሥልጣን ለመስጠትና ኃላፊነቷን ለማስታወቅ ነው።

በዚህ ትእዛዝ መሠረት ፓትርያርኩ ሰብሳቢ የሆኑበት፣ ሊቃነ ጳጳሳትና በፓትርያርኩ አቅራቢነት ንጉሠ ነገሥቱ የሚሾሟቸው ስምንት ምዕመናን የሚገኙበት የቤተክህነት ጉባዔ አቋቁመዋል።



www.ethiopianorthodox.org

ይህ ትእዛዝ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በዘመናዊ አስተዳደር ሥርዓት ሥራዋን እንድትመራ ደንግጓል። በትእዛዙ መሠረት ቤተክርስቲያን የምዕመናንን ፈላጎት ለማሟላት የሚያስችላትን ተግባር እንድታከናውን፣ ንብረቷን ለመጠበቅ፣ አዳዲስ ንብረት ለማፍራት፣ ለማሻሻልና አስፈላጊ ሆኖ የተገኘውን ተግባር ሁሉ ለመፈጸም ሙሉ ሥልጣን ሰጥቷታል።

በዚህ ትእዛዝ መሠረት ቤተክርስቲያን ውል ለመዋዋል፣ ለመክሰስና ለመከሰስ ሀብት ለመቀበልና ለማፍራት፣ ለማስተዳደር፣ ለማንቀሳቀስ፣ ገንዘብ ለመበደር፣ ሥልጣኗን ለመወከል፣ አስተዳደራዊ ሥራዋን ለመሥራት የሚያስችላት ደንብ ለማውጣት ሙሉ ሥልጣን ተሰጥቷታል።

አስተዳደራቸውን በሚያሻሽሉበት ጊዜ ሁሉ የቤተክርስቲያኒቱንም አስተዳደር ዘመናዊ መል ለማስያዝ ኃላፊነት እንደነበረባቸው ሙሉ ግንዛበ ነበራቸው። በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፻፳፮ መሠረ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሥጋዊ አስተዳደርና ድርጅት በሕ እንደሚመራ አመልክቷል።

ዛሬም የሀገሪቱ አስተዳደር ሕግ አካል የሆነው የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ ፫ ቁጥር ፫፻፺፰ ሕጋዊ ሰውነ እንዳላት፣ በቁጥር ፫፻፺፱ የየሀገረ ስብከቱ አድባራት ገዳማት በአስተዳደር ሕጐች መሠረት መብት ግዴታዎችም እንዳሏቸው ያረጋግጣል።

እነዚህን መመሪያዎችና ደንቦች መሠረት በማድረ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በዘመና



በ፲፱፻፳፩ ዓ.ም የተሾሙት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ዘመናዊ የሥራ አመራር ኖሯት የሚጠበቅባትን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶች በብቃት መወጣት እንዲያስችላት ያወጧቸው ልዩ ልዩ ትእዛዞችና ደንቦች መሠረታቸው በወቅቱ የሀገሪቱ ሕጎች ሁሉ ምንጭ የሆነው ሕገ መንግሥትና ዛሬም የሀገራችን ሕግ አካል የሆነው የፍትሐብሔር ሕግ ደግፈዋቸዋል።

የንጉሠ ነገሥቱ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፩፻፳፮ እንደሚያስረዳው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት መሠረታዊት ቤተክርስቲያን ሆናለች። በመሆኑም ንጉሠ ነገሥቱ ሥጋዊ

መልክ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ለመስጠት ወንጌልን ለማስፋፋት በሚያስችል መልክ ከመንበ ፓትርያርክ ጀምሮ እስከ ሀገረ ስብከት አስተዳደራ መዋቅር እንዲዘረጋ አድርገዋል። አሁን ያለው የጠቅላ ቤተክህነት መነሻና መሠረቱም ይኸው ነው።

ቤተክርስቲያናችንን ዛሬ ካላት የአስተዳደር ተቋም ላ ያደረሷት በብዙ ሂደትና ጥረት ነበር። ቀደም ሲል የግብጽ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስ እያሉ የቤተክህነ አስተዳደራዊ ሥራ ይመራ የነበረው በእጨጌው ሲሆ ጽ/ቤቱም በታላቁ ቤተ መንግሥት ዕንቁላል ቤት በመባ በሚታወቀው ቤት ውስጥ ነበር። ኢትዮጵያ ከዜ



www.ethiopianorthodox.org

መካከል ሊቀ ጳጳሳት ከሾመች በኋላ ከመንግሥት ባለሥልጣኖች አሉ ከሚባሉት መካከል ንጉሠ ነገሥቱ እየመረጡ በልዩ ልዩ ማዕረግ፣ በዋና ዳይሬክተርነት፣ በሥራ አስኪያጅነትና፣ በመጨረሻም በሚኒስትርነት ማዕረግ፣ በመሾም ቤተክርስቲያኒቱን በዘመናዊ አስተዳደር እንድትመራ አድርገዋል።

ጠቅላይ ቤተክህነት ሲመሠረት በየሀገረ ስብከቱ የሚያካሂዳቸውን ልዩ ልዩ ሥራዎች ማስፈጸሚያ ከቤተክርስቲያን መሬት ላይ ታክስ እንዲሰበሰብ፣ ለቤተክርስቲያን የገቢ ምንጭ ለመፍጠር በአዲስ አበባ ታላላቅ ሕንፃዎችን በመሥራት ከነዚህም ምንጮች በተገኘው ገቢ በየሀገረ ስብከቱ መምህራንንና የአስተዳደር ሠራተኞችን መድቦ እንዲያሠሩ ሥራቸውን በአግባቡ ማካሄዳቸውን እየተቆጣጠረ ቤተ ክርስቲያን የሚጠበቅባትን ሥራ እንድታከናውን አድርገዋል።

ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ቤተክርስቲያንን በዘመናዊ አስተዳደር ለመምራት በነበራቸው ጽኑ ፍላጐት በዚህ መጽሔት በሌላ ክፍል በዝርዝር እንደቀረበው ዘመናዊ የመንፈሳዊ ትምህርት ቤቶችን አቋቁመው ወጣቶች ከቤተክርስቲያን ትምህርት ጋር ዘመናዊ ትምህርት እንዲማሩና ቤተክርስቲያናቸውን እንዲያስተዳድሩ፣ እንዲመሩ አድርገዋል።

በሠለጠኑት ሀገሮች የሚገኙት ሌሎቹም አብያተ ክርስቲያናት ሥራቸውን እንዴት እንደሚመሩ ልምድና ዕውቀት እንዲቀስሙ ለማስቻል ወጣቶችን በግብጽ፣ በግሪክ፣ በእንግሊዝ፣ በሶቭዬት ኅብረት፣ በሮማንያና በአሜሪካ በሌሎችም ሀገሮች ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት እንዲማሩ አድርገዋል። ከእነዚህም ወጣቶች መካከል ጥቂቶቹ በቤተ ክርስቲያን ዛሬም በማገልገል ላይ የሚገኙ ሲሆን ለቤተክርስቲያን አመራር የበቁም እንዳሉ ይታወቃል።

ስለዚህ ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ኢትዮጵያን በዘመናዊ ሥልጣኔ ለማራመድ ያሳዩትን ጥረት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ዘመናዊ የአስተዳደር ሥርዓት ዘርግተው ሕገ መንግሥታዊ ድጋፍ የሰጡ ከመሆኑም ሌላ ራሳቸው የጉዳዩ ባለቤት በመሆን አስተዳደርዋ እንዲቃና ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል።

በመሆኑም አሁን ቤተክርስቲያናችን የምትከተለው የአስተዳደር ሥርዓት፣ የአህጉረ ስብከት ክፍፍል፣ በየሀገረ ስብከቱ መንበረ ጵጵስና መቋቋም፣ ከዋናው መ/ቤት ጀምሮ እስከ ሀገረ ስብከት ከዚያም በታች እስከ አጥቢያ ቤተክርስቲያን የተዘረጋው የሥልጣን ተዋረድና ሰንሰለት የተመሠረተውና የተጠናከረው ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በጣሉት መሠረት በመሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ታላቅ ባለውለታ ናቸው። ✣

## ሰ. መንፈሳዊ መብትን በማስጠበቅ

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ውለታ የዋሉ ሰፊ ታሪክ የሠሩ ታላቅ ንጉሠ ነገሥት ስለ ነበሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለእርሳቸው የምትሰጠው ክብር በእጅጉ የላቀ ነው። ርቱዐ ሃይማኖት ዳግማዊ ቆስጠንጢኖስ ትላቸዋለች።

በመሠረቱ የኢትዮጵያን ታሪክ ስንመለከት ይች አገር የታሪክ ቀዳሚነት ካላቸው የዓለም ዐበይት አህጉር አንድዋ መሆንዋን እንገነዘባለን። የኢትዮጵያ ጥንታዊነት የሚረጋገጠውም የእውነት ምንጭ በሆነው በቅዱስ መጻሕፍ ነው። ኢትዮጵያ ድኅረ ማየ አይሀ የኖኅ የልጅ ልጅ ከሆነው የኢትዮጵያ አባት በመባል ከሚታወቀው ከኩሽ ጀምሮ በዘመነ በጥሊሞስ ማለት ከልደተ ክርስቶስ በፊት በ፪፻፹፭ ዓመት በሰባ ሊቃናት «ኢትዮጵያ» የሚል ስያሜ እስካገኘችበት ዘመን ድረስ ኩሽ እየተባለች የምትጠራ ነበረች። እንደ ዕብራውያን በአምልኮተ እግዚአብሔር ጸንታ እደ ሕሊናዋን ወደ እግዚአብሔር ዘርግታ የምትኖር ቅድስት ሀገር ስለ መሆንዋም «ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር» ተብሎ ተጽፎላታል። መዝ.፷፯፥፴፩።

የኢትዮጵያ ቀዳሚነት፣ ክብርና ልዕልና ጎልቶ የሚታወቀው በቅድመ ክርስትና በነበረው ዘመን ብቻ አልነበረም። እምነተ ክርስትናን በመቀበል ረገድም በኢየሩሳሌም ዙርያ ከሚኖሩ የፍልስጥኤም አውራጃዎች በቀር ሌላውን ዓለም ቀድማ በ፴፬ ዓመተ ምሕረት ክርስትናን የተቀበለች አገር ኢትዮጵያ በመሆንዋ በክብር ላይ ክብር አግኝታለች። የታሪክ ብኩርናዋን ጠብቃለች፣ ግብ.ሐ ፰፥፳፯።

ይሁንና የክርስትና እምነትን ለማስፋፋት የሚረዱ ሥርዓቶች ያልተሟሉ በመኖራቸው ኢትዮጵያ በራሷ ፈቃድና ውዴታ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ያመጡላት ዘንድ በመልክዐ ምድር ወደምትቀርባት፣ በታሪክ ወደምትመስላት ወደ ግብጽ ልጆችዋን ላከች። ደጋግ ነገሥታት ዒዛናና ሳይዛና (አብርሃወአጽብሃ) መልእክተኞቻቸውን በቅንነት ወደ እስክንድርያ ሲልኩ



www.ethiopianorthodox.org

መልሱንም ከደጉ አባት ከቅዱስ አትናቴዎስ በቅንነት አግኝተው ነበር።

በዚህ መሠረት የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ኤጲስ ቆጶስ ቅዱስ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ከቅዱሳን ነገሥታት አብርሃ ወአጽብሓ ጋር በመሆን የወንጌል ብርሃን በመላ ኢትዮጵያ እንዲያበራ አድርገዋል። ዳሩ ግን ይህ የቅንነት ሥራ በግብጻውያን ዘንድ ፈሩን ለቆ ወደ ግል ክብር ማስጠበቂያነት በመለወጡ፣ «ወሰብአ ኢትዮጵያሰ ኢይሢሙ ሊቀ እማእምራኒሆሙ» የሚል ጥንት ያልነበረ

ክፍለ ዘመን በቅዱስ ሀርቤ (ገብረ ማርያም) ዘመ
መንግሥት የቀረበው ጥያቄ ከባድና ወሳኝ ጥያቄ በመሆ
ንጉሥ ሀርቤ «ጥያቄዬ መልስ የማያገኝ ከሆነ ዓባይ
በካርቱም በኩል ዘግቼ ከግብጽ እንዲቋረጥ አደርጋለሁ»
በሚል ቁርጥ ሐሳብ ተነስቶ እንደነበር ይነገራል።

ይህ ጥያቄ ሲወድቅ ሲነሳ፣ ሲታወስ ሲረሳ፣ ከቆ
በኋላ ዐፄ ዮሐንስ አራተኛ ለግብጽ ቤተ ክርስቲያ
ያቀረቡት ጥያቄ በግብጻዊ ሊቀ ጳጳስ የሚመ
ኢትዮጵያውያን አባቶች እንዲሾሙ ነበር። ነገር ግ



በ፲፱፻፵ ዓ.ም አምስቱ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት በካይሮ በመንበረ ቅዱስ ማርቆስ ካቴድራል በተሾሙበት ጊዜ
ግርማዊነታቸው በጸሎተ ቅዳሴ ላይ

የፈጠራ አንቀጽ፣ እንግዳ ሰርዋጽ በመጨመር ሢመተ ጵጵስናን ለኢትዮጵያውያን መስጠት ከእግዚአብሔር መቅሰፍትን የሚያመጣ እንደሆነ አድርገው ለማሳመን ስብከታቸውን ቀጠሉበት። ይህም ብቻ አይደለም ሚያዝያ ፲ ቀን በሚነበበው ስንክሳር ላይም «የኢትዮጵያ ሰዎች ጵጵስናን ስለ ፈለጉ እግዚአብሔር ተቆጥቶ በሀገራቸው ሦስት ዓመት ሙሉ ዝናም ከልክሎ በድርቅ ቀጣቸው» የሚል ጽሑፍ አስቀምጠዋል።

ይህ በሰባተኛው ክፍለ ዘመን የገባ ሰርዋጽ አባባሉ የግብጻውያንን ተጥባበ ነገር ከማመልከት አልፎ ቅንጣት ታህል የእውነት መሠረትነት እንደሌለው አከራካሪ ባይሆንም ለእግዚአብሔር መንግሥት መስፋፋት እንጂ ለግል ዝናና ክብር ጭንቀት ያልነበራቸው የኢትዮጵያ ሊቃውንት ግን በቀጭን ክር ታስሮ ረዥም ዘመን መኳዝን መረጡ፤ ችግሩ እየከፋ ዘመን እየሰፋ በሄደ ቁጥር ግን ጥያቄ ማንሳቱ የማይታለፍ ሆነ፤ በተለይም በ፲፩ኛው መቶ

ግብጻውያን፣ ኢትዮጵያውያንን ከመሾም ይል
የራሳቸውን ሰው ቁጥር ጨምሮ መላክን ስለ መረጠ
በ፲፰፻፸፬ ዓመተ ምሕረት አራት ግብጻውያን ጳጳሳ
ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ተደረገ።

ይሁን እንጂ አገልግሎት ላልተሟላላት፣ ተጽዕኖው
ችግሩ ለበዛባት ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ግን ይህ መል
ዘላቂ መልስ የሚሆን አልነበረም ችግሩ በዘላቂነት ሊፈ
የሚችለው «ወሰብአ ኢትዮጵያሰ ኢይሢሙ ሊ
እማእምራኒሆሙ» የሚለው አንቀጽ ተሰር
ኢትዮጵያውያን አባቶች የጵጵስና ማዕርግ አግኝተ
ሕዝባቸውን በአግባቡ ማገልገል የሚችሉበት መብ
ሲያገኙ ብቻ እንደሆነ በብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን ዘን
የሚታመንበት ጉዳይ ሆነና በመንግሥትም ሆነ በቤ
ክርስቲያን አባቶች ዘንድ ጥያቄው ቀጠለ።

ነገር ግን እግዚአብሔር በዚህ ላይ ሥራው
የሚሠራበት ጊዜ ባለመድረሱ ለነቢየ እግዚአብሔ



www.ethiopianorthodox.org

ለቅዱስ ዳዊት «አኮ አንተ ዘተሐንጽ ሊተ ቤተ አላወልድከ ዘይወጽእ እምሐቌከ» ቤት የምትሠራልኝ አንተ አይደለህም፣ ልጅህ ነው እንጂ ተብሎ እንደተነገረው ሁሉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ መብት የማስፈጸሙ ዕድል ለቀደምት ነገሥታት ሳይሆን ለግርማዊ ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ዕድል ሆነ። በዚህ መሠረት ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ገና የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከመባላቸው በፊት ከአልጋ ወራሽነት ዘመናቸው ጊዜ ጀምሮ በሙሉ ፍላጎትና ፈቃደኝነት ጠረቱን ቀጠሉበት።

ከ፲፱፻፲፱ ዓ.ም በፊት ከግብጻዊው የኢትዮጵያ ጳጳስ ከአቡነ ማቴዎስ ዕረፍት በኋላ በሀገሩ ስፋት መጠን ለስብከተ ወንጌል አገልግሎት የሚያስፈልጉ በዛ ያሉ ኢትዮጵያውያን አባቶች እንዲሾሙ ጠበቅ ያለ ጥያቄ ለግብጽ ቤተ ክርስቲያን የቀረበው በልዑል አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ተፈሪ መኰንን ነበር። ከዚያ ዘመን ጀምሮ የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን ለኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ይገባል የሚለው ጥያቄ እየተጠናከረ ቀጠለ እንጂ አልተቋረጠም።

በዚህ መሠረት የእስክንድርያው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሐንስ እንደተሾሙ የቀረበው ጥያቄ፣ ከመንበረ ማርቆስ አንድ ሊቀ ጳጳሳት እንዲሾምና ሊቀ ጳጳሳቱም በአዲስ አበባ ኤጲስቆጳሳትን እንዲሾም የሚል ነበር፣ ነገር ግን ግብጻዊው ፓትርያርክ ይህንን አሳብ ለመቀበል ፈቃደኛ አልሆኑም ነበር። የፓትርያርኩ ፍላጎት አንድ ግብጻዊ ሊቀ ጳጳሳትና ከኢትዮጵያውያንም እጨጌውን ብቻ ለመሾም፣ እንዲሁም ሊቀ ጳጳሳቱን የሚረዱ ሁለት ግብጻውያን ጳጳሳትን ለመመደብ ነበር። ይሁን እንጂ ይህ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ፈላጎት አሁንም በቂ ሆኖ ባለመገኘቱ የተሻለ ውጤት ለማግኘት፣ ኢትዮጵያውያን ልኡካን ከቤተ መንግሥት እና ከቤተ ክህነት ወደ ግብጽ እንዲላኩ ተመረጠና በብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ የሚመራ የልኡካን ቡድን ወደ ካይሮ ተላከ።

በዚህ ጊዜ ከብዙ ውይይትና ውጣ ውረድ በኋላ፣ ግንቦት ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ.ም በተደረገ ስብሰባ፣ በአንድ ግብጻዊ ሊቀ ጳጳሳት የሚመሩ አምስት ኢትዮጵያውያን አባቶች ጵጵስና እንዲሾሙ ስምምነት ላይ ተደረሰ።

በዚህ የስምምነት ውሳኔ መሠረት፣ ለኤጲስ ቆጶስነት ከተመረጡ አምስት ኢትዮጵያውያን አባቶች አራቱን ይዘው ወደ ግብጽ እንዲሔዱ የገንዘብ ሚኒስቴሩ ሚኒስትር ክቡር በጅሮንድ ዘለቀ አግደው ስለ ታዘዙ፣ ከንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከንጉሥ ተፈሪ፣ ለግብጽ ቤተ ክርስቲያን ከተጻፈ ደብዳቤ ጋር ወደ ካይሮ ተጓዙ።

ጉዞው በውሳኔ ላይ የተመሠረተ የብዙ ጊዜ ጥረት ውጤት በመሆኑ፣ ግንቦት ፳፭ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ.ም አራት ኢትዮጵያውያን አባቶች በመንበረ ማርቆስ ሥርዓቱ ተፈጽሞላቸው የጵጵስና ማዕርግ ለማግኘት በቁና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ታላቅ ግምት የተሰጠው የመጀመሪያው የታሪክ ምዕራፍ ኾነ። እነሱም በኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ታሪክ ቀዳሚውን ምዕራፍ ለመያዝ የበቁ ዕድለኞች ተባሉ።

እነዚህ ለኢትዮጵያውያን ጵጵስና መሾም የታሪክ ምዕራፍ በር ከፋቾች በመሆን የታሪክ ብኵርና ለማግኘት የታደሉ አባቶችም፣

፩ኛ. ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ – የትግራይና የሰሜን ጳጳስ

፪ኛ. ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ – የወሎና የላስታ ጳጳስ

፫ኛ. ብፁዕ አቡነ አብርሃም – የጎዳምና የጎንደር ጳጳስ

፬ኛ. ብፁዕ አቡነ ሚካኤል – የምዕራብ ኢትዮጵያ ጳጳስ ናቸው።

ምንም እንኳ ብፁዕ እጨጌ ገብር መንፈስ ቅዱስ በጤና ምክንያት ወደ ካይሮ መሔድ ባለመቻላቸው የተሾሙ ኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጶሳት አራት ብቻ ቢሆኑም፣ የግንቦቱ የስምምነት ውሳኔ የሚያመለክተው ግን፣ አምስት ኢትዮጵያውያን አባቶች እንዲሾሙ በመሆኑ፣ በአጋጣሚ ሁኔታ የኢትዮጵያ የክብር እንግዳ ሆነው አዲስ አበባ የተገኙ የእስክንድርያው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሐንስ፣ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ኤጲስ ቆጶስነት እንዲሾሙ በመፍቀዳቸው ጥር ፩ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ.ም በዕለተ ሐሙስ በአዲስ አበባ ከተማ በታዕካ ነገሥት በአታ ለማርያም ሥርዓተ ሢመቱ ተፈጽሞላቸው ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ በመባል አምስተኛው ኢትዮጵያዊ ኤጲስ ቆጶስ ሆነው ተሾሙ።

ከ፮ ዓመታት በኋላም በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በመውረርዋ በመንፈሳዊና በማኅበራዊ ዘርፍ የደረሰው ግፍና በደል ከ እስከ የሌለው እንደ ነበር ሁሉም ያውቃል።

ሀገሪቱን ከቤተ ክርስቲያኒቱ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱን ከሀገሪቱ ነጥሎ ማየት ፈጽሞ የሚቻል ባለመሆኑ በአገሪቱ የተፈጸመው ሁሉ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይም ተፈጽሟል። ለሀገራቸው ክብርና ነፃነት፣ አበው ጳጳሳት በርካታ ሊቃውንት ካህናትና ምእመናን የሕይወት መሥዋዕትነት ከፍለዋል፣ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ተቃጥለዋል፣ አያሌ



www.ethiopianorthodox.org

ነዋያተ ቅድሳት ተዘርፈዋል፣ ቁጥር ስፍር የሌለው የቤተ ክርስቲያኒቱ ሀብትና ንብረት ተዘርፏል።

ይሁንና ከአምስት ዓመታት የኢትዮጵያውያን አርበኞች ብርቱ ተጋድሎና ከንጉሠ ነገሥቱ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት በኋላ፣ ፈቃደ እግዚአብሔር ሆኖ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በድል አድራጊነት ወደ ሀገራቸው በተመለሱ ጊዜ ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጋር የነበረው ግንኙነት እንዲቀጥል የማድረጉን ጉዳይ ያልዘነጉት ስለ ነበር፣ ጊዜ ሳይወስድ በ፲፱፻፴፬ ዓ.ም ካይሮ ባለው የኢትዮጵያ መንግሥት ጉዳይ አስፈጻሚ

ጉዳዩ በዚህ መልኩ ለሁለት ዓመታት ያህል ከቆየ በኋ ግን አቡነ መቃርዮስ የመንበረ ማርቆስ ፓትርያርክ ሆነው ስ ተመረጡ ፓትርያርኩ ራሳቸው በሁለቱ አብያተ ክርስቲያና ያለው ንግግር እንዲቀጥል መጋቢት ፳፫ ቀን ፲፱፻፴፮ ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ለግርማዊነታቸው ጥያቄ አቀረቡ።

የፓትርያርኩ ጥያቄ በግርማዊነታቸውና በቤ ክርስቲያኒቱ በኩል ተቀባይነት በማግኘቱም ፓትርያርክ መልእክተኞቻቸውን ወደ አዲስ አበባ ላኩ፡ መልእክተኞቹም በግርማዊነታቸው ከታዘዙ አምስ ባለሥልጣኖች ጋር በመሆን በብፁዕ እጬጌ ገብረ ጊዮርጊ



በ፲፱፻፳ ዓ.ም የተሾሙት አምስቱ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት

በኩል ንግግር እንዲጀመር አደረጉ፤ በዚህ ጥረትም፣ ግብጻዊው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሐንስ ግንቦት ፲፰ ቀን ፲፱፻፴፬ ዓ.ም መልእክተኞቻቸውን ወደ አዲስ አበባ ላኩ። እነዚህ መልእክተኞች በግርማዊነታቸው ከታዘዙ ባለሥልጣኖችና ከቤተ ክርስቲያኒቱ ኃላፊዎች ጋር ሲመካከሩ ከሰነበቱ በኋላ በግብጽ ሲኖዶስ የተላለፈው ውግዘት በቅድሚያ እንዲነሣና በሌሎች ጉዳዮች ላይ ንግግሩ እንዲቀጥል የሚል ዐቢይ ውሳኔ ተላለፈ።

ይሁን እንጂ ፓትርያርኩ በማረፋቸው ምክንያት ይሁን በሌላ፣ ምክንያቱ በግልጽ የታወቀ ባይሆንም፣ ተጠባባቂ ፓትርያርክ ሆነው በተሠየሙ በአቡነ ዮሳብ የተመራው የግብጹ ሲኖዶስ ግን ውሳኔውን በከፊል ስለ ተቀበለውና የግዝቱ አፈታትም በከፊል እንዲሆን የሚል ስለ ነበር፣ ግርማዊነታቸውንም ሆነ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ደስ የሚያሰኝ ውሳኔ አልነበረም።

ሰብሳቢነት (በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ) ከሰኔ ፲ እስከ ፳፩ ቀን ፲፱፻፴፮ ዓ.ም ሲነጋገሩ ከቆዩ በኋ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄዎችን ግልፅ የሚያደር በስድስት አንቀጾች የተካተተ ውሳኔ ለግብጽ ቤ ክርስቲያን እንዲቀርብ ተደረገ።

ነገር ግን ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄ መል ነው ተብሎ የካቲት ፳፪ ቀን ፲፱፻፴፯ ዓ.ም ከፓትርያርክ የተላከው መልስ በሰላም ፈንታ ክርክርን የሚያሰፋ ሆና በመገኘቱ መጋቢት ፲፰ ቀን ፲፱፻፴፯ ዓ.ም ሌላ መል ከቤተ ክርስቲያኒቱና ከቤተ መንግሥት ተጻፈ። ይሁ እንጂ በእስክንድርያው ፓትርያርክ በብፁዕ ወቅዱስ አቡ መቃርዮስ ዕረፍት ምክንያት አንደገና ነገሩ ዘገየ።

ቢሆንም፣ ጥር ፩ ቀን ፲፱፻፴፰ ዓ.ም ክቡር ፊታውራ ሀብተ ሚካኤልና፣ ብላታ መርስዔኀዘን ወልደ ቂርቆስ ወ



www.ethiopianorthodox.org

ካይሮ ተላኩና የጽሑፍ መልእክታቸውን ለአቡነ አትናቴዎስ ተጠባባቂ ፓትርያርክ አቀረቡ።

ጥር ፳፫ ቀን የተሰበሰበው የግብጹ ሲኖዶስ ግን ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄ ውጪ ሁለት ግብጻውያን ኤጲስ ቆጶሳት በኢትዮጵያ እንዲሾሙ ስለ ወሰነ ክርክሩ ቀጠለ፤ ከብዙ ክርክር በኋላም ወደፊት በግንቦት ወር የፓትርያርኩ ምርጫና በዓለ ሢመት እንደተፈጸመ አምስት ኢትዮጵያውያን አባቶች እንዲሾሙ ስምምነት ላይ ተደረሰና በሲኖዶሱ ውሳኔና በስምምነቱ መሠረት ለጵጵስና የተመረጡ አምስት ኢትዮጵያውያን አባቶች በግንቦት ወር ፲፱፻፵፰ ዓ.ም ወደ ካይሮ ተጓዙ።

የፓትርያርኩ ሥርዓተ ሢመት ግንቦት ፲ ቀን ፲፱፻፵፰ ዓ.ም እንደ ተፈጸመ ኢትዮጵያውያኑ ጳጳሳት የሚሾሙበት ቀን ሲጠበቅ ሳለ ግን ኢትዮጵያዊው ሊቀ ጳጳሳት በበታቹ ጳጳሳትንና ኤጲስ ቆጶሳትን እንዳይሾም የሚያግድ ውል በመቅረቡ ሌላ የክርክር መድረክ ተከፈተ። ይሾማሉ ተብለው የተላኩ አባቶችም በመጡበት አካሄድ ተመልሰው አገራቸው ገቡ። በግብጽና በኢተዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የነበረው ግንኙነትም ለሁለት ዓመት ያህል ተቋርጦ ቆየ።

ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት የሰጡት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ግን በችግሩ ሳይማረሩ፣ በግብጻውያን ተንኮል ሳይበገሩ፣ ተቋርጦ የቆየው ንግግር መቀጠል ይችል ዘንድ መልእክተኞችን በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም ወደ ካይሮ ላኩ። ውይይቱ ቀጠለ፣ አምስቱ ኢትዮጵያውያን አባቶች ካለምንም ቅድመ ሁኔታ ጵጵስና እንዲሾሙ ስምምነት ላይ ተደረሰ። ይልቁንም ከግብጻዊው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ከአቡነ ቄርሎስ በኋላ የሚቀጥለው ሊቀ ጳጳሳት ኢትዮጵያዊ እንዲሆን በመወሰኑ፣ አዲስ ውጤት ብቅ ማለት ጀመረ። በዚህ ውሣኔ መሠረትም አምስቱ ኢትዮጵያውያን አባቶች ሐምሌ ፲፰ ቀን ፲፱፻፵፱ ዓ.ም ካይሮ ላይ በፓትርያርክ ዮሳብ እጅ ተቀብተው ጵጵስና ተሾሙ። እነሱም፤

፩. ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ – የሸዋ ጳጳስ

፪. ብፁዕ አቡነ ሚካኤል – የጎንደር ጳጳስ

፫. ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ – የሐረር ጳጳስ

፬. ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ – የነቀምት ጳጳስ

፭. ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ – የይርጋዓለም ጳጳስ ናቸው።

ግብጻዊው ሊቀ ጳጳሳት ጥቅምት ፲፪ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ.ም እንዳረፉ ኢትዮጵያዊው ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስም ጥር ፮ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ.ም በፓትርያርክ ዮሳብ ፈቃድ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ ለመሆን በቁ። ኢትዮጵያዊው ሊቀ ጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ባስልዮስም ነሐሴ ፳፯ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ.ም አምስት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳትን ሾሙ፤ እነሱም

፩. ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ – የጎሬ ጳጳስ

፪. ብፁዕ አቡነ ገብርኤል – የወሎ ጳጳስ

፫. ብፁዕ አቡነ ፊሊጶስ – የኢየሩሳሌም ጳጳስ

፬. ብፁዕ አቡነ ማርቆስ – የኤርትራ ጳጳስ

፭. ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ – የከፋ ጳጳስ ናቸው።

ቀጥለውም ብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ባስልዮስ ግንቦት ፲፮ ቀን ፲፱፻፵፭ ዓ.ም ሦስት ጳጳሳትን፣ ሐምሌ ፳፩ ቀን ፲፱፻፵፰ ዓ.ም አንድ ጳጳስ ቀብተው ሾሙ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መብት በማይናወጥ መሠረት ላይ ተጥሎ አስተማማኝ ደረጃ ላይ ደረሰ። ግብጻውያንን ተለማምጦ የመኖሩ ጉዳይ የማብቂያ ጊዜ ሆነ። ለምሳሌ ታኅሣሥ ፲፯ ቀን ፲፱፻፵፱ ዓ.ም ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለግብጽ ቤተ ክርስቲያን የተጻፈ ደብዳቤን ስንመለከት እንዲህ የሚል ነበር። «በፓትርያርኩ ምርጫ ተካፋይ እንድትሆን ለቤተ ክርስቲያናችን ስለ ላካችሁት ጥሪ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ጉዳይ ያላት አግባብ በደንባችሁ ውስጥ በግልጽ ያልተወሰነ በመሆኑ፣ ባለፉት ፓትርያርክም ላይ ያደረጋችሁት ውሳኔ በአስከተለው አድራጎት የቤተ ክርስቲያናችን የሚገባት መብት ባለመከበሩ አሁን በምርጫው ላይ ለመገኘት ያለመቻላችንን ስንገልጽ እናዝናለን።» «በምርጫው ሕግ ውስጥ የኢትዮጵያ መብት በሚገባ ስላልተገለጸና ይገባናል ስለምንለው መብት ለምርጫው ተካፋይ ከመሆናችን በፊት መልእክተኛ እንድንልክና አስቀድሞ እንድንነጋገርበት»። የሚል ቁርጥ ውሳኔ ነበር። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በአቋሟ ስለ ጸናችም የመንበረ ማርቆስ ተጠባባቂ ፓትርያርክ ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፵፱ ዓ.ም ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በጻፉት ደብዳቤ የኢትዮጵያውያን መራጮች ስም ዝርዝር ይላክላቸው ዘንድ ግርማዊነታቸውን በመማጸን ለወደፊትም ቢሆን ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና ከግርማዊነታቸው ጋር አስቀድሞ ሳይመካከሩበትና በጉዳዩ ተካፋይ ሳይሆኑ ምንም ዓይነት ውሳኔ እንዳይደረግ የግብጽ ቅዱስ ሲኖዶስ የወሰነ መሆኑን አረጋገጡ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ፣ የተላከላቸውን ልመና በመቀበል መልእክተኞች ወደ ግብጽ እንዲሄዱ ስለ ፈቀዱ በግርማዊነታቸው ውሳኔ በልዑል ደጃዝማች አሥራተ ካሣ



www.ethiopianorthodox.org

መሪነት ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ያሉበት አምስት ልኡካን ግንቦት ፲፯ ቀን ፲፱፻፶ ዓ.ም ወደ ካይሮ እንዲጓዙ ተደረገ። ኮሚቴው የሄደው ፓትርያርክ መርጦ ለመመለስ ብቻ ስላልነበረ ሌሎች ክርክሮችም ሲካሄዱ ሰነበቱ። ከነጥቦቹ መካከልም፣

፩ኛ. የመራጭነት መብት በሕዝበ ክርስቲያኑ ብዛት መጠን እንዲሆን

፪ኛ. ለፓትርያርክነት ዕጩ ሆኖ የሚቀርበው አባት የወገን ልዩነት ሳይደረግ ይሁን

፫ኛ. ያለፈው የፓትርያርኩ የምርጫ ሕግ ተሽሮ እንደገና እንዲሻሻል ስለ ፓትርያርኩ ምርጫና ስለ መንፈሳዊው ጉዳይ ባለሥልጣኑ ቅዱስ ሲኖዶስ ብቻ ይሁን የሚሉ ነበሩ።

ግብጻውያን በከፊልም ቢሆን ሐሳቡን ሲቀበሉ ፓትርያርኩ ግብጻዊ ተወላጅ መሆን አለበት የሚለው አቋማቸው ግን የማይለወጥ ኾነ፤ ክርክሩ በጣም እየጠነከረ በመሄዱም ለመግባቢያ ሲሉ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ደረጃ ወደ ምክትል ፓትርያርክነት ከፍ እንዲል ሐሳብ አቀረቡ።

ይህ ሐሳብ አዲስ መስሎ የሚታይ ቢሆንም የኢትዮጵያ ልኡካን ግን፣ ምክትል ፓትርያርክ ደረጃ በሚል ሐሳብ ፈጽመው እንደማይስማሙ አረጋገጡ፤ የኾነ ሆኖ ግን ለጊዜው፣

- ኢትዮጵያውያን በመራጭነት ረገድ እኩልነት እንዲያገኙ
- የምርጫው ሕግ ተለውጦ በስምምነት እንዲወሰን
- ስለ ምርጫውና ስለ መንፈሳዊው ጉዳይ ባለሥልጣነ ቅዱስ ሲኖዶስ እንዲሆን
- ፓትርያርኩ ለጊዜው ግብጻዊ እንዲሆን በማለት ለወቅቱ ምርጫ ብቻ የሚያገለግል ጊዜያዊ ስምምነት ላይ ተደረሰ።

ግብጻውያን በዚህ እንቅስቃሴ ደስተኞች አልሆኑም፤ በሕልማቸውም በውናቸውም ሥልጣን ከእጃቸው ሲያፈተልክ ይታያቸውና እንቅልፍ ይነሳቸዋል፤ ቃላቸውንና ውሳኔያቸውን እንዳያከብሩ ያደርጋቸዋል። በዚህ ምክንያት ታኅሣሥ ፲፯ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ.ም ግብጻዊው ተጠባባቂ ፓትርያርክ የተሻሻለው የምርጫ ሕግ በሥራ ላይ ሊውል ያልቻለ መሆኑን ገልጸው ጻፉ። የኢትዮጵ[ያ] ቤተ ክርስቲያን ግን ከተፈረመው ስምምነት ውስጥ አንዱ ስንኳ ቢጎድል መላው ስምምነት እንደፈረ[ሰ] እንደምትቆጥረውና የምርጫው ሕግ በሥራ ላይ ሳይው[ል] ቀርቶ ያለ ኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ተካፋይነ[ት] ፓትርያርክ ቢመረጥ የራስዋ ፓትርያርክ አድር[ጋ] የማትቀበል መሆንዋንና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መብት የሚያስጠብቅ መፍትሔ እስከሚገኝ ድረስ ራስዋ[ን] ችላ፣ የራስዋን ሥራ በበኩልዋ የምትፈጽም መሆንዋ[ን] በግልጽ አስታወቀች።

ግብጻውያን በአንድ በኩል ውሳኔያቸውን እየጣሱ ቃላቸውን እያፈረሱ፣ ችግር ሲፈጥሩ፣ በሌላ በኩል ደግ[ሞ] ግርማዊነታቸውን በጎን ለማሳመን ጥረት ያደርጉ ነበር፤



ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የፓትርያርክነት በዓለ ሢመት ላይ ንጉሣዊ ንግግር ሲያደርጉ



www.ethiopianorthodox.org

ስለሆነመ ሚያዝያ ፲፪ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ መልእክተኞች ይላኩላቸው ዘንድ ግርማዊነታቸውን በመለመን ለማግባባት ሞክረው ነበር።

ከግርማዊነታቸው ያገኙት መልስ ግን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መብት በሚገባ ታውቆ ከመረጋገጡ በፊት መልእክተኞችን መላክ የማይቻል መሆኑ የሚል ነበር እንጂ እንዳሰቡት አልሆነላቸውም።

የግርማዊነታቸውንና የቤተ ክርስቲያኒቱን ቁርጥ አሳብ የተረዱ ግብጻውያንም አዲስ የተመረጡት ፓትርያርክ ቄርሎስ ስድስተኛ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መብት ላይ ያላቸውን አቋም ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በአስቸኳይ እንዲገልጹ አደረጉ። በዚህ መሠረት፣ ፓትርያርኩ፣

፩ኛ. የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መሪ ማዕርግ ለማሳደግና ሥልጣኑንም ከፍ ለማድረግ ያሰቡ መሆናቸውን፤

፪ኛ. ይህን ሐሳብ በግልጽ የሚያስረዱ ሦስት ጳጳሳትና አራት ምእመናን ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ ማቀዳቸውን፣ በመግለጽ ግንቦት ፳ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ለግርማዊነታቸው ማረጋገጫ ሰጡ። ይኸው ሐሳብ በግርማዊነታቸው ዘንድ ተቀባይነት በማግኘቱ የፓትርያርኩ ልዑካን ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ተፈቀደና መልእክተኞቹ ግንቦት ፳፬ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ.ም አዲስ አበባ ገቡ። የፓፓው ልዑካንም፣ ኢትዮጵያዊውን ሊቀ ጳጳሳት በፓትርያርክነት ማዕርግ ከፍ ለማድረግና ፓትርያርኩም ሙሉ መብት እንዲኖረው ለመፍቀድ ፓፓው የተዘጋጁ መሆናቸውን አረጋገጡ።

ይህ መልካም ጅምር፣ መልኩን ሳይለውጥ ፍጻሜ ለመድረስ በማሰብ የኢትዮጵያ መልእክተኞች ወደ ካይሮ እንዲሄዱ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈቃድ ስለ ተሰጠ ሰኔ ፬ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ.ም በልዑል ደጃዝማች አሥራተ ካሣ መሪነት ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስና ብላታ መርስዔ ኃዘን ወልደ ቂርቆስ አባላት የሆኑበት ቡድን ተላከ። የግርማዊነታቸውንም ደብዳቤ ለፓፓው አቀረቡ።

በዚህ ጊዜ በሁለቱም አብያተ ክርስቲያናት መካከል ሰፊ ክርክርና ውይይት የታየበት ድርድር ከተካሄደ በኋላ ሰኔ ፲፰ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ.ም ስምምነት ላይ የተደረሰበት ታሪካዊ ሰነድ በፕሮቶኮል ተፈረመ። ሰነዱ በፓፓው መጽደቅ ስለ ነበረበት ለፓትርያርክ ቄርሎስ ፮ኛ ቀርቦ ከጸደቀ በኋላ የማጽደቂያው ጽሑፍ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ተላከ። ይህን ታላቅ የምሥራች ያገኙ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም ግብጽን ለመጎብኘት ፈቃደኛ በመሆን ካይሮ ሲገቡ በተለይም ለግብጽ ቤተ ክርስቲያን ልዩና ታላቅ ክብር ሆነ።

የዚህ የግርማዊነታቸው ጉብኝት ክብሩ፣ ለግብጽ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄንም ወሳኝ ምዕራፍ ላይ የሚያደርስ ታሪካዊ ጉብኝት ነበር። የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የካይሮ ጉብኝት የቤተ ክርስቲያኒቱን ጉዳይ መሠረት ያደረገ በመሆኑ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የፓትርያርክነት ደረጃ የማግኘቱ ጉዳይ በግርማዊነታቸውና በፓፓው በተደረገ ውይይት የመጨረሻውን እልባት እንዳስገኘ ተረጋገጠ።

በዚህ መሠረት የኢትዮጵያው ፓትርያርክ በዓለ ሢመት ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ.ም እንዲሆን ስለ ተወሰነና የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ ብፁዕ ሊቀ ጳጳሳቱ አቡነ ባስልዮስ እንዲሆኑ መፈቀዱን ሰኔ ፳ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ.ም የተጻፈ ደብዳቤ በልዑል ደጃዝማች አሥራተ ካሣ እጅ ለግብጽ ፓፓ ለቄርሎስ ፮ኛ ተሰጠ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስም ከክብር ተከታዮቻቸው ጋር ሰኔ ፲፱ ቀን ካይሮ ገብተው ነበር።

ለሥርዓተ ሢመቱ በወጣው መርሐ ግብር መሠረትም ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ.ም እሑድ ዕለት የኢትዮጵያዊው የብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ሢመተ ፕትርክና ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በተገኙበት ተፈጸመ። ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ በፓፓው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ፮ኛ እጅ የፓትርያርክነት አክሊል ተቀዳጁ። የመጀመሪያውም ኢትዮጵያዊ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ለመሆን በቁ፤ ዕለቷ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዕለተ ኀሪት ሆነች። የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የዘመናት ጠረትና የቤተ ክርስቲያኒቱ ፍላጎት በእግዚአብሔር ፈቃድ ተፈጸመ «ወሰብአ ኢትዮጵያሰ ኢይሢሙ ሊቀ እማዕምራኒሆሙ» የምትለው ያቺ ዕፀ በለስዋ የሐሰት ሥርዋጽ ፍሬ ሳይገኝባት ደርቃ ቀረች፤ ሥርዋም ተነቀለ። የቤተ ክርስቲያናችን ሙሉ መብትና ፍጹም ክብር እውን ሆነ። ኢትዮጵያውያን አባቶችም፣ ኤጲስ ቆጶሳት፣ ሊቃነ ጳጳሳትና ከዚያም አልፎ ፓትርያርኮች ለመሆን በቁ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴ፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለዘመናት አጥታው የኖረችውን መንፈሳዊ መብትና ታላቅ ክብር እንድትቀዳጅ ያደረጉት፣ በ፴፩ ዓመታት ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ብቻ አልነበረም፤ ብዙ ገንዘብ ተከፍሎበታል፣ ብዙ ንብረትም ታክሎበታል፣ ስጦታው፣ ሽልማቱና፣ ገጸ በረከቱ ቀላል አልነበረም።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ ቤተ ክርስቲያኒቱ በሳቸው ዘመን የሚገባትን መብትና ክብር እንድታገኝ፣ ጥረታቸውንና ድካማቸውን ለባረከላቸው ለኃያሉ



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር ምስጋናቸውን አቀረቡ እንጂ እንዲህ አደረግሁኝ ብለው በግላቸው አልተኩራሩበትም ነበር፤ ይህ ሁኔታም የግርማዊነታቸውን ታላቅ ሰውነትና ሃይማኖታዊ ሕይወት የሚያረጋግጥ ነው።

ለምሳሌ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ እንደተሾሙ ግርማዊነታቸው ባደረጉት ንግግር፤ «በአፍሪቃ መካከል የክርስቲያን ደሴት ኾና የኖረችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚገባትን ትልቅነትና ክብር እንድታገኝ በዘመናችን ደክመንበታል። ድካማችንን ባርኮ ይህንን ፍሬ እንዲያፈራ ላደረገልንና ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ

ግርማዊነትዎ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ለማሳደግ ይህ ዛሬ የተገኘው ማዕርግ ከነመብቱ ለኢትዮጵያ እንዲሆ ባለፉት ፴፩ ዓመታት ውስጥ ያደረገው ድካምና ትጋ ይህን ፍሬ ለማፍራት በቅቷል። እስከ ዛሬም ድረስ ወደዚ ግብ ለመድረስ በግርማዊነትዎ ለተደረገው ሰላማዊ ትግ መደምደሚያው ይሆናል...» ብለው ነበር።

እንግዲህ በአንድ ግብጻዊ አባት ስትመራ የኖረች ቤተ ክርስቲያን፤ ያ ሁሉ የተጽዕኖ ዘመን አልፎ ክብርዋን መብትዋን አስጠበቀች። ዘመነ አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን



ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ለብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ኒሻን ሲሸልሙ

ለኢትዮጵያ የተገኘበትን ይህን ቀን ለማየት ላበቃን ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋናችንን እናቀርባለን። ...ይህ ከፍተኛ ሥራ በዘመናችን ተጀምሮ በዘመናችን እንዲፈጸም ዕድል ስላገኘን ለእግዚአብሔር የምናቀርበው ምስጋና ከፍ ያለ ነው» ያሉትን ስንመለከት ከፍ ብሎ የተጠቀሰውን አባባል ግልፅ ያደርግልናል።

እንዲሁም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ በወቅቱ ባደረጉት ንግግር ላይ፤

«...በግርማዊነትዎ መሪነት ሁል ጊዜ ከክብር ወደ ክብር በመሸጋገር ላደገችው ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይህ የፓትርያርክነት ማዕርግ ዛሬ ስለ ተፈጸመላትና ለዚሁ ማዕርግ የኔ ደካማ ሰውነት ቀዳሚነትን ለማግኘት ስለ ታደለ ከሁሉ አስቀድሜ ለልዑል እግዚአብሔር መስጋና አቀርባለሁ።

ሳይጨምር፤ ከ፫፻፶፮ ዓ.ም እስከ ፲፱፻፳፩ ዓ.ም ድረስ በ፳፻፳፭ ዓመታት ውስጥ ወደ ኢትዮጵያ የተላኩ ግብጻውያን ጳጳሳት ፩፻፱ ብቻ ሲሆኑ፤ የኢትዮጵያውያን አባቶች ጵጵስና መሾም ከጀመሩበት ከ፲፱፻፳፩ ዓ.ም ጀምር ይህ የታሪክ ማስታወሻ እስከ ተጻፈበት እስከ ወርኃ ጥቅምት ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ባለው አጭር ጊዜ ውስጥ ግን (በ፫ ዓመታት ብቻ) ቤተ ክርስቲያናችን የ፺፰ ጳጳሳት፤ የ፭ ፓትርያርኮችና በአገር ውስጥ የ፴፯ አህጉረ ስብከት በውጪው ዓለምም የ፲ አህጉረ ስብከት በጠቅላላ የ፵፯ አህጉረ ስብከት ባለቤት ለመሆን በቅታለች። በአሁኑ ጊዜ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ፤ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፤ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የሚመራ ቅዱስ ሲኖዶስ ያላ



www.ethiopianorthodox.org

ሲሆን ፶፪ቱ ኤጲስ ቆጶሳትና ሊቃነ ጳጳሳት በሕይወት ያሉ ናቸው። አንድን የውጭ ዜጋ አባት እያጣች ስትቸገር የኖረች ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ በአገር ውስጥና በውጭው ዓለም በራስዋ ልጆች የምትገለገል ሆናለች።

ይህ በታሪክ ምዕራፍ ታላቅ ትርጉም ያለው ውጤት የተገኘው በባለታሪኩ ታላቅ ንጉሠ ነገሥት በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ብርቱ ጥረት እንጂ በአጋጣሚ አልነበረም። እንደ እውነቱ ከሆነ የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ታላቅ ሰውነት፣ ደግነትና ሰፊ ታሪክ በዚህ ማስታወሻ ተቀንጭቦ እንዲቀርብ ሲደረግ በማስታወሻነቱ እንዲጠቅም ታስቦ እንጂ ታሪኩን ያሟላል ተብሎ አይደለም።

እንደ እውነቱ ከሆነ የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማንነትና ታሪካዊ ሥራ የሚገለጠው ከመቃብር በላይ በዋለው ሕያው ሥራቸውና በጽሑፍ በተመዘገበው ታሪካቸው ብቻ አልሆነም፤ ሰው ቢከዳቸውም ከሳቸው ዕረፍት በኋላ እሳቸውን ተከትሎ ብቅ ያለው ሥርዓትና ዘመንም የሳቸውን ማንነት አፍ አውጥቶ መስክሮላቸዋል። በነጭና በቀይ ሽብር ምክንያት በልጆችዋ ደም የታጠበችው የኢትዮጵያ ምድር «ማረኝ ኃይለ ሥላሴ ማረኝ» ብላለች።

እውነት መናገር፣ እውነት መመስከር ከተቻለ ዘንድ፣ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴ፣ የአፍሪካ ኮከብ፣ የኢትዮጵያ ብርሃን፣ የሰላም አባት፣ የነፃነት አርበኛ፣ የሃይማኖት ጋሻ ለመባል ያበቃቸውን ሰፊ ታሪክ ያለው ሥራ የሠሩ በመላው ዓለም አንቱ ተብለው የተከበሩ፣ በኢትዮጵያ የሥልጣኔ ጮራ እንዲያበራ የጣሩ፣ አዲሱ ትውልድ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆን ያደረጉ፣ ሕዝባቸውንም በሰላም፣ በነፃነትና በጥበብ ጎዳና የመሩ ታላቅ ባለታሪክ፣ ንጉሠ ነገሥት ነበሩ።

ደርግ ግን ሳይበድሉት በደላቸው፤ በበጎ ፋንታ የክፉ ብድራት ከፈላቸው፤ ካለ ፍርድ በግፍ ገደላቸው፤ የመቃብር ቦታ ስንኳ ነፍጓቸው የትም ጣላቸው፤ ታሪካቸው እንዲረሳ፣ ዝክረ ስማቸው እንዳይወሳ ብርቱ ጠንቃቄና ተጽዕኖ አደረገ።

ያልረሳቸው እግዚአብሔር ግን በጊዜው ጊዜ ስማቸው ተነሥቶ ራሳቸው «መካነ ዕረፍቴ ብለው ባሠሩት መካነ መቃብር አፅማቸው እንዲያርፍ ስለ ፈቀደ፣ እነሆ ዛሬ ክቡር አፅማቸው በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በክብር ለማረፍ ችሏል። ✣

# ሐ. አብያተ ክርስቲያናትን በማሳነፅ

«...ከወገብህ የሚወጣውን ዘርህን ከአንተ በኋላ አስነሣለሁ፣ እርሱ ለስሜ ቤት ይሠራል፣ (፪ኛሳሙ.፯፥፲፪–፲፫)።

ይህ ቃል ንጉሥ ዳዊት የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ለመሥራት አስቦ ሳለ ቤተ መቅደስን የሚሠራለት እሱ ሳይሆን ከአብራኩ የሚወጣው ልጁ ሰሎሞን መሆኑን እግዚአብሔር ለዳዊት የሰጠውን ተስፋ የሚገልፅ ነው።

በዚህ ተስፋ መሠረት ንጉሥ ሰሎሞን በዳዊት ዙፋን ተተክቶ በነገሠ በአራተኛ ዓመቱ የቤተ መቅደስን ሥራ ጀምሮ እጅግ ከፍ ባለ ጥበብ ስለ ሠራ እግዚአብሔር በሥራው ተደስቶ «ለዘለዓለም ስሜ በዚያ ያድር ዘንድ ይህን የሠራኸውን ቤት ቀድሻለሁ ዓይኖቼና ልቤም በዘመኑ ሁሉ በዚያ ይሆናሉ» ብሎታል። (፩ኛነገ.፱፥፫)።

ከዚህ በላይ በቀረቡት ጥቅሶች እንደተጠቆመው የእግዚአብሔር ስም መመስገኛ፣ የምእመናን መማፀኛ የሆነውን ቤተመቅደስ ወይም ቤተ ክርስቲያን ማሠራት የተቀደሰና እግዚአብሔር የሚወደው ተግባር መሆኑን የተገነዘቡት የኢትዮጵያ ነገሥታት ከአብርሃ ወአጽባሓ ጀምሮ ዛሬ በቅርስነታቸው አኩሪ የሆኑትን አብያተ ክርስቲያናት በአክሱም፣ በላሊበላ፣ በጣና ሐይቅና በሌሎችም ቦታዎች አሠርተው አልፈዋል።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴም የደጋጉን ነገሥታት አርአያ በመከተል ገና ከደጃዝማችነታቸው ጀምሮ በአልጋወራሽነታቸው ጊዜና ከነገሡም በኋላ በዘመናቸው የተደረሰበትን የሕንፃ ጥበብ ሥራ ላይ በማዋል በየቦታውና በየጊዜው ታላላቅ ካቴድራሎችንና ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትን አሳንፀዋል። መሣፍንቱና መኳንንቱ፣ ሻለቃውና ምስለኔው በገዢነት በየተመደቡበት ግዛት ሁሉ አዳዲስ ቤተ ክርስቲያን እንዲያሠሩ፣ የፈረሰውን፣ ያረጀውን እንዲያሳድሱ ሐምሌ ፲፫ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ.ም ባወጡት አዋጅ እንደሚከተለው አዘዋል።

«መኳንንትም፣ የሻለቃም በሰጠንህ ግዛት ለነፍስ ደኅንነት፣ ለሰላም ኑሮ ዕረፍት የሚለመንበት ቤተ እግዚአብሔር ሳይሠራ የመኖሪያ ቤትህን በማደራጀት ባላገሩም ተጐዳን ብሎ ይጮኻል። ቤተ ክርስቲያን በመፍረሱ፣ የተሠራውም ከተበላሸ በኋላ ባለመታደሱ ተቆርቋሪ ስላላገኘ ለነፍስም ጉዳት፣ ለሥጋም መቅሠፍት የሚያመጣ ሆኗልና በያውራጃህ የተተከሉትን አብያተ ክርስቲያናት የፈረሰውንም አሠራ፣ ያረጀውንም አሳድስ። የሃይማኖት መሠረቱ የክርስቲያን ምልክቱ ቤተክርስቲያን መሥራት ነው።»



www.ethiopianorthodox.org

ግርማዊነታቸው ይህን አዋጅ ካወጁ በኋላ ራሳቸው አርአያ በመሆን በየክፍላተ ሀገሩ፣ በየከተማው ትላልቅ አድባራትንና ገዳማትን ማሠራት ጀመሩ። ከእነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።


## ፩ኛ. መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል

ግርማዊ ጃንሆይ ንጉሠ ነገሥት ከተባሉ በኋላ ካሠሯቸው አብያተ ክርስቲያናት አንዱ መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ነው። ታኅሣሥ ፲፫ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ.ም የመሠረቱን ድንጋይ ጥለው ሥራው በጥሩ ሁኔታ ተጀምሮ ለፍጻሜ ሊደርስ ጥቂት ሲቀረው ጠላት በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም ሀገራችንን ስለ ወረረ ቢቋረጥም በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም ንጉሠ ነገሥቱ በድል አድራጊነት ሲመለሱ ሥራው እንደገና ቀጠለ። በቅልጥፍና እንዲካሄድ ስለ ተደረገም በሚገባ ተጠናቆ ጥር ፯ ቀን ፲፱፻፴፮ ዓ.ም ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ። መታሰቢያነቱ በ፳ቱ የጠላት ወረራ ዓመታት ለተዋጉት አርበኞች እንዲሆን ከማድረጋቸውም ጋር ቅዳሴ ቤቱ ሲከበር የአርበኞችን አፅም አሰብስበው በታላቅ ሰልፍና በልዩ የጸሎት ሥነ ሥርዓት በተዘጋጀለት ቦታ አስገቡ።

በዚህም ቀን ባደረጉት ንግግር «እጅግ ከፍ ያለው የዓለም ሁሉ ገዥ እግዚአብሔር ለኢትዮጵያና ለሕዝ ባችን፣ ለእኛና ለአርበኞቻችን በየጊዜው ካደረገልንና ወደ ፊትም ከሚያደርግልን የችሮታ ሥራዎች አንደኛውን ዛሬ ስለ ፈጸመልን ልናመሰግነው ይገባናል። ለንጉሠ ነገሥት ቤተ ዘመዳችን የዕረፍት ስፍራ እንዲሆን በመሠረትነው የክ ብር ቦታ በሥራቸውና በመሥዋዕትነታቸው ውለታቸውን ልንመልስላቸው የተገባቸው አገልጋዮች ደንበኛ የርስት ተካፋይ እንዲሆኑ ፈቀድን። የሚገባቸውን ፈጽመው ማረፋቸውን ስንመሰክርላቸው በአፅማቸው ፊት የክብር ሰላምታ እንሰጣለን።» የሚል መሪ ቃል ይገኝበታል።

ካቴድራሉ በሚሰጠው ቀልጣፋና ዘመናዊ አገልግሎት እየተሳበ የሚመጣው ሕዝበ ክርስቲያን ቁጥር በየጊዜው እያደገ በመሄዱ ይህንኑ በአግባቡ ለማስተናገድ እንዲቻል ሦስት ጊዜ እንዲሰፋ ተደርጓል። በመሆኑም አሁን ባለበት ደረጃ የቤተክርስቲያኑ ወለል ስፋት ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ፴፮ ሜትር ሲሆን ከሰሜን ወደ ደቡብ ፳፮ ሜትር፣ ቁመቱም መካከሉ ፴፰ ሜትር ነው።

ይህን ያህል ስፋት ያለው የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በመካከለኛው ክፍል በአጋዕዝተ ዓለም ሥላሴ፣ በስተቀኝ በቅድስት ድንግል ማርያም፣ በስተግራ በቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ የተሰየሙ ሦስት መንበሮች አሉት። በውስጥም በውጭም ባለው ስፋት ምክንያት ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ በዓላት የሚከበሩት፣ ብፁዓን ኤጲስ ቆጶሳት፣ ቅዱሳን ፓትርያርኮች የሚሾሙበት፣ ለታላላቅ የሃይማኖት መሪዎችም አቀባበል የሚደረግበት ካቴድራል ነው።



ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ያሳነፁት፣ አፅማቸው ያረፈበት መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል

## ፪ኛ. ምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም

የዚህ ቤተ ክርስቲያን የአመሠራረት ታሪክ የሚነሣው ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በጠላት ወረራ ዘመን በእንግሊዝ አገር በስደት ከኖሩበት ዘመን ጀምሮ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

ንጉሡ በለንደን ከተማ ሳሉ በኢየሩሳሌም ይገኙ ከነበሩት ከእጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ዘንድ ልከው የመድኃኔዓለምን ጽላት በማስወሰድ አንድ መካነ ጸሎት መሠረቱ። ያችም መካነ ጸሎት በስደት ያለች ኦርቶዶክሳዊት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ተብላ ትጠራ ነበር። በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም ሚያዝያ ፳፯ ቀን ግርማዊነታቸው በድል አድራጊነት ሰንደቅ ዓላማ እያውለበለቡ ወደ ኢትዮጵያ ከመጡ በኋላ በስደት የነበረው የመድኃኔዓለም ታቦት ግርማዊት እቴጌ መነን ከእንግሊዝ አገር ወደ አዲስ አበባ በገቡበት ነሐሴ ፳፫ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ.ም አብሮ አዲስ አበባ ገባ። ከዚያ በኋላ ቤተ ሳይዳ ተብሎ ይጠራ በነበረው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሆስፒታል ግቢ በታነፀው ቤተ ክርስቲያን ምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ተብሎ ሚያዚያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፴፮ ዓ.ም ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ። በዚህ ቤተ ክርስቲያን የሚካሄደው ጸሎት ከለንደን ጀምሮ በአማርኛ የተዘጋጀ ስለ ነበረ የአዲስ አበባ ምእመናንን በብዛት ስቦ ነበር። በዚህም ምክንያት ተገልጋዩ ሕዝብ እየበዛ ስለ ሄደ የተፈሪ መኮንንና የእቴጌ መነን ት/ቤት ተማሪዎችም እሁድ እሁድ ከዚህ ቤተ ክርስቲያን የማይለዩ ስለ ነበር በመጥበቡ አሁን በሚገኝበት ቦታ ላይ በ፲፱፻፵ ዓ.ም ሚያዚያ ፳፯ ቀን በግርማዊነታቸው ሌላ የመሠረት ድንጋይ ተጣለ።

በዚህ ጊዜ ባሰሙት ንግግር «በተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ክበብ ውስጥ ይህን የአዲሱን ቤተ ክርስቲያን መሠረት ስንመሥርት በዚህ ተማሪ ቤት የሚማሩት ክርስቲያናውያን ወጣቶች የኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖታቸውን ሥርዓት እንዲጠቀሙበት አስበን ነው። የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው። ሃይማኖቱን የማያከብር፣ ሃይማኖት የሌለው፣ እርሱም የሚያምነው ደገፉ የሌለው፣ እርሱንም ማንም የማያምነው የሁለት ዓለም ስደተኛ ነው።» በማለት የሃይማኖትን አስፈላጊነት በአፍንአት አስረድተዋል።

አሁን በአገልግሎት ላይ የሚገኘው ምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያንም መሠረቱ በተጣለ በሁለት ዓመቱ ሥራው ተፈጽሞ ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፵፪ ዓ.ም ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ። በመሆኑም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ አገልግሎቱን በስፋት በመስጠት ላይ ይገኛል።

## ፫ኛ. የደብረ ሊባኖስ ገዳም ቤተ ክርስቲያን

በሰሜን ምዕራብ ሸዋ ሰላሌ ሀገረ ስብከት የሚገኘው የደብረ ሊባኖስ ገዳም በ፲፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከኖሩት ከዐፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ የታወቀ ሲሆን ቤተክርስቲያኑን በቀድሞ ጊዜ ዐፄ ይኩኖ አምላክና ዐፄ ይስሐቅ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ዐፄ ዮሐንስና ዐፄ ምኒልክ በጥሩ ሁኔታ አሠርተውት ነበር። ነገር ግን የተሠራበት መሬት አፈሩ የሚሸሽ በመሆኑና ሕንፃው በመሰነጣጠቁ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ይህን ዓይተው በአዲስ ዕቅድ ለመሥራት እንደነገሡ የገቡትን ቃል ኪዳን በመጠበቅ ፈቃደ እግዚአብሔር ሲሞላ አሁን ያለውን መሠረተ–ጽኑ ሕንፃ አሠሩ።

ግርማዊነታቸው የዚህን ሕንፃ መሠረት የጣሉት ግንቦት ፳፬ ቀን ፲፱፻፶፪ ዓ.ም ሲሆን ሥራው በሥራ ሚኒስቴር ተቆጣጣሪነት በሚገባ ተጠናቆ ስላለቀ ኅዳር ፱ ቀን ፲፱፻፶፮ ዓ.ም ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ። የተለያዩ ሥራዎችን ጨምሮ የፈጀው ገንዘብ በዚያን ጊዜው ዋጋ ብር ፩ ሚሊዮን ፭፻፺፫ ሺህ ፩፻፹፭.፴ (አንድ ሚሊየን አምስት መቶ ዘጠና ሦስት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ አምስት ከሰላሳ ሳንቲም) ነበር።

ከዚህም ሌላ ስጦታን በተመለከተ ለዚህ ገዳም

፩ኛ. ግምታቸው ሰባ ሺህ ብር የሆነ የፋርስ ምንጣፎች (ሥጋጃዎች በያይነቱ

፪ኛ. ወርቀዘቦና ሙካሽ ሥራ ልብሰ ተክህኖ ለ7 ልሁካን የሦስት ጊዜ ቅያሬ

፫ኛ. ልዩ ልዩ ንዋየ ቅድሳትን ንጉሠ ነገሥቱ ሰጥተዋል።


## ፬ኛ. አክሱም ጽዮን

አክሱም ጽዮን የኢትዮጵያ ቅድስት ከተማ ናት። የኦሪትም ሆነ የክርስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በዚች ከተማ በኩል ነው። በዚህም ምክንያት ነገሥታት ሁሉ አክብረዋታል። ሕጓንና ሥርዓቷን ጠብቀውላት ኖረዋል። ሲያያዝ በመጣው ታሪክ እንደሚገኘው በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን የመጣችው ቅድስት ታቦተ ጽዮን በጥንቱ ዘመን በአክሱም አቅራቢያ በሚገኝ ቦታ በምኲራበ ኦሪት ነበረች። ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ከገባ በኋላ ግን አብርሃና አጽብሃ የመጀመሪያይቱን ቤተ ክርስቲያን አሳነፁ። ይህች ቤተክርስቲያን ፲፪ የመቅደስ ክፍሎች እንደነበሯት ይነገራል። ከዚያ ወዲህ አክሱም በተደጋጋሚ ፈርሳ በተደጋጋሚ ታንፃለች።

አሁን ያለውን ቤተ ክርስቲያን ያሠሩት ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ናቸው። የመሠረቱን ድንጋይ መስከረም ፲፪ ቀን ፲፱፻፵፮ ዓ.ም አኖሩ። ሥራው በአማረ ሁኔታ በዘመናዊ መልክ እንዲሠራ ስለ ፈለጉ ለዚሁ ሥራ አንድ ሚሊዮን ሦስት መቶ ሺህ ብር ወጪ እንዲደረግለት አዘዙ። ከዚያን ዕለት ጀምሮ የቤተ ክርስቲያኑ ሥራ የሚቃናበትን፣ ፕላኑ የሚዘጋጅበትን ዘዴ ካስጠኑ በኋላ



www.ethiopianorthodox.org



ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ያሳነፁት የርእሰ አድባራት ወገዳማት አክሱም ጽዮን ካቴድራል

ሥራውን በቅርብ የሚከታተል ራሱን የቻለ ኮሚቴ አቋቋሙ። ገንዘቡም በዚህ ኮሚቴ አማካይነት እንዲራባ፣ ፕላኑም እንዲዘጋጅ አደረጉ። የገንዘቡ መራባት የፕላኑ ዝግጅት፣ እንዲሁም በዓይነቱ ልዩ የሆነው የቤተ ክርስቲያኑ ሥራ ብዙ ጊዜ ስለ ወሰደ ሕንፃው ተጠናቆ የተመረቀው ጥር ፳፱ ቀን ፲፱፻፵፯ ዓ.ም ነበር።

በዐፄ ፋሲል የተሠራው የጥንቱ ቤተ ክርስቲያን እስከ አሁንም ለሴቶች የተከለከለ ነው። ግርማዊነታቸው ግን አዲሱ ካቴድራል ለሴቶችም ለወንዶችም መገልገያ እንዲሆን አድርገዋል። ይህም ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እኩል ነው የሚለውን ያረጋገጠ ትክክለኛ ድርጊት ነው። በግርማዊነታቸው መልካም ፈቃድ አዲስ ለተሠራው ካቴድራል ግምቱ ሰማኒያ ሺህ ብር የሆነ ልብሰ ተክህኖና ንዋየ ቅድሳት፣ የተሰጠ ሲሆን ካህናቱም ልዩ ለዩ የማዕረግ ልብሶችን ተሸልመዋል።

በዚህ ዘመናዊ ካቴድራል ሥራ የጥንቱ የአክሱም ታላቅነት ተገልጧል። የቤተ ክርስቲያኑ ስፋት፣ የሥራው ጥብቀት፣ የእቅዱ ማማር፣ የስጦታውም ብዛት ታላቅነቷን የሚያንፀባርቅ ነው። በመሆኑም ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የአክሱምን ገናናነት ያደሱ ገናና ንጉሠ ነገሥት ነበሩ።

## ፫ኛ. ደብረ ሰላም ቅዱስ እስጢፋኖስ

የደብረ ሰላም ቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተው ግርማዊ ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴ አልጋወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን በነበሩበት በ፲፱፻፱ ዓ.ም ነበር። በዚያን ጊዜ ዘመኑ በፈቀደው መልክ ጥሩ ቤተ ክርስቲያን ታንፆ አገልግሎት ላይ ውሎ ሳለ ባልታወቀ ምክንያት በ፲፱፻፴፪ ዓ.ም ተቃጠለ። ይህም በካህናቱና በሕዝቡ ላይ ከፍተኛ ችግር አስከተለ።

ግርማዊነታቸው በድል አድራጊነት ከተመለሱ በኋላ ፩ኛ. የካህናቱንና የምእመናኑን ችግር ለማቃለል ፪ኛ. ድሮውኑ የመሠረቱትና ያቃኑት እንደመሆናቸው ፕላኑ በሥራ ሚኒስቴር ተጠንቶ ዘመናዊ ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራ አዘዙ። ሥራውም በዚሁ ሚኒስቴር ቁጥጥር ተካሄዶና ተጠናቆ ጥቅምት ፲፯ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ። በዚህም ቀን እንዳጋጣሚ ሆኖ የግብጽ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ፮ኛ ተገኝተው የቅዳሴ ቤቱን በዓል አብረው አክብረዋል።

ንጉሠ ነገሥቱ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑን ማሠራት ብቻ ሳይሆን ካህናቱ የሚረዱበትን ሀብት የሚተዳደሩበትንም መብት ሰጥተዋል። ሕንፃው ዘመናዊና ውበት ያለው አገልግሎቱም ቀልጣፋ በመሆኑ እስካሁንም ድረስ ብዙ ምእመናን ወደዚያ ይጐርፋሉ።

## ፬ኛ. ዝቋላ ገዳም

ከታላላቆቹ ጥንታውያን ገዳማት አንዱ የሆነው የዝቋላ ገዳም ቤተ ክርስቲያን በዘመናዊ መልክ እንዲሠራ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በማዘዛቸው ጥናቱና የሥራ ፕላኑ አልቆ በ፲፱፻፶፰ ዓ.ም የመሠረት ድንጋዩን እንዲያስቀምጡ ተደረገ። ሥራውም በሚገባ ተከናውኖ በዚያው ዓመት ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ።



www.ethiopianorthodox.org

## ፯ኛ. ደብረ ኃይለ ቁልቢ ገብርኤል

ይህ ደብር የተመሠረተው በልዑል ራስ መኮንን ሲሆን ገባሬ ተአምራት በመሆኑ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ የውጭ ዜጎችም በብዛት እየተገኙ በዓሉን በሚገባ ሲያከብሩ፣ ከተአምራቱም ሲሳተፉ ይታያሉ። ግርማዊ ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ተገልጋዩ ሕዝብ በየዓመቱ እየጨመረ ከመሄዱ አንፃር የቤተ ክርስቲያኑን ጥበት አይተው ሰፊ ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራ አዘዙ። በትእዛዙም መሠረት ፕላን ተሠርቶ ፳፪ (ሕዝብ ሊይዝ በሚችል ሁኔታ በ፲፱፻፶፯ ዓ.ም በ፬ መቶ ፳፫ ሺህ ብር ተሠራ። በአካባቢው ተወዳዳሪ የሌለው ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ነው።

## ፰ኛ. በተለያዩ ክፍላተ ሀገር ያሳነጿቸው አብያተ ክርስቲያናት

### ሀ. በአዲስ አበባ

ቀደም ሲል ከጠቀስናቸው ሌላ ግርማዊ ጃንሆይ በአዲስ አበባና በዙሪያዋ ያሠሯቸው።

- የመናገሻ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን (አሁን ምዕራብ ሸዋ)
- የጉለሌ ቅዱስ ሚካኤል (ደብረመዊዕ) ቤተ ክርስቲያን
- የቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ቤተ ክርስቲያን
- ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚጸልዩበት መንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ናቸው።

### ለ. በሸዋ ሀገረ ስብከት

- ዜና ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን
- የናዝሬት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን (አሁን ምሥራቅ ሸዋ)
- የደብረ ዘይት ቅዱስ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን (አሁን ምሥራቅ ሸዋ)
- የአምቦ ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን (አሁን ምዕራብ ሸዋ)

### ሐ. በወሎ ሀገረ ስብከት

- ደብረ ቤቴል ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን
- አሰብ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን

### መ. በትግራይ ሀገረ ስብከት

- ደብር ዓባይ አባ ሣሙኤል ቤተ ክርስቲያን

### ሠ. በበጌምድርና ሰሜን ሀገረ ስብከት

- መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም
- አደባባይ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም
- ዋልድባ (ዳልሻህ) ቤተ ክርስቲያን በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም
- ማኅበረ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም
- ሰይኮ ኪዳነምሕረት ቤተ ክርስቲያን በ፲፱፻፶፯ ዓ.ም



ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ያሳነፁት የታላቁ ገዳም የደብረ ሊባኖስ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን



www.ethiopianorthodox.org

- አብረንታንት አባ ሳሙኤል ቤተ ክርስቲያን በ፲፱፻፶፰ ዓ.ም
- ሰቋር ኪዳነምሕረት ቤተ ክርስቲያን

## ረ. ቀድሞ የኢትዮጵያ ክፍል በነበረችው በኤርትራ

- ምጽዋ ደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤተ ክርስቲያን
- አሥመራ ተክለሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን
- አሥመራ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን
- መንደፈራ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን

## ሰ. በወለጋ ሀገረ ስብከት

- ለቀምት ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በ፲፱፻፶፰ ዓ.ም
- አሶሳ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም
- ደምቢ ዶሎ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን በ፲፱፻፷፱ ዓ.ም

## ሸ. በሐረርጌ ሀገረ ስብከት

- ሐረር አደሬ ጢቆ መካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን
- ኤጀርሳ ጓሮ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን
- ዓለማያ ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን
- ሐረር ጥምቀተ ባሕር ተክለሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን

ከእነዚህም ጋር ሙሉ እድሳት ያስደረጉላቸው በቆርቆሮ ያስከደኗቸው፣ ደብር ያደረጓቸው፣ የገደሟቸው አብያተ ክርስቲያናት በጣም ብዙ ናቸው።

«ሕንፃ ወውሉድ የዐብዩ ስመ» (ሲራክ ፵፬÷፲፱) ሕንፃና ልጅ ስምን ሲያስጠሩ ይኖራሉ እንደተባለው ከልጆቻቸው ባላነሰ ሁኔታ እነዚህና ሌሎችም ያልተጠቀሱ ዐበይት ሥራዎቻቸው የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴን ሲያስጠሩት ይኖራሉ። ✣

# መ. ቅዱሳት መጻሕፍትን በማሳተም

ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዕድገት ካደረጉት አያሌ ጥረት አንዱ ቅዱሳት መጻሕፍት:-

ሀ. በቁም ጽሕፈት በብራና እየተጻፉ፣

ለ. ማተሚያ ቤት በማቋቋም ቅዱሳት መጻሕፍት በግእዝና በአማርኛ እየታተሙ እንዲቀርቡ ያደረጉት ታላቅ ተግባር ነው።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅድመ ክርስትና የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ድኅረ ክርስትናም የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲሁም የገድላተ ቅዱሳንና የድርሳናት ባለቤት መሆንዋ የሚታወቅ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍቱ በመጀመሪያ ከየተጻፉበት ቋንቋ የተተረጎሙትና የተጻፉት በጊዜው የሕዝቡ ሁሉ መግባቢያና ብሔራዊ ቋንቋ በነበረው በግእዝ ነበር።

ከጊዜ በኋላ ግን የአማርኛ ቋንቋ እያደገ በመምጣ የሕዝቡ መግባቢያና ብሔራዊ ቋንቋ በመሆኑ ግእዝ በቤተ ክርስቲያን በሊቃውንት ዘንድ ብቻ እንጂ በሕዝቡ ዘንድ የማይታወቅ ሆነ። በዚህም ምክንያት ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ገና አልጋ ወራሽ ከነበሩበት ጊዜ አንሥተው ለዚህ ለቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም ጽሕፈትና ኅትመት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ከንጉሠ ነገሥት ሥራቸው ጋር አመራር እየሰጡ ቅዱሳት መጻሕፍት ከግእዝ ወደ አማርኛና ልዩ ልዩ ቋንቋዎች እንዲተረጎሙና እንዲጻፉ እንዲታተሙም አድርገዋል።

ይኸውም በመጀመሪያ በ፲፱፻፲ ዓ.ም በቤተ መንግሥታቸው የመጻሕፍት ማደራጃ ክፍል አቋቋሙ። በዚህ ክፍል:-

ሀ. ቀለም የሚያሹ

ለ. ብራና የሚያወጡ

ሐ. የቁም ጽሕፈት

መ. የሐረግና የሥዕል ባለሙያዎች

ሠ. ከግዕዝ ወደ አማርኛ የሚተረጉሙ የትርጓሜ ሊቃውንትን አሰባስበው ቅዱሳት መጻሕፍት በብራና በግእዝና በአማርኛ እየተጻፉ ለየገዳማቱና ለየአድባራቱ እንዲሰጡ በቤተ መዘክርም እንዲገኙ አድርገዋል።

በዚህም ታላቅና መንፈሳዊ ተግባራቸው ታላቁን ክርስቲያን ንጉሥ ቆስጠንጢኖስን መስለውታል። ቆስጠንጢኖስ የማተሚያ መሣሪያ ባልተሠራበት ጊዜ የነበረ በመሆኑ ቅዱስ ወንጌል ለአብያተ ክርስቲያናት እንዲዳረስ በአደረገው የአሠራር ስልት ሃምሳ ያህል አርባዕቱ ወንጌል እየተጻፈ ለአብያተ ክርስቲያናት እንዲዳረስ አድርጎ ነበር። (አውሳብዩስ)

ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴም በአንድ በኩል መጻሕፍት ከግእዝ ወደ አማርኛ እየተተረጎሙ በብዛት እንዲጻፉና የግእዝ ቋንቋ የማያውቁ ኢትዮጵያውያን በአማርኛ ለማንበብ እንዲችሉ አብያተ ክርስቲያናትም በግእዝና በአማርኛ በተጻፉ መጻሕፍት እንዲገለገሉ በሌላ በኩልም የቀለም ማሸት፣ የብራና ማውጣት፣ የቁም



www.ethiopianorthodox.org

ጽሕፈት፣ የሐረግና የሥዕል ሙያ እንዲጠናከር ያደረጉት ታሪካዊ ጥረት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሲጠቀስ የሚኖርና የማይዘነጋ ነው። በአንድ አንድ ጥንታውያን ታላላቅ አድባራትና ገዳማት ካልሆነ በቀር በየአድባራቱና ገዳማቱ የማይገኙ መጻሕፍት በመጀመሪያ ከያሉበት እየተፈለጉ በግእዝ ተጽፈው እንዲገኙ አድርገዋል።

በዚህ ጊዜ ከየገዳማቱ እየተጻፉ ከመጡት መጻሕፍት ለአብነት ያህል መጥቀስ ቢያስፈልግ፣

ለዕለታዊ መፍቀድ የሚያስፈልጋቸው ሠርክ ኅብስት ሁሉ ዘወትር ከቤተ መንግሥት እንዲሰጣቸው በማድረግ ግርማዊነታቸው እየተንከባከቡ ያሠሩዋቸው እንደነበር ይታወቃል።

የትርጕሙም ስልት ሁለት ዓይነት ነበር። ይኸውም:-

፩ኛ. ነጠላ ትርጉም፣

፪ኛ. አንድምታ ትርጉም ነው።



ግርማዊነታቸው ወንጌለ ዘወርቅ ሲሳለሙ

ሀ. «መጽሐፈ ሐዊ» ከጣና ደሴት

ለ. «መጽሐፈ ዲድስቅልያ» ከደብረ ሊባኖስ ተጽፈው መጥተዋል።

ከዚያ በፊት የተጻፉትንና በዚያም ጊዜ በግእዝ የሚጻፉትን መጻሕፍት የሚያውቁና የሚያነብቡ ሊቃውንት ካህናት ብቻ መሆናቸውን በማስተዋል በዚያ የመጻሕፍት ማደራጃ ክፍል ውስጥ የመጻሕፍት ንባብና ትርጉም ክፍል ነበር፤ በዚህ ክፍል የቅዱሳት መጻሕፍትን ንባብ ትርጉምና ምሥጢር ጠንቅቀው የሚያውቁ ፲፰ ያህል ሊቃውንት ነበሩበት።

በነዚህ ሊቃውንት ንባባቸውና ትርጉማቸው በሚገባ እየተዘጋጀ የሚቀርቡትን መጻሕፍት በቁም ጽሕፈት የሚጽፉ ደግሞ ከአሥር በላይ ቁም ጸሓፊዎች ነበሩ። በዚህ ከፍተኛ የአእምሮ ሥራ የተጠመዱ ሊቃውንት ለሥራቸው መቃናት እንዲረዳቸው በኑሮአቸው ተገቢ ድጋፍና ጥንቃቄ ይደረግላቸው ነበር። ከወርኃዊ ደመወዛቸው በላይ

በዚህ ሁኔታ እየተዘጋጁ ከተጻፉ በኋላ ቅድሚያ እየተሰጣቸው መታተም የሚገባቸው መጻሕፍት በቅደም ተከተል ታትመዋል። ሌሎች ደግሞ በግእዝና በአማርኛ በብራና እየተጻፉ ሐረግ እየተጣለባቸው ሥዕል እየተሣለባቸው፣ እየተጠረዙ፣ እየታፈፉና እየተደጐሱ በታላላቅ ገዳማትና አድባራት አገልግሎት እንዲሰጡና በቤተ መጻሕፍት ወመዘክርም እንዲቀመጡ የተደረጉ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት እንዲሁም ልዩ ልዩ ገድለ ቅዱሳን የቁጥርና የታሪክ መጻሕፍት እጅግ ብዙዎች ናቸው።

ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በዚህ ሁኔታ ሊቃውንቱን ከአሰባሰቡና ከአቀራረቡ በኋላ እርስ በርሳቸው እንዲተዋወቁ ከአደረጉና የቁም ጽሕፈቱንና የትርጕሙን ሥራ ከአጠናከሩ በኋላ የኅትመት መኪና በገንዘባቸው በመግዛትና ማተሚያ ቤት በማቋቋም ቅዱሳት መጻሕፍትን የማሳተም ሥራን ጀመሩ።



www.ethiopianorthodox.org

በመጀመሪያ በሙሉ ንባብና በአንድምታ ትርጓሜ የታተሙ መጻሕፍት፣

- የዮሐንስ አፈወርቅ ድርሳንና ተግሣጽ
- አምስቱ መጻሕፍተ ሰሎሞን
- መጽሐፈ ሲራክ
- አርባዕቱ ወንጌል
- ኪዳንና ትምህርተ ኅቡዓት
- አሥራ አራቱ መጽሐፍተ ቅዳሴ
- ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም
- አረጋዊ መንፈሳዊ
- ፊልክስዩስ
- ማር ይስሐቅ፣ ሲሆኑ በነጠላ ትርጉም የታተሙ መጻሕፍት ደግሞ
- መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ
- አሥራ አራቱ መጻሕፍተ ቅዳሴ
- የተለያዩ የጸሎት መጻሕፍት
- ዳዊት
- ፍትሐ ነገሥት
- ተአምረ ማርያምና የመሳሰሉ ናቸው።

ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉም በግእዝና በአማርኛ ተጽፈው መገኘት ያለባቸው መሆኑን በማሰብ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምትቀበላቸውን የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ያካተተ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በነጠላ ትርጉም በቁም ጽሕፈት እንዲጻፉ አደረጉ። ይኸው ሥራ በ፲፱፻፳፩ ዓ.ም ተጀምሮ በ፲፱፻፳፯ ዓ.ም ሊጠናቀቅ ችሏል። የነጠና ትርጒሙና የቁም ጽሕፈቱ ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ ለኅትመት ሳይቀርብ የኢጣሊያ ፋሽስት ሀገራችንን ስለ ወረራት የኅትመቱ ሥራ ለጊዜው ዘግይቶ ነበር።

በኋላ ግን ግርማዊነታቸው በስደት እንዳሉ ዝግጅቱ በሙሉ ስለ ደረሳቸው «ባክስተን» በተባለ የክርስቲያን ማኅበር አማካይነት በእንግሊዝ ሀገር በፎቶ አፍሴት እንዲታተም አድርገውት ታትሟል። ወደ ኢትዮጵያም ገብቶ በየአድባራቱና ገዳማቱ እንዲሁም በግለሰቦች እጅ ሁሉ ይገኛል።

ግርማዊ ጃንሆይ በድል አድራጊነት ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ በኋላ ቀደም ሲል የተጀመረው የቅዱሳት መጻሕፍት ኅትመት እንዲቀጥል ይልቁንም ከግእዝ ወደ አማርኛ ያስተረጎሙት የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከእናቱ ከእብራይስጥና ከግሪኩ መጻሕፍት (ቴክስት) አንዳንድ የቃል ልዩነት አለ ስለ ተባለ የልዩነቱ ሁኔታ እንዲጣራና በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አማርኛ እንዲስተካከል በየካቲት ፲፱፻፴፱ ዓ.ም አንድ የሊቃውንት ጉባኤ አቋቋሙ። በዚህም ጉባኤ ፯ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ፫ የውጭ ሀገር ሊቃውንት ይገኙበት ነበር። ይህ ዝግጅት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምትቀበላቸውን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ያካተተ ሲሆን በ፲፱፻፵፯ ዓ.ም በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታትሞ ወጥቶ በሥራ ላይ ውሏል።



ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ቅዱሳት መጻሕፍትን ሲመለከቱ



www.ethiopianorthodox.org

የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የቅዱሳት መጻሕፍት ኅትመት ሥራ እጅግ ተጠናክሮ የታየበትና የቤተ ክርስቲያናችን የትርጓሜና የዜማ ትምህርት መጻሕፍት በብዛት የታተሙበት፣ የሊቃውንቱም የመማርና የማስተማር የሥራ ክብደት የተቃለለበት ነው።

ይህም ሊሆን የቻለው ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ከሊቃውንቱ ጋር የኖሩ የጉባኤን ጣዕም ያወቁ በመሆናቸውና ቤተ ክርስቲያንም ብዙ ምሥጢር እንዳላት ሊቃውንትም በአእምሮአቸውና በየጉባኤ ቤታቸው የተደበቀ ብዙ ዕውቀት እንዳላቸው በመረዳታቸው ይኸው ተጠብቆ የኖረ መንፈሳዊ ዕውቀት ለዓለም እንዲዳረስና በሀገራችንም በብዛት እንዲታወቅ ለማድረግ አስበው ነው።

ሊቃውንቱ በየደረጃቸው በትርጉምና በቁም ጽሕፈት ለመሥራት በአንድ ላይ መሰባሰባቸው እርስ በርሳቸው እንዲተዋወቁ ዕውቀትም እንዲለዋወጡ ምሥጢራት መጻሕፍትንም በስፋት እንዲገልጡ ረድቷል።

ይህ የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የቁም ጽሕፈት ሥራን የማቋቋምና የቅዱሳት መጻሕፍት ኅትመትን የማፋጠን ሒደት ጥንታዊ ቅርስን ለማበርከትና ጠብቆ ለማቆየት እጅግ ረድቷል።

ይኸውም:-

ሀ. የቁም ጽሕፈት ሥራ በራሱ የመንፈሳዊ ተግባረ እድ ቅርስ ስለሆነ

- የቀለም ማሽት
- የብራና ማውጣት
- ብራና ደምፆ ብርዕ ቀርጾ የመጻፍ
- የጥራዝ፣ የድጉስና የቶታን ማስገባት ሥራዎች እንዳይረሱና እንዳይጠፉ እየተሠራባቸው እንዲስፋፉና በቅርስነትም እየተጠበቁ እንዲቆዩ አድርጓል።

ለ. ቀደም ሲል ተጽፈው በአንዳንድ ታላላቅ ገዳማትና አድባራት ካልሆነ በቀር በሁሉም የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የማይገኙ መጻሕፍት ከሚገኙበት እየተፈለጉና እየተጻፉ በአብያተ ክርስቲያናትና በቤተ መዘክር እንዲገኙ በመደረጉ ቀደም ያሉት በቅርስነት እንዲጠበቁ አዳዲሶቹ አገልግሎት እንዲሰጥባቸውና እየቆዩም በቅርስነት እንዲጠበቁ ሁነዋል።

ሐ. የቅዱሳት መጻሕፍት ኅትመትም ለቅርስ አጠባበቅ የሚያበረክተው ድርሻ ከፍተኛ ነው። ይኸውም ቅዱሳት መጻሕፍት በግእዝና በአማርኛ እየታተሙ ሲወጡ አብያተ ክርስቲያናት አነዚህን የታተሙ መጻሕፍት በቀላሉ እያገኙ በመገልገል የነበሩዋቸውን የብራና መጻሕፍት በቅርስነት ጠብቆ ለማቆየት በከፍተኛ ሁኔታ ጠቅሟል።

ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማስተርጐም፣ በማጻፍና በማሳተም ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና ለኢትዮጵያ ያበረከቱት የዕውቀት ሀብት አንድ በአንድ በዝርዝር ይቅረብ ቢባል በዚህ አነስተኛ ዐምድ የሚጠቃለል አይሆንም። ዋና ዋናውን በማስታወስ ብቻ ከላይ የተገለፁት ሥራዎች ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ተልእኮ መሟላት፣ ለኢትዮጵያውያን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ዕድገት ምን ያህል ይጥሩ እንደ ነበር ያስረዳሉ። ሥራዎች ቋሚ ምስክሮች ናቸው። ሥራ ሠሪውን የገልጻል፤ ሠሪም በሥራ ይታወቃል።

ስለዚህ ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት ጠባቂ ለኢትዮጵያውያን የመንፈሳዊ ትምህርት፣ ዕውቀትና ሥልጣኔ ብርሃን መሆናቸውን ሥራው ራሱ የመሰክራል። ትውልድም ይህን ሊያውቀውና ሊረዳው ይገባል። ይህ የቅዱሳት መጻሕፍትን የትርጉም፣ የቁም ጽሕፈትና የኅትመት ሥራን አጠናክሮ ቅዱሳት መጻሕፍትን የማበርከት ጉዳይ ግርማዊነታቸው ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሁለንተናዊ ዕድገት ካደረጓቸው በርካታ ዐበይት ተግባራት አንዱ ክፍል መሆኑ ግልፅ ነው።

ይሁን እንጂ ለሥጋዊና ለመንፈሳዊ ሕይወት መርሕ፣ ለሰላምና ለአንድነት፣ የሰዎችን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ሕይወት በትምህርት ለማስተካከልና ሁሉን በቀና መንገድ ለመምራት የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት መሠረት ነው። በመሆኑም ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ መጻሕፍትን በማስተርጐም፣ በማጻፍና በማሳተም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲሟላ፣ የኢትዮጵያውያን ሁሉ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ሕይወት በትምህርት እንዲታደስ ያደረጉ ስለሆነ በዚህ በኩል ያደረጉት ጥረት ለሌላው ሁሉ መሠረት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ስለሆነም ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና ለኢትዮጵያውያን እጅግ ባለውለታ ናቸው፤ ታሪካቸው በሥራቸው ሥራቸውም በታሪካቸው ሲታወስ የኖራል። ከአስተረጎሟቸው፣ ከአጻፏቸውና ከአሳተሟቸው መጻሕፍት ትምህርት ጋር ስማቸውና ታሪካቸው ሲጠቀስና ሲታወስ ይኖራል። በሕይወታቸው የታመኑበትና ለስሙ መመስገኛ የሚሆኑ ዐበይት ተግባራትን ስሙን እየጠሩ ያከናወኑለት እግዚአብሔር በስሙ አምነው መልካምና ደግ ሥራ የሚሠሩ ሁሉ ሥራቸው ከስማቸው፣ ስማቸውም ከሥራቸው ሳይለይ ሲታሰብና ሲጠቀስ እንዲኖር ለሚያስተውለውም ትምህርት እንዲሆን ፈቃዱ ነውና።፨



www.ethiopianorthodox.org

# ሠ. መንፈሳዊ ትምህርትንና ትምህርት ቤቶችን በማስፋፋት

በኢትዮጵያ ትምህርት በከፍተኛ ደረጃ ከተስፋፋባቸውና ዕድገት ካገኘባቸው ዘመናት በቀዳሚነት ሊጠቀስ የሚገባው የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ነው። በሠለጠኑ ሀገሮች እንደተረጋገጠው በኢትዮጵያም ሕዝቡን ከድንቁርና፣ ከበሽታና ከድህነት ለማላቀቅ ትምህርት ፍቱን መድኃኒት መሆኑን በማጤን፣ እንዲሁም ሰው የሥጋም የነፍስም ውሑድ እንደመሆኑ መጠን ከሥጋዊ ትምህርት ጋር መንፈሳዊ ትምህርትም የሚያስፈልገው መሆኑን በመገንዘብ፣ ይልቁንም መንፈሳዊ ትምህርት በኢትዮጵያ የረጅም ዘመን ታሪክ ያለው መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ግርማዊ ጃንሆይ በዘመነ መንግሥታቸው ሥጋዊ ትምህርት ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ትምህርትም በከፍተኛ ደረጃ እንዲስፋፋና እንዲያድግ የላቀ ጥረት አድርገዋል። ከልጅነታቸው ጀምሮ ከመንፈሳዊውም ከሥጋዊውም ትምህርት እየቀሰሙ ያደጉ ስለሆኑ ለሁለቱም የትምህርት ዘርፍ ዕድገት ሳይታክቱ ይሠሩ እንደነበረ ታሪካቸው ይመሰክራል።

ለመግለጽ ስለሆነ በዚህ ረገድ ከፈጸሟቸው አያሌ ተግባራት ዋና ዋናዎቹ ከዚህ ቀጥሎ ተጠቅሰዋል።

በመጀመሪያ ደረጃ ግርማዊ ጃንሆይ ገና በአልጋ ወራሽነታቸው ጊዜ የደብር አለቆች በየደብሩ፣ የገዳማት መምህራንም በየገዳማቸው እንዲያስተምሩ አዋጅ አውጥተዋል። በዚህም አዋጅ መሠረት በየገዳማቱና በየአድባራቱ የሚሰጠው መንፈሳዊ ትምህርት እየተስፋፋና እየተጠናከረ መሄድ ጀመረ።

በሁለተኛ ደረጃ ቤተክርስቲያንን በአግባቡ ለማስተዳደር ትምህርቱንም በተፈለገው መጠን ለማስፋፋት ቋሚ በጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ሚያዝያ ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ.ም ስለቤተክርስቲያን በወጣው ደንብ አንቀጽ ፪ እና ፫ በልዩ ልዩ ምክንያት ለቤተ ክርስቲያን ከተሰጠ ርስት ጉልት የሚገኘው ግብር እየተሰበሰበ ለቤተ ክርስቲያንና ለመንፈሳዊ ትምህርት ማስፋፊያ እንዲውል ፈቅደዋል።

በሦስተኛ ደረጃ መንፈሳዊ ጉባኤ (አሁን ቤተ ክህነት) በቀረበው ጥያቄ መሠረት ለቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ እንዲሆን ከተፈቀደው መሬት ከጎጃምና ከጎንደር በስተቀር ከሌሎች ጠቅላይ ግዛቶች የሚሰበሰበው የትምህርት ታክስ ለመንፈሳዊ ትምህርት ማስፋፊያ እንዲውል ግንቦት ፳፫



ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ለመንፈሳውያን ደቀመዛሙርት ሺልማት ሲሰጡ

ይ
ሁንና የዚህ ጽሑፍ ትኵረት ስለዘመናዊ ትምህርት ለማውሳት ሳይሆን ግርማዊነታቸው ስለመንፈሳዊ ትምህርት መስፋፋት ያደረጉትን ጥረት በመጠኑም ቢሆን

ቀን ፲፱፻፵፩ ዓ.ም በቁጥር ፪ ሺህ ፪፻፰/፰ በተጻፈ ደብዳቤ ለገንዘብ ሚኒስቴር ትእዛዝ ሰጥተዋል። ከዚህ ገቢ ከመቶ ሃያው እጅ (፳%) እየተነሣ ለብቻው ተቀምጦ



www.ethiopianorthodox.org

ግርማዊነታቸው ለመንፈሳዊ ጉዳይ የሚያዙበት እንዲሆን ተደርጓል።

በአራተኛ ደረጃ የትምህርት ታክስ በቀጥታ ለመንግሥት በሚከፍሉት በጎጃምና በጎንደር ለሚገኙ የታላላቅ አድባራትና ገዳማት የዜማ፣ የቅኔና የትርጓሜ መጻሕፍት መምህራን ከትምህርት ሚኒስቴር በጀት፣ ደመወዝ እንዲከፈላቸው አድርገው ነበር። ይሁንና በደርግ ዘመን መምህራኑ ጡረታ ሲወጡ ደመወዙ ለተተኪ መምህራን እንዳይሰጥ ስለተከለከለ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ተቋርጧል።

በአምስተኛ ደረጃ ለመንፈሳዊ ትምህርት ዕድገት ባላቸው ጽኑ ፍላጎት እንደዘመናዊ ትምህርት ደረጃ አግኝቶ፣ ከንባብ ቤት እስከ ትርጓሜ መጻሕፍት ድረስ ደረጃ በሰባት ክፍል ተከፍሎ እንዲሰጥ አድርገዋል።

ይኸውም ደረጃ

፩ኛ. የንባብና የጽሕፈት ት/ቤት

፪ኛ. የዜማ ት/ቤት

፫ኛ. የቅኔ ት/ቤት

፬ኛ. የብሉያት መጻሕፍት ትርጓሜ ት/ቤት

፭ኛ. የሐዲሳት መጻሕፍት ትርጓሜ ት/ቤት

፮ኛ. የሊቃውንት መጻሕፍት ትርጓሜ ት/ቤት

፯ኛ. የመጽሐፈ መነኮሳት ትርጓሜ ት/ቤት ነው።

በስድስተኛ ደረጃ በዘመናዊ ትምህርት ለምስጉናን መምህራንና በፈተና ከ፩ኛ እስከ ፫ኛ ለወጡ ተማሪዎች የማበረታቻ ሽልማት ይሰጡ እንደ ነበረ ሁሉ ለመንፈሳዊ ትምህርት መምህራንና ተማሪዎችም በየጊዜው ሽልማት እየሰጠ ትምህርቱ እንዲስፋፋ ያበረታቱ ነበር። ለአብነት ያህል ብንጠቅስ መዘክረ ምግባር መንፈሳዊ በተባለው መጽሐፍ በገጽ ፪፻፫ ላይ እንደተገለጸው ሰኔ ፱ ቀን ፲፱፻፵፩ ዓ.ም የቅዱስ ጳውሎስንና የፈለገ ሕይወት ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ በአዲስ አበባ ገዳማትና አድባራት ለሚገኙ የዜማ፣ የቅኔና የአራቱ ጉባኤያት መምህራን የወርቅ ሜዳልያ፣ ለንባብ መምህራን የብር ሜዳልያ ሲሸለሙ በፈተና ከ፩ኛ እስከ ፫ኛ ለወጡ ደቀመዛሙርትም ተገቢውን ሽልማት ሰጥተዋል። በዚህ ቀን ሽልማቱን ከሰጡ በኋላ ባደረጉት ንግግር:-

«መንፈሳዊ ትምህርት ባገራችን ከብዙ ዘመን ጀምሮ የኖረ ነው እንጂ አዲስ ነገር አይደለም። ይህ ትምህርት የሁለት ዓለም ጥቅም የሚገኝበት የማይናወጽ የድንጋይ መሠረት ስለሆነ ለዓለማዊው ትምህርትና ሥራ ሁሉ መሠረት እንዲሆን አጥብቀን የምናስብበት ነው» ብለዋል።

በሰባተኛ ደረጃ በሃምሳዎቹ መጨረሻና በስልሳዎቹ መጀመሪያ ዓመታት የላቀ ዕውቀት የነበራቸው የመንፈሳዊ ትምህርት ሊቃውንት ላበረከቱት አገልግሎትና ለነበራቸው ጥልቅ ዕውቀት የከፍተኛ ደረጃ ሽልማት እንዲያገኙ አድርገዋል። በዚህ ረገድ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ያገኙት ታዋቂው የአራቱ ጉባኤያት መምህር አለቃ አየለ ዓለሙ፣ በግርማዊነታቸው የሽልማት ድርጅት ቦርድ ተመርጠው ከፍ ያለ ሽልማት ያገኙት የቅኔው ሊቅ አለቃ ጠበቡ ገሜና የድጓውና የአቋቋሙ መምህር ሊቀጠበብት አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ ሊጠቀሱ የሚገባቸው ናቸው።

በስምንተኛ ደረጃ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ለመንፈሳዊ ትምህርት ካላቸው ፍቅርና ለመምህራኑም ከነበራቸው አክብሮት የተነሣ እንደ እነ ጌታ አለቃ ኀሩይ ያሉትን ሊቃውንት በቤተ መንግሥታቸው በማስቀመጥ ጉባኤ እንዲያስሙ ያደርጉ ነበር።

በዘጠነኛ ደረጃ ዘመናዊ ትምህርት እየተስፋፋ ሲሄድ ወጣቱ ትውልድ የግብረ ገብነት ትምህርት የሚያስፈልገው መሆኑን በማጤን በመንፈሳዊ ት/ቤቶች የሠለጠኑ የግብረ ገብ መምህራን በየት/ቤቱ እየተመደቡ እንዲያስተምሩ አድርገዋል።

በአሥረኛ ደረጃ ሥልጣነ ክህነት ያላቸው መነኮሳትና ቀሳውስት በሆስፒታሎች፣ በወታደራዊ ክፍሎች፣ በምድር ጦር፣ በአየር ኃይል፣ በባሕር ኃይል፣ በወኅኒ ቤቶች እየተመደቡ የትምህርተ አበ ነፍስ አገልግሎት እንዲሰጡ በመደረጉ በአጠቃላይ በግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ መንፈሳዊና ሥጋዊ ሕይወት በተመዛዘነ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነበር።

በሌላ በኩልም ግርማዊነታቸው ከድል በኋላ ለመንፈሳዊ ትምህርት ዕድገት ያበረከቱት ድርሻ እጅግ ጎልቶ የሚታየው ዓለማዊውና መንፈሳዊው ትምህርት በአንድነት ተቀናጅቶ እንዲካሄድ በማቀድ ባቋቋሟቸው ት/ቤቶች ውጤት ነው። ከእነዚህም መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

## ፩ኛ. የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ


ይህ ከፍተኛ የትምህርት ማዕከል አሁን ወዳለበት ቦታ ከመዛወሩና ደረጃውም ወደኮሌጅነት ከፍ ከማለቱ በፊት ትምህርት የጀመረው በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ውስጥ



www.ethiopianorthodox.org

ነበር። ግርማዊነታቸው በድል አድራጊነት እንደተመለሱ ዕውቀት በበለጠ እንዲስፋፋ በተለይም ካህናት በሕዝቡ ዘንድ ተሰሚነት ስላላቸው እነርሱ ዕውቀታቸውን ቢያሻሽሉ ለሕዝብ የተሻለ አገልግሎት ይሰጣሉ ብለው በማሰብ ት/ቤት እስኪዘጋጅ ድረስ ቤተ መንግሥታቸውን ት/ቤት አድርገው በቶሎ ደርሰው አገርንና ቤተ ክርስቲያንን በበለጠ ያገለግላሉ ተብለው የተገመቱትን ሊቃውንት ሰብስበው፣ መምህር መድበው የእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲማሩ አድርገዋል። በዚህ ወቅት ከተናገሩት ቃል ጥቂት ብንጠቅስ:-

ት/ቤት በመክፈት በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት የተጀመረው ትምህርት እንዲቀጥል አደረጉ። በዚያን ጊዜ ትምህርት ቤቱ በሁለት የተከፈለ ነበር። አንደኛው የቀሳውስት ክፍል ሲሆን አስቀድመው ለቀሰሱና ከፍተኛ የሆነ ትምህርት ለሚፈልጉ የተከፈተ የሦስት ዓመት ጥናት የሚደረግበት ነበር። ሁለተኛው የዲያቆናት ክፍል ሲሆን ከአሁኑ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ጋር በመመሳሰል ስምንት ዓመት የሚፈጅ ነበር። በተጨማሪም እንደ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ዶግማ፣ ቴዎሎጂ፣ ዜና አበውና ዜማም እንዲማሩ ይደረግ ነበር። ይህ ት/ቤት በ፲፱፻፵፭ ዓ.ም ወደ ሁለተኛ



ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ያሳነፁት የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ

«...ዛሬ የምትሠሩባቸውን መጻሕፍት አባቶቻችን የውጭ አገር ቋንቋ ተምረው ወደ ቋንቋችን መልሰው ባይተረጉሙልን ኑሮ በአሁኑ ጊዜ አሕዛብ ተብለን መጠራት ያገኘን ነበር። እናንተንማ በደጃችሁ እያላችሁ ሳትማሩት መቆየታችሁ የሚያፀፀት ነው። ...እኛ እንድትማሩ የፈለግነው በቤተ መንግሥት ሥር የቋንቋ ትምህርት ሲስፋፋ ቤተክርስቲያን በዚህ በኩል የሚሚደግፋት እንዳታጣ በማሰብ ነው።» ብለዋል። የቋንቋውን ትምህርት ጀምረው እስከ መጨረሻው ከተከታተሉት ሊቃውንት መካከል መምህር መልእክቱ በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎጵሎስ የተባሉት የኢትዮጵያ ሁለተኛ ፓትርያርክ ነበሩበት።

ከተወሰነ ጊዜ በኋላም በጀት ፈቅደው የውስጥና የውጭ አገር መምህራን እንዲቀጠሩ አድርገው አሁን መንፈሳዊ ኮሌጅ እየተባለ የሚጠራውን የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ

ደረጃ፣ በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም ወደ ኮሌጅ ደረጃ በማደግና በዚሁም ዓመት የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ አካል በመሆን ከተመሠረተበት ከ፲፱፻፷፭ ዓ.ም እስከ ፲፱፻፷፯ ዓ.ም ድረስ በቆየባቸው ጊዜያት በርካታ የሁለተኛ ደረጃ፣ የመምህራን ማሠልጠኛና የኮሌጅ ምሩቃንን ካፈራ በኋላ በደርግ ተወርሶ መንፈሳዊ ትምህርት እንዳይሰጥበት ተደርጎ ነበር። ይሁን እንጂ ከደርግ ውድቀት በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት ቤተ ክርስቲያኒቱን የመምራት ኃላፊነት ከተቀበሉ በኋላ በቅዱስ ሲኖዶስ በማስወሰን ባደረጉት ብርቱ ጥረት በወቅቱ የነበረው የሽግግር መንግሥት ኮሌጁ ለሕጋዊ ባለቤቱ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እንዲመለስ ስለፈቀደ ከ፲፱፻፹፮ ዓ.ም ጀምሮ እንደገና ተከፍቶና የቀድሞው የትምህርት ፕሮግራሙ [illegible]



www.ethiopianorthodox.org

ደቀመዛሙርትን በዲፕሎማና በዲግሪ እያስመረቀ ወጣት ምሁራንን በማበርከት ላይ ይገኛል። በመሆኑም ግርማዊ ጃንሆይ ለዚህ ኮሌጅ የነደፉት ዓላማ እንደገና ተግባራዊ መሆን ጀምሯል።

## ፪ኛ. ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት

ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የቅድስት ሥላሴን መንፈሳዊ ት/ቤት እንደከፈቱ ሁሉ ግርማዊት እቴጌ መነንም የሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስን ት/ቤት በ፲፱፻፴፰ ዓ.ም በራሳቸው መሬት ላይ ከፈቱ። አስተዳደሩን ለብዙ ጊዜ በልዩ ጽ/ቤታቸው ተቆጣጣሪነት አድርገው መሠረት ካስያዙ በኋላ ከበቂ ማደሪያ ጋር ለቤተክህነት አስረከቡ።

ዓላማው በጠላት ወረራ ወቅት ጉዳት የደረሰባቸውን ወጣቶች ሰብስቦ ለመርዳት ሲሆን የመጨረሻ ግቡ ግን እነሱንም ሆነ ሌላውን ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ለማሠልጠን ነበር። በዚሁ ዓላማ መሠረት ብዙዎች የቤተክርስቲያን አገልጋዮችን በበቂ መንፈሳዊ ዕውቀት እያሠለጠነ በማውጣት ለቤተክርስቲያኒቱ ታላቅ ድጋፍ ሆኗል።

የትምህርት ቤቱ ደረጃ ለብዙ ጊዜ ከ፩–፰ኛ ሆኖ ከቆየ በኋላ ከ፲፱፻፶፱ ዓ.ም ጀምሮ ሙሉ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመሆን ወጣቶች እንደሌላው የመንግሥት ት/ቤት ሁሉ ትምህርታቸውን አጠናቀው ለ፪ኛ ደረጃ መግቢያ ፈተና እየቀረቡ በሚገባ ስላለፉ ወደ ቅድስት ሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እየተዛወሩ ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ስለተደረገ መንፈሳዊ ኮሌጅ ሌላ መጋቢ ት/ቤት አገኘ።

ት/ቤቱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ከዘመናዊ ትምህርት ጎን ለጎን ብሉያት ሐዲሳት ሲሰጡበት የኖረ ነው። አሁንም ዕውቅ የብሉይና የሐዲስ መምህራን ስላሉበት በስብከተ ወንጌል የበሰሉ ምሩቃንን እያስመረቀ ያወጣል።

ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ ሰዋሰወ ብርሃን ት/ቤት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴና ግርማዊት እቴጌ መነን በቀየሱትና በተመኙት ዓላማ፣ በኋላም ቤተክርስቲያኒቱ በአዲስ መልክ እንዲደራጅ ባደረገችው ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት ደረጃ አገልግሎቱን በማበርከት ላይ ይገኛል።

## ፫ኛ. የልዑል ራስ መኰንን መምህራን ማሠልጠኛ ት/ቤት

በግርማዊ ጃንሆይ መልካም ፈቃድ በ፲፱፻፴፬ ዓ.ም የተመሠረተው ይህ ት/ቤት በሐረር ከተማ ጥምቀተ ባሕር እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ይገኛል። ት/ቤቱ በደርግ ጊዜ ከመወረሱ በፊት የሚመራው በሐረርጌ ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት ተቆጣጣሪነት የነበረ ሲሆን ለመምህራኑ ደመወዝም ሆነ ለአዳሪ ተማሪዎች የምግብና የልብስ ወጪ የሚችለው ይኸው ጽ/ቤት ነበር።

ልዑል ራስ መኰንን የግርማዊ ጃንሆይ አባት በሐረርጌ ለመንፈሳዊ ተግባር ከፍ ያለ ድርሻ ያበረከቱ ስለነበሩ ት/ቤቱ በሳቸው ስም እንዲሰየም ተደረገ። ሕንፃውን ግን የሰጡ ግርማዊነታቸው ነበሩ።

የት/ቤቱ ዓቢይ ዓላማ ግርማዊ ጃንሆይ እንዳቀዱት የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን በልዩ ልዩ መሥመር ለማገልገል የሚችሉ መንፈሳውያን ወጣቶችን ለማሠልጠን ነበር። በዚሁ መሠረት ከዚህ ት/ቤት ወደ ቅድስት ሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተላልፈው ትምህርታቸውን በኮሌጅ ደረጃ ጨርሰው ዲግሪ ያገኙና በከፍተኛ የሥራ ኃላፊነት ላይ ተመድበው የሚያገለግሉ ብዙዎች ናቸው።

ከላይ እንደተጠቀሰው በደርግ ዘመን ቢቋረጥም እስከዚያ ጊዜ ድረስ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ሌላው መጋቢ ይህ ት/ቤት ነበር። ት/ቤቱ እንደተመሠረተ ዓላማውን የተከተለ የጋለ እርምጃ ነበረው። በሀገር ትምህርት በሳል ዕውቀት ያላቸው በርካታ ተማሪዎችም ነበሩበት። በተመሠረተ ጊዜ በዚህ ት/ቤት ገብተው እንዲማሩ የሚፈቀድላቸው ወንዶች ብቻ ነበሩ። ከጊዜ በኋላ በተለይ በአዲስ መልክ በተሠራው ት/ቤት ሁለቱም ጾታዎች አብረው እንዲማሩ ተፈቅዷል።

## ፬ኛ. ሰበታ ቤተደናግል ጠባባት ገዳም ት/ቤት

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና ግርማዊት እቴጌ መነን በሰበታ የሚገኘውን ቤተ መንግሥታቸውን ለቤተክርስቲያን በመስጠት የሴቶች ገዳም እንዲሆን ከማድረግ ጋር ትምህርት ቤትም እንዲከፈት ፈቅደው ዕጓለማውታ ሕፃናትና የአካባቢው ልጆች ዘመናዊውንና መንፈሳዊውን ትምህርት እየተማሩ በሥነ ሥርዓት እንዲያድጉ አድርገዋል።

፭ኛ. ከላይ በተጠቀሱትና በሌሎችም ትምህርት ቤቶች ከተማሩት ደቀ መዛሙርት መካከል መንፈሳዊ ዝንባሌ ያላቸው ወጣቶች እየተመረጡ ወደ ውጭ አህጉር በተለይም ወደ ግብጽ፣ ግሪክ፣ ሩሲያ፣ ሮማንያ አሜሪካና ወደመሳሰሉት እየተላኩ ትምህርታቸውን በከፍተኛ ደረጃ እንዲከታተሉ አድርገዋል። ከቅዱስ ፓትርያርኩ ጀምሮ ዛሬ በቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳደር ተሰይመው በከፍተኛ



www.ethiopianorthodox.org

ደረጃ መንፈሳዊ አመራር በመስጠት ላይ ከሚገኙት ብፁዓን አባቶችና ምሁራን አንዳንዶቹ በግርማዊነታቸው ፈቃድ ተልከው በአገር ውስጥና በውጭ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት የተማሩ ናቸው።

እንግዲህ ከዚህ በላይ ከሰፈረው ጽሑፍ እንደተረዳነው ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ነበሩ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት በአቀራረቡ እየተሻሻለ እንዲቀጥል ከዘመናዊው ትምህርት ጋርም ተቀናጅቶ እንዲሰጥና ትምህርቱንም የተከታተሉ ምሁራን ቤተክርስቲያኒቱን በተሻለና በተቃና አስተዳደራዊ መሥመር እንዲመሩ ለማስቻል ያደረጉትን በጎ ጥረት ተመልክተናል።

ስለዚህ ባለውለታና ታላቅ ክርስቲያን ንጉሠ ነገሥት ስለሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪካቸውን ከፍ አድርጋ ስታወሳና በጸሎቷ ዘወትር ስታዘክራቸው ትኖራለች። ✣

## ረ. ስብከተ ወንጌል በማጠናከር

«ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ»
(ማር.፲፮፥፲፭)

ይህ ቃል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር በምድረ እስራኤል የሰበከውን ወንጌል ሐዋርያት ፈለጉን በመከተል ለዓለም ሁሉ እንዲያዳርሱት ያዘዘበት ቃል ነው። ሐዋርያዊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም በዚህ አምላካዊ ትእዛዝ መሠረት ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ወንጌልን ስታስተምር ኖራለች።

ከጥንት ጀምሮ የቤተ ክርስቲያኒቱ ዓቢይ ተግባር ሆኖ የኖረው የወንጌል ትምህርት እያደረ በተጠናከረ ሁኔታ እየተስፋፋ የመጣው በተለይም በዘመናዊ የአቀራረብ ስልትና ዘዴ መስጠት የተጀመረው በግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ነው። ለዚህም መነሻ መሠረት የሆነው ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ግርማዊነታቸው ዘመናዊና መንፈሳዊ ትምህርት ተቀናጅቶ የሚሰጥባቸው ት/ቤቶችን በማቋቋማቸው ከእነዚህ እየተመረቁ የሚወጡት ሰባክያን ለዚሁ ተግባር መመደብ በመቻላቸው ነው።

ሰባክያን እየበዙ ሲሄዱ የሚሰጡት የወንጌል ትምህርት በአፀደ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ተወስኖ እንዳይቀር፣ ሠራተኛው ሕዝበ ክርስቲያንም በያለበት ሆኖ የእግዚአብሔርን ቃል መስማት እንዲችል በግርማዊነታቸው መልካም ፈቃድ ከሃምሳዎቹ ዓመታት አጋማሽ ጀምሮ የወንጌል ትምህርት በኢትዮጵያ ሬድዮ ጣቢያ መስጠት ተጀመረ። ይህም የቤተክርስቲያኒቱ መሪዎች በታላላቅ በዓላት ከሚሰጡት ቡራኬና ቃለ ምዕዳን ሌላ ነው።

በመርሐ ግብሩ መሠረት ዘወትር ጧት ለ፲፭ ደቂቃ ዕለቱን፣ ወቅቱን የተመለከተ ጸሎትና ትምህርተ ወንጌል ለመላው ሕዝበ ክርስቲያን ሲተላለፍ፣ በዓቢይ ጾምና በጾመፍልሰታ ግን ጧት ብቻ ሳይሆን ማታም ይኸው ትምህርት ይተላለፍ ነበር። ከስብከቱም ጋር ልብ የሚመስጠው ያሬዳዊ ዜማ አብሮ ይሰማ ነበር። ይህ ፕሮግራም ይመራ የነበረው በጠቅላይ ቤተ ክህነት የስብከተ ወንጌል መምሪያ አማካይነት ነበር። ለማናቸውም መንፈሳዊ ሥራ ቅድሚያ የሚሰጡት ግርማዊ ጃንሆይ የኢትዮጵያ ሬድዮ ጣቢያ በተቋቋመበት ጊዜ ምግበ ነፍስ



ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ለትምህርተ ወንጌል ሥርጭት የሬዲዮ ጣቢያን መርቀው በከፈቱበት ጊዜ



www.ethiopianorthodox.org

በሆነው በቃለ እግዚአብሔር በጸሎት እንዲከፈት ማድረጋቸው በታሪክ ተዘግቦ ይገኛል።

የብሥራተ ወንጌል ሬድዮ ጣቢያም የካቲት ፲፱ ቀን ፲፱፻፶፰ ዓ.ም ሲቋቋም እንደዚሁ በጸሎት እንዲከፈት አድርገዋል። ምንም እንኳ ጣቢያው በሌላ የሃይማኖት ድርጅት የተቋቋመ ቢሆንም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም እንድታስትምርበት ግርማዊ ጃንሆይ ስለፈቀዱ በየዕለቱ የ፴ ደቂቃ ፕሮግራም ተሰጧት በደርግ መንግሥት እስከ ተዘጋበት ጊዜ ድረስ ሰፊ ትምህርት አቅርባበታለች።

ለዚህ ፕሮግራም ሰባክያንን ቀጥሮ ሥራውን በኃላፊነት የመራ የነበረው ከግርማዊነታቸው ልዩ ካቢኔ በጀት ተመድቦለት በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሥር የተቋቋመው ሐዋርያዊ ድርጅት ነበር።

በዚህ ድርጅት የድርሰትና የማስታወቂያ ክፍል የሚዘጋጀው ትምህርት ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን፣ ሃይማኖትን፣ የቤተክርስቲያንን ታሪክና ሌሎችንም ተዛማጅ የትምህርት ርእሶች ያካተተ ሲሆን የስርጭቱም ሰዓት በየቀኑ ከአዲስ አበባ ውጭ ላለው ሕዝብ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ከዓርባ ደቂቃ እስከ መሽቱ አንድ ሰዓት ከሃምሳ አምስት ደቂቃ ድረስ ሲሆን ለአዲስ አበባ ሕዝብ ደግሞ ከምሽቱ ሦስት ከሩብ እስከ መሽቱ ሦስት ሰዓት ተኩል ነበር።

የሐዋርያዊ ድርጅትና የጠቅላይ ቤተ ክህነት ሰባክያነ ወንጌል ከመደበኛው ሥራቸው በተጨማሪ በሥራ ቀናት ጧት ጧት በየትምህርት ቤቱ እየተገኙ የወጣቱን ሞራል የሚገነባ፣ ለማኅበራዊና መንፈሳዊ ሕይወቱ መመሪያ የሚሆን ትምህርት ይሰጡ ስለነበር፣ በትምህርቱ ሕይወታቸው የተለወጠው ብዙዎች ናቸው።

«ወዘአንበሌየስ ኢትክሉ ገቢረ ወኢምንተኒ» (ዮሐ.፲፭፥፭) ያለ እኔ ምንም ምን ማድረግ አትችሉም የሚለውን አምላካዊ ቃል ተገንዝበው በሥራቸው ሁሉ የእግዚአብሔርን ስም አስቀድመው ይንቀሳቀሱ የነበሩት ግርማዊ ጃንሆይ በወንጌል ትምህርት የሕዝቡ ሞራል እንዲታነጽ፣ እምነቱ እንዲጠነክርና ለሀገሩ ታማኝ ዜጋ እንዲሆን ያደርጉት የነበረው ጥረት አስተዋይ አእምሮ ላላቸው ሁሉ አርአያነቱ ከፍ ያለ ነው። ✣

## ሰ. የውጭ ግንኙነትን በማሳደግ

ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በውስጥም በውጭም በስፋት ተደራጅታ ትምህርተ ወንጌልን እንድታዳርስና ምእመናንን እንድታበዛ ከፍተኛ ዓላማ ነበራቸው። ይህንም ዓላማቸውን ከግቡ ለማድረስ:-

- በአፍሪቃና በመካከለኛው ምሥራቅ፣
- በአውሮፓና በአሜሪካ ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስ ቲያን መቋቋም ያልተቆጠበ ጥረት አድርገዋል።

ግርማዊነታቸው ከ፲፱፻፳፰ እስከ ፲፱፻፴፫ ዓ.ም በባት ኢንግላንድ በስደት በቆዩበት ወቅት ራሳቸውና ቤተ ሰባቸው ሌሎችም ተከታዮቻቸው የሚጸልዩበት ቤተ ጸሎት እንዲዘጋጅ አድርገው ነበር። ዘወትር የሚጸልዩና ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያንን የሚፈጽሙ ፰ መነኮሳት ካህናት አብረዋቸው ነበሩ። የተሟሉ ንዋያተ ቅዱሳትም ተዘጋጅተው ተወስደው ነበር። ይህም ድርጊት የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን በእንግሊዝ ሀገር ለማቋቋም መሠረት ሆኖ ቆይቷል።

ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ከድል በኋላ በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም በጎረቤት ሀገር በካርቱም ሱዳን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንድትቋቋም መመሪያና ትእዛዝ ከመስጠታቸው ጋር ለሕንፃው ማሠሪያ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ለግሰዋል።

ከ፲፱፻፵፰ ዓ.ም ጀምሮ እስከ ፲፱፻፶፱ ዓ.ም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በኒውዮርክ፣ በካረቢያን ደሴቶች ማለት በትሪኒዳድ በቶቤጎ፣ በባርቤዶስ፣ በጋያና፣ በጃማይካና በቬርሙዳ፣ በበርጂን አይላንድስ በሴንት ቶማስና በሴንት ኪትስ ደሴቶች ከአሥር ያላነሱ አብያተ ክርስቲያናት በግርማዊነታቸው ፈቃድና ትእዛዝ ተቋቁመዋል።

በእነዚህ ደሴቶች ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መቋቋም መነሻ ምክንያት የሆኑት ራሳቸው ተወላጆች ነበሩ። ከጥቁር ሕዝብ ሀገሮች ሁሉ ነፃ ሕዝብና ነፃ ቤተ ክርስቲያን ያሏት ነፃ ሀገር ኢትዮጵያ ብቻ ስለሆነች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን እምነት ለመከተል ፈለጉ፤ አስተማሪ ካህንም እንዲላክላቸው ጠየቁ፤ በተለይም የትሪንዳድና የቶቤጎ መንግሥታት በሀገራቸው ለምትቋቋመው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ግንባታ ሠላሳ ሄክታር መሬት ሰጥተዋል።

ግርማዊነታቸው ስለ ጥቁር ሕዝብ ነፃነት ከፍተኛ ተጋድሎ ያደርጉ ስለነበር በ፲፱፻፶፱ ዓ.ም ጃማይካን በጎበኙ



www.ethiopianorthodox.org

ጊዜ የጃማይካና የሌሎችም የካረቢያን ሕዝቦች ስለ እርሳቸው የተለየ አመለካከት ነበራቸው። ይህንም ልዩ አመለካከት ለማስቀረት ግርማዊነታቸው ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው ካህናት እንዲላኩላቸውና ስለ ክርስቶስ ትክክለኛ እምነት እንዲኖራቸው አድርገዋል።



ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በ፲፱፻፶፯ ዓ.ም በአዲስ አበባ አፍሪካ አዳራሽ የተካሄደውን የኦሪየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጉባኤ በንግግር ሲከፍቱ

በ፲፱፻፷፰ ዓ.ም በሎንደን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም በግርማዊነታቸው ፈቃድና ትእዛዝ ተመሠረተች። ዛሬም ይህች ቤተ ክርስቲያን በሎንዶን ለሚኖሩ የኢትዮጵያ ምእመናንና እምነትዋን ለሚከተሉ ሌሎች ሕዝቦችም ሐዋርያዊ ተልእኮ በመስጠት ትገኛለች።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክረስቲያን በዓለም ያለች እንደመሆንዋ መጠን ስለ ሌላው ዓለም ማወቅ፣ ማየትና መስማት ስለ ራስዋም ለሌላው ማሳወቅ፣ የተራድኦ፣ የሰላም ግንኙነትና የመሪዎች የጉብኝት ለውውጥ ማድረግ እንደሚገባት ግርማዊነታቸው አርቆ በማሰብ የውጭ ግንኙነትዋ እንዲጠናከር አድርገዋል። በዚሁ መሠረት:-

፩. በ፲፱፻፵ ዓ.ም የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት፣

፪. በ፲፱፻፶፮ ዓ.ም የመላው አፍሪቃ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ሲመሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሥራች አባል እንድትሆን ፈቅደዋል፣

፫. በ፲፱፻፷፫ ዓ.ም በግርማዊነታቸው ፈቃድ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ማዕከላዊ ኮሚቴ አራተኛ ስብሰባን አስተናገዳለች፣

፬. በ፲፱፻፷፩ ዓ.ም የሮማንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ጁስቲንያን ግርማዊነታቸው ባደረጉላቸው ጥሪ መሠረት የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ጎብኝተዋል። ከዚያ በፊት ግን ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በ፲፱፻፶፯ ዓ.ም የሮማውያን መንግሥት በጎበኙ ጊዜ እውነተኛ ክርስቲያን ንጉሠ ነገሥት ስለነበሩ የሮማንያን ቤተ ክርስቲያን ጎብኝተዋል። ያን ጊዜም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዲጎበኙላቸው ግርማዊነታቸውን ስለ ጠየቁ ጥቅምት ፳፰ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ.ም ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ የቅዱስ ፓትርያርኩ እንደራሴ የሮማንያን ቤተ ክርስቲያን እንዲጎበኙና ስለ ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት እንዲወያዩ ተደርጓል።

፭. በ፲፱፻፶፯ ዓ.ም ከጥር ፯–፲፫ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በ፬፻፴፩ ዓ.ም በኤፌሶን ከተደረገው ጉባኤ ወዲህ መጀመሪያ የሆነውን የኦሪየንታል ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት የቅዱሳን ፓትርያርኮችን ጉባኤ አዘጋጅና አስተናጋጅ በመሆን ከፍተኛ የውጭ ግንኙነትን ተልእኮ ፈጽማለች። ይህ ታሪካዊ ጉባኤ በአዲስ አበባ እንዲደረግ በእግዚአብሔር ኃይል ቀስቃሽና አነሣሽ ደገኛው ክርስቲያን ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ነበሩ። ለዚሁ ጉባኤ በኦሬንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ አንድ ምዕራፍ ተከፍቶለት የግርማዊነታቸው ስም እንደ ቆስጠንጢኖስ ሲዘከር ይኖራል።



www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ታሪካዊ ጉባኤ የነበሩትን ቅዱሳን ፓትርያርኮች በመወከል ፓትርያርካዊ ንግግር ያደረጉት የአንጾኪያ–ሶርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ፓትርያርክ ማር አገናጢዮስ ያዕቆብ ስለ ታላቁ ክርስቲያን ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴ እንዲህ ብለዋል።

«ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በዚህ ታሪካዊ ጉባኤ መክፈቻ ዕለት የግርማዊነትዎን ንግግር ስናዳምጥ በ፫፻፳፭ ዓ.ም በተደረገው የኒቅያ ጉባኤ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ያደረገው የጉባኤው መክፈቻ ንግግር ትዝ ይለናል። ቤተ ክርስቲያኖቻችን ለብዙ ዘመናት በዚህ መልክ አልተሰበሰቡም፤ ነገር ግን አሁን እግዚአብሔር በአገልጋዩ በግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ እንድንሰበሰብ ፈቀደልን።

«የክርስትና ሃይማኖት ጋሻ የሆኑት ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ እኛን ለማሰባሰብ ማበረታታትን፣ ኦርቶዶክሳዊ እምነትንና ጥብዐን ባያሳዩን ኖሮ ይህ ሁሉ ሊሆን ባልቻለም ነበር።»

«የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ መሠረት ያለው እምነት፣ ዕውቀትና ትሕትና ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር መስጠታቸው በአንድነት እንድንሰበሰብ አነሣሥቶናል። ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ አንድ ብቸኛ ኦርቶዶክሳዊ ንጉሣችን ናቸው።»

የማላንካራ ሕንድ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ፓትርያርክ ማር ባስልዮስም ስለ ግርማዊነታቸው ታላቅነት «ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ለኦርቶዶክስ እምነት ጋሻ እንደሆኑ የሁላችንን አሳብ በምናገርበት ጊዜ እመካለሁ» ብለዋል።

ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በቅዱሳን ፓትርያርኮች እንደተባለላቸው ነበሩ፣ አዎ ከዚያም በላይ ነበሩ።

፯ በጥር ፲፱፻፶፰ ዓ.ም የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ፒሜን በግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ፈቃድ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ኢትዮጵያን ጎብኝተዋል። ስለ ሁለቱም አብያተ ክርስቲያናት መግለጫ ወጥቶ በመሪዎች ተፈርሟል።

ግርማዊነታቸው ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የውጭ ግንኙነት ከፈጸሙአቸው ተግባራት ለአብነት ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ተሞከረ እንጂ በሊቃነ ጳጳሳት፣ በጳጳሳትና በሊቃውንት የተደረገው የጉብኝትና የነፃ ትምህርት ልውውጥ በጣም ብዙ ነው። ግርማዊነታቸው ዓለማትን በጎበኙበት ወቅት ሁሉ ቤተ ክርስቲያኒቱን ያላስተዋዋቁበት ጊዜ እንደ ሌለ የታወቀ ነው፤ በዘመናቸው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ሕዝብ የይለፍ ደብተር አርማ «ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር» የሚለው ጥቅስ ነበር። ጥቅሱን በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የይለፍ ደብተር ላይ የሚመለከት የዓለም ሕዝብ ሁሉ ኢትዮጵያ መምለኪተ እግዚአብሔር፣ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴም እውነተኛ ክርስቲያን ንጉሠ ነገሥት እንዲሆኑ ያስተውል ነበር። ✣



ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የወዳጅ አገሮች አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችን ሲያነጋግሩ



www.ethiopianorthodox.org

# «እግዚአብሔር የፃድቃን ሞት አስፀያፊ ቢሆንም» እግዚአብሔር አፅማቸውን ይጠብቃል

ይህ ቃል ስለ ሰው ልጅ አፅም ክቡርነትና በእግዚአ ብሔር ዘንድ ስለሚደረግለት ጥበቃም የተነገረ የቅዱስ መጽሐፍ የምስክርነት ቃል ነው (መዝ.፴፬፥፳)

የሰው ልጅ አንደኛ በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል የተፈጠረ፣ ሁለተኛ ተስፋ ትንሣኤ ያለው ልዩ ፍጡር በመሆኑ በሕይወት የቆመውም ሆነ በሞት የወደቀው አካሉ በሰውነቱ ብቻ በእግዚአብሔር ዘንድ በእርግጥ ከሌላው ሥነ ፍጥረት የተለየ ክብር አለው፤ የሚደረግለት ጥበቃም እንዲሁ ከሌላው ሥጋዊና ደማዊ ፍጥረት የተለየ ነው።

እንዲሁ በእግዚአብሔርም በሰውም ዘንድ ዋጋ ያላቸው የክብር ባለቤቶች ናቸው። ስለሆነም ከሞት በኋላ ለእነዚህ ዓይነት ወገኖች አፅም የሚሰጠው ክብርና የሚደረገውም ጥበቃ ወይም እንክብካቤ በደረጃው ከሌላው የተለየ ነው። እንዲያውም ለአፅማቸው የሚሰጠው ክብር በቁመናቸው ሳሉ ከነበረው አጅግ የላቀ መሆኑ ግልፅ ነው፤ ይኸውም በዚህ ዓለም ማንኛውንም መንፈሳዊና ማኅበራዊ ተልእኮ የሚጠይቀውን መሥዋዕትነት በመክፈል ለሕያው ታሪክ የሚበቁ የገድል ሰዎች በአብዛኛው ውለታቸውና ታላቅነታቸው ጎልቶ የሚታወቀው ከአለፉ በኋላ ስለሚሆን ነው። የእነዚህ ዓይነቱ ሰማዕታት አፅም እንደ ማንኛውም



የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ አፅም አርፎበት የቆየው የታዕካ ነገሥት በዓታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን

ይህ እንዳለ ሆኖ በተለይ አካሔዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረግ የዚህ ዓለም ሩጫቸውን የፈጸሙ ቅዱሳን፣ ጻድቃንና ሰማዕታት በእግዚአብሔር ዘንድ የተለዩ ሰዎች በመሆናቸው የእነሱ አካልም ከሌላው ሰው የተለየ ክብር ያለው ነው። አፅማቸው በሕይወተ ሥጋ ሳሉ የሠሩትን በጎ ሥራና የፈጸሙትን ገድል ሁሉ ተግባራዊ ያደረጉበት አካል ስለሆነ ቅዱስ ነው፣ ክቡር ነው፣ ሕያው ነው።

በዚህ ዓለም ለሀገርም ሆነ ለወገን የሚጠቅም መሥዋዕትነት በመክፈል ለሕያው ታሪክ የበቁ ሰዎችም ሰው አፅም የሚታይ ሳይሆን ለሀገርና ለወገን የሚያኮራ ሥራ የተሠራበት፣ በሰውና በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ ያለው መንፈሳዊና ማኅበራዊ ጽድቅ የተፈጸመበት ልዩ አካል ስለሆነ በእርግጥ የክብር ክብር አለው።

«እግዚአብሔር አፅሞቻቸውን ሁሉ ይጠብቃል» በሚል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅስ በመነሣት ይህን የምስክርነት ቃል ለመስጠት ምክንያት የሆነን ሌላ አይደለም፤ በዛሬው ዕለት ከአንድ የክብር ቦታ ወደ ሌላ የክብር ቦታ ተዛውሮ እንዲያርፍ እየተደረገ ያለው የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ፍልሰተ አፅም ሥነ ሥርዓት አፈጻጸም ነው።



www.ethiopianorthodox.org

ዛሬ በዚህ ሁኔታ ፍልሰተ አፅማቸው እየተከበረ ያለው ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በመንፈሳዊም ሆነ በሥጋዊው የሥራ መስክ አኩሪ ሥራ የሠሩ ታላቅ መሪ ነበሩ። ለዚህም እውነተኛ ምስክራቸው ሕያው ታሪካቸው ነው። ይህ ታሪካቸው ወደፊት በሚነሣው ትውልድ ዘንድም የበለጠ ሲያስከብራቸው እንደሚኖር አርግጠኛ ሆኖ መናገር ይቻላል። ይኸውም የኢትዮጵያ ሕዝብ በረጅም ዘመን ታሪኩ የባለ ታሪክ ሰዎችን ዝክረ–ስም የማይዘነጋ ታላቅ ሕዝብ መሆኑ ስለሚታወቅ ነው። ዛሬ በየገዳማቱና አድባራቱ እንደ አፅመ ቅዱሳን ልዩ ጥበቃ እየተደረገለት የሚገኘው የጥንታውያን ዕውቅ መሪዎች አፅም፣ እንዲሁም በብርቅና ድንቅ ቅርስነት በክብር እየተጠበቁ ያሉ በየዘመኑ የተነሡ የታሪክ ሰዎች ታሪክ የሠሩባቸውና ገድል የፈጸሙባቸው መሣሪያዎችም ሆኑ ከተለያዩ ቀደምት አበው ለቤተ ክርስቲያን የተበረከቱ ንዋያተ ቅዱሳት ብዛት በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ይህ ሁሉ የሚያመለክተው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለታሪክና ባለታሪክ የሚሰጠውን ክብር ከፍተኛነት ነው።

የታሪክ ተወቃሽነት በማያስፈራቸው ግፈኞች እንደ ጉድፍ የትም ተጥሎ የነበረው የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ አካለ ሥጋ ከተጣለበት ድብቅ ቦታ ተፈልጎ ተገኝቶ በመጀመሪያ በታላቋ የታዕካ ነገሥት በአታ ለማርያም ገዳም በክብር ዐርፎ እንዲቆይ፣ አሁን ደግሞ ራሳቸው ንጉሠ ነገሥቱ ባሠሩት መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ዐርፎ እስከደገኛው ትንሣኤ ድረስ የክብር ቆይታ እንዲያደርግ የመንግሥትም የሕዝብም ፈቃድ የሆነው በሚገባ ስለሆነ ድርጊቱ ለዚህ መልካም ተልእኮ አፈጻጸም የደከሙትን ሁሉ የሚያስመሰግን ነው።

የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ አፅም አሁን ለዚህ ክብር የበቃው ቅዱስ መጽሐፍ «እግዚአብሔር አፅሞቻቸውን ሁሉ ይጠብቃል» ሲል እንደተናገረው በእግዚአብሔር ረድኤት ህልውናው ተጠብቆ ስለቆየ ነው። እግዚአብሔር የተናገረውን የሚፈጽም አምላክ መሆኑን መረዳት የሚቻለውም ከእንዲህ ዓይነቱ ተግባር ሁሉ ነው።

አፅምን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ማዛወር አሁን የተጀመረ ባህል አይደለም፣ ጥንትም የነበረ ልማደ ሰብእ ነው። በምድረ ግብጽ በስደት ይኖር የነበረው የእግዚአብሔር ሰው ያዕቆብ ሲሞት አካለ ሥጋው ከግብጽ ወደ ከነዓን ፈልሶ ራሱ አስቀድሞ በመረጠው መካነ ዕረፍት እንዲያርፍ ተደርጓል (ዘፍ.፵፱፥፳፱፤ ፶፥፲፪)። የልጁ ዮሴፍ አፅምም በራሱ የአደራ ቃል መሠረት ከግብጽ ወደ ከነዓን እንዲፈልስ ሆኗል (ዘፍ.፶፥፳፫፤ ዘጸ.፲፫፥፲፱)።

የሰው ልጅ ሕይወት በልደት ተጀምሮ በሞት የሚያከትም ነገር አይደለም፤ የሰውን ተፈጥሮ ከሌላው የተለየ የሚያደርገው ይህ ውሱን ሕይወት ሳይሆን ከሞትና መቃብር ማዶ ያለው ዘለዓለማዊ ኑሮ ነው። ለሰው ልጅ አካል ይህን ያህል ክብር የሚሰጠውም ለዚያ ዘላለማዊ ሕይወት የተፈጠረ መሆኑን በማረጋገጥ ስለሆነ ድርጊቱ ሃይማኖታዊ ነው።

ይህም ሲባል በክብር ቦታ ለማረፍ ያልቻለ አፅም ሁሉ ክብር የሌለው ነው ማለት አይደለም። በዚህ ዓለም ላይ በተለይ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ጽድቅን በመፈጸም ራሳቸውን መሥዋዕት የሚያደርጉ የገድልና የትሩፋት ሰዎችም ሆኑ የሀገር ነፃነትና ሉዓላዊነት የሚጠይቀውን ገድል በመፈጸም ላይ እንዳሉ የሚወድቁ አርበኞች አጽም አቀማመጥ ተመሳሳይነት ላይኖረው ይችላል። ሁኖም ያ አፅም የጻድቃን ሰማዕታት፣ ያ አጽም የአርበኞች አጽም እስከሆነ ድረስ የወደቀበትና የረገፈበት ቦታ ሁሉ የክብር ቦታ ነው። አምላካችን ከሃሊ ስለሆነ የረገፈ አጽማቸውን ሁሉ በየወደቀበት ቦታ ለክብር ትንሣኤ በክብር ይጠብቀዋል፤ ያስጠብቀዋል።

በዘመነ ሰማዕታት የሰማዕታትን አፅም እየሰበሰቡ በክብር ቦታ የሚያስቅምጡ አማንያን እንደነበሩ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያዘክራል። ይህ በጎ ተግባር ከዚያም በኋላ በትውፊትነት ስለቀጠለ በሁሉም ዘመን ሲፈጸም ኑሯል።

ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በዘመናቸው ንጉሠ ነገሥት ወይም የሀገር መሪ ብቻ ሳይሆኑ፣

- የኢትዮጵያ ኦረቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከግብጽ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን የበላይ አመራር ነፃ ሁና በራስዋ ጳጳሳትና ቅዱስ ሲኖዶስ እንድትመራ፣
- አብያተ ክርስቲያናት እንዲታነጹ፣
- መንፈሳውያን መጻሕፍት እየታተሙ ለምእመናን እንዲዳረሱ፣
- . በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዕድገትና ጥንካሬ እንድታገኝ ጥረት ያደረጉ የቤተ ክርስቲያን ባለውለታ ስለነበሩ የቤተ ክርስቲያናችን ምእመናን ሆን ተብሎ ፍለጋው እንዲጠፋ ተደርጎ የነበረውን አፅማቸውን ፈልጎ በማግኘት ለዚህ ክብር ማብቃታቸው ቤተ ክርስቲያናችን በምእመናኖቿ እንድትኮራና እንድትመካ የሚያደርግ ቅዱስ ተግባር ነው።

በተለይም ንጉሠ ነገሥቱ በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ራሳቸው ለራሳቸው በአዘጋጁት መካነ ዕረፍት አፅማቸው እንዲያርፍ መደረጉ ከሒሊና ወቀሳ ነጻ የሚያደርግ በጎ ተግባር ስለሆነ ይህን በጎ ተግባር ለማቀድና ለመፈጸም የበቁ ሁሉ በዚህ ተግባራቸው መንፈሳዊ ደስታ ሊሰማቸው ይገባል።

«እግዚአብሔር አፅሞቻቸውን ሁሉ ይጠብቃል» ተብሎ የተነገረው አምላካዊ ቃል ዛሬም በዚህ ሁኔታ ሲፈጸም ለማየት በመብቃታችን ለቅዱስ አምላካችን ክብርና ምስጋና እናቀርባለን። ✣



www.ethiopianorthodox.org

# «ስምከ ሕያው ዘኢይመውት»
# ስምህ የማይሞት ሕያው ነው

የሰው ልጅ ከሌሎች ምድራውያን ፍጥረታት ሁሉ ተለይቶ በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ ስለ ተፈጠረ በነፍሱ ሕያውና ዘለዓለማዊ ነው። የሰው ነፍስ ወደ ሰጭዋ ወደ እግዚአብሔር ስትመለስ ለጊዜው በመቃብር እንዲቆይ የሚደረገው ሥጋውም በፍጻሜ ዘመን ተነሥቶ ከነፍስ ጋር በመዋሐድ እንደገና ሕያው ሆኖ ለዘለዓለም ይኖራል።

ከዚህም ጋር ሰው ከሞተ በኋላ ስሙ በዚህ ዓለም ሕያው ሆኖ ሁል ጊዜ ሲወሳ እንዲኖር የሚያደርጉ ብዙ ምክንያቶች አሉ።

«ደስ የሚያሰኘኝን ነገር ለሚመርጡ የማይጠፋ የዘለዓለም ስምን እሰጣቸዋለሁ» ይላል እግዚአብሔር (ሲራ.፵፬፥፲–፲፬፤ ሲራ.፴፺፥፳፱፡ ኢሳ.፶፮፥፭)።

ሰው መዋቲ ቢሆንም ለዓለም የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ሁል ጊዜ ስለሚታወስ ስሙ ከሥራው ጋር ሕያው ሆኖ ይኖራል። ስለዚህም፣ ስም ከመቃብር በላይ ነው» ይባላል። ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከታሪክ እንደምንረዳው እንደ እነ አብርሃም፣ ሙሴና ዳዊት ያሉ



ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

ታላላቅ ሰዎች ስለ እግዚአብሔርም፣ ስለ ሕዝብም በፈጸሙት ሥነ ገድል ሞተው ሳሉ ሕያዋን ናቸው፤ ተቀብረውም ሳሉ ከመቃብር በላይ ናቸው። እንዲህ ስለ ተባለም ሞትንና መቃብርን ለመካድ አይደለም፤ ነገር ግን አስደናቂው ሥራቸውና ሕያው ታሪካቸው የሞት ጠላ ሳይጋርዳቸው፣ የመቃብር አፈርም ሳይጫናቸው ሁል ጊዜ የሚኖሩ መሆናቸውን ለመናገር ነው።

ሰዎች በዓለም ላይ በተለያዩ ምክንያቶች ስመ ገናና ወይም ዝነኛ ሊሆኑ ይችላሉ፤ በተፈጥሮ ዕውቀታቸውና በትምህርታቸው፣ በሃይማኖተኛነታቸውና በበጎ ሥነ ምግባራቸው፣ በደግነታቸውና በለጋስነታቸው፣ በጀግንነታቸውና በሀገር ታዳጊነታቸው፣ በፍቅራቸውና ስለ ሰው ዘርዕ ሁሉ ዕኩልነት ባላቸው ቀና አመለካከት፣ በአመራርና በአስተዳደር ችሎታቸው፣ በጥበባቸውና አዲስ ግኝትን በማስገኘታቸው፣ በሀገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ተግባራቸው በመሳሰለውም ሁሉ የማይሞት ሕያው ስምን ያተርፋሉ። እንደ እነዚህ ላሉ ሰዎችም የእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ይናገርላቸዋል።

«የደጋግ ሰዎች ጽድቃቸው አይረሳም፣
ክብራቸው አያልቅም፣
በሕዝቡ ዘንድ ብልህና አስተዋይ የሆነ ሰው
ዋጋውን ያገኛል ስሙም ለዘለዓለም ይኖራል»

እነሆ ከሃያ አምስት ዓመታት በኋላ የከበረ አፅማቸውን በዚህ በተቀደሰው ምዕራፈ ክብር በማሳረፍ በከፍተኛ ክብር የምናስባቸው ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሠሩት ሥራቸው ሕያው ናቸው፤ በሕያው ታሪካቸውም ሕያው ናቸው።

www.ethiopianorthodox.org

በአንድ ወቅት ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ታሪካዊ ንግግር ሲያደርጉ «ታሪክ በማናቸውም መልኩ አይደመሰስም፣ የታላቅ ሥራ መታሰቢያም ለጊዜው በግዙፍ ከመታየት ቢሰወርም ጠላት ሊማርከው አይችልም። ከፍተኛ ዋጋ ያለውን የሰዎችን ሥራ ሊያጠፉ የሚደክሙ ቢኖሩ ለማጥፋት የተነሡት ራሳቸው በክፉ ሥራቸው የራሳቸውን ታሪክ ያጠፋሉ፣ የታላላቅ ሰዎች ሥራ ግን የክፉዎች ተንኮል ሳይደመስሰው ሁል ጊዜ ሕያው ሆኖ ይኖራል» ብለው ነበር። አዎ ይህ ቃላቸው ወቅታዊ ትንቢታዊም ነበር። በመሆኑም በየጊዜው የማያቋርጥ ቀጣይ ትርጓሜን የዞ ይታያል። በታላላቅ ሰዎች ላይ በትዕቢትና በዓመፅ በየጊዜው የተነሡ ሁሉ ዓመፃቸው በራሳቸው ተመልሷል «የትዕቢተኛ እግር አይምጣብኝ፣ የኃጢአተኛም እጅ አያውከኝ፤ ዓመፅን የሚያደርጉ ይወድቃሉ፣ ይሰደዳሉ፣ መቆምም አይችሉም» የሚለው ትንቢታዊ ቃል ይፈጸምባቸዋል (መዝ.፴፭፥፲፩–፲፪)

የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ሥራቸውንና ታሪካቸውን፣ ስማቸውንና የስማቸውንም መታሰቢያ ለማጥፋት ተሞክሮ ነበር፤ ይሁን እንጂ በእርሻ ውስጥ አፈር የለበሰ የስንዴ ዘር አፈሩን ዘልቆ እንደሚበቅልና እንደሚያፈራ የተሰወረው ሥራቸውና ታሪካቸው በእግዚአብሔር ፈቃድ ተገልጦ እነሆ ዛሬ በአደባባይ ለመነገር ቻለ «የማይገለጥ የተከደነ፣ የማይታወቅም የተሰወረ የለምና» ምን ጊዜም ቢሆን እግዚአብሔር ያከበረውን ማንም ሊያዋርደው አይችልም። እግዚአብሔር የባረከውንም ሊረግመው የሚችል ማንም የለም።

ስለሆነም የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የክብር፣ የሥራና የታሪክ ሰውነት ምን ጊዜም አይሰወርም። መልካም ሥራቸው ከእነ ክብሩ በተተኪው ትውልድ ተወርሶ ሲወሳ ይኖራል።

የቀደሙት ሃይማኖታቸው የጸና የኢትዮጵያ ነገሥታት የተመኙትንና በተስፋ የተመለከቱትን ብዙ ጊዜም የደከሙለትን ከፍተኛውን የፓትርያርክነት መዐርግ ለቤተ ክርስቲያናችን እንዲገኝ ማድረጋቸውን ትውልድና ታሪክ ለዘለዓለም አይረሱትም የማይሞተው ስማቸው በወርቅ ቀለም የተጻፈበት አንደኛው ዓመደ ወርቅም ይህ ታሪካቸው ነው። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊት ጥንታዊት፣ ታሪካዊትና ብሔራዊት ለመሆንዋ የተገባውን ክብርና መብት ያገኘች በግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ነው። ለነፃይቱ ኢትዮጵያ ነፃ ቤተ ክርስቲያን እንድትኖራት አድርገዋል። እነዚህ ነፃ ሀገርና ነፃ ቤተ ክርስቲያን በነፃነት በሚኖሩበት ዘመን ሁሉ የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ስም የማይሞት ሕያው ነው።

ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ለቤተ ክርስቲያን የዋሉት መልካም ውለታ ሁሉ በሥነ መንግሥት አቅዋም ዝነኛነትን ለማትረፍ የተደረገ ሳይሆን እንደ ቆስጠንጢኖስና እንደ አባቶቻቸው አብርሃና አጽብሐ ዕውነተኛ ሃይማኖታዊ መሪ በመሆናቸው የተከናወነ ነበር። ለሥራቸው ሁሉ እግዚአብሔርን ጀማሪና ፈጻሚ አድርገው ይሠሩ ነበርና ነው። ግርማዊነታቸው በዘመናቸው «የክርስትና ሃየማኖት ጠባቂ» ከመሆናቸው በላይ ለክርስትና ሃየማኖትና ለበጎ ሥነ ምግባር በስፋት መዘርጋት እንደ አንድ ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ነበሩ።

ስለዚህም ሁሉ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ታላቁ ክርስቲያን ንጉሥ ቆስጠንጢኖስን «አሥራ ሦስተኛ ሐዋርያ» በማለት ሁል ጊዜ በክብር እንደሚያስቡት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ዐቢይ ገብረ ሐዋርያ ለፈጸሙት ለግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ስለ ክርስትና ሃይማኖት ጠባቂነታቸው ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚገባትን መብትና ነፃነት ስለማስገኘታቸውና ስለ መንከባከባቸው ከፍተኛ ክብርን ትሰጣለች።

አብያተ ክርስቲያናትን በማሳነፅ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማስተርጎም፣ በማጻፍና በማሳተም፣ የከበሩ ንዋያተ ቅዱሳትን በመለገስ፣ መንፈሳውያን ትምህርት ቤቶችን በመደገፍ ለመምህራኑና ለደቀመዛሙርቱም አስፈላጊውን ሁሉ በማሟላት፣ እጅግ የተደነቁ የቤተ ክርስቲያን ቅርሶችም እንዲጠበቁ በማድረግ የፈጸሟቸውን ተግባራትና ሌሎችንም ውለታዎቻቸውን ሁሉ ቤተ ክርስቲያናችን ዘወትር ትመሰክራለች። ለመጭው ትውልድም በታሪክ ታስተላልፋለች እጅግ ይጠነቀቁላት የነበሩትን ታላቅ መሪ እንደ ቆስጠንጢኖስና እንደ ቴዎዶስዮስ «ፍቁረ ክርስቶስ፣ ቀዋሚሃ ለቤተ ክርስቲያን» በማለት ትጠራቸዋለች። በመጻሕፍትዋና በመዛግብትዋ በአረፍትዋና በአዕማድዋ እንዲሁም በከበሩ ንዋያተ ቅዱሳትዋ ተመዝግቦ የሚገኘውን መታሰቢያቸውን ሁሉ ለዘለዓለም ትጠብቃለች። በማይቋረጠውና በልዑል እግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ባለው ጸሎትዋም አትረሳቸውም፤ የሚረሱ አይደሉምና።

ቅዱሳት መጻሕፍት «እግዚአብሔርን በመታመን የሚመካ ሰውን ብዙዎች ስለ ጥበቡ ያመሰግኑታል፤ መታሰቢያው አይጠፋም፣ ስሙም ለልጅ ልጅ ዘመን ጸንቶ ይኖራል፣ ሕዝቦች ሁሉ ስለ ብልህነቱ ይነጋገራሉ፣ በጉባኤም መካከል ያመሰግኑታል የስሙ ሕያውነትም ከሺህ ልጆች ይሻላል፣ ከሞተም በኋላ ሥራው የጸና ነው» በማለት በልዑል እግዚአብሔር ለሚመኩ ሰዎች የተሰጠውን እርግጠኛ ተስፋ ይመሰክራሉ (ሲራ.፴፱፥፱–፲፩)

በዚህ ሕያው ቃል መሠረት በኃያሉ እግዚአብሔር በመታመንና በመመካት ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን የኃላፊነት ሥራ ይሠሩ የነበሩት ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በብልህ አመራራቸውና ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትና ዕድገት በነበራቸው አቀዋም በሕይወታቸው የተመሰገኑትን ያህል ዛሬም ከሞታቸው በኋላ እየተመሰገኑ ነው። ወደ ፊትም ታሪክ በውዳሴ ያዘክራቸዋል። ስማቸውና ሥራቸውም ለልጅ ልጅ ዘመን ጸንቶ የኖራል።

አፅማቸው በአልባሌ ቦታ ተደብቆ እንዲቀር ያልፈቀደ እግዚአብሔር አምላክ፤ ስማቸውም ታሪካቸውም ተደብቆ እንዲቀር አይፈቅድምና። ✣

«ወይትባረክ እግዚአብሔር»



www.ethiopianorthodox.org

# «ዝክረ ጻድቅ ለዓለም ይሄሉ»
# የጻድቅ መታሰቢያ ለዘለዓለም ይኖራል

በባሕርዩ ጻድቅ ፍጹም እግዚአብሔር ብቻ ነው። በቅን መንገድ የሚመላለስ፣ የጽድቅን ሥራ የሚሠራ አካሔዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገ በሰውና በእግዚአብሔር ፊት የሚወደድ በጎ አገልግሎት ያለው ሰውም ጻድቅ የባላል።

ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት «እግዚአብሔርን የሚፈራ፣ አስተዋይ አእምሮ፣ ቅን ልቡና ያለው በፍርድ ጊዜ ቃሉን የሚጠብቅ ሰው ንዑድ ክቡር ነው። እንደዚህ ያለው ሰው በመከራ አይታወክም፣ ለዘለዓለም አይናወጥም፣ ከክፉ ነገርም አይፈራም፣ ክብርና ባለጠግነት በቤቱ ነው፣ ጽድቁ ለዘለዓለም ይኖራል፣ ሥራው ለትውልደ ትውልድ ይነገራል። መታሰቢያው አይጠፋም» በማለት የማይጠፋ ታሪክና የማይረሳ ሕያው ስም ማግኘት የሚያስችሉ መንገዶችን አመልክቷል።

አኗኗራቸውና አካሔዳቸው በፈሪሀ እግዚአብሔር የነበረ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ወደ መቶ በተጠጋው የዕድሜ ብልጽግናቸው ብቻ ሳይሆን ከአንድ ምዕተ ዓመት አጋማሽ በላይ በቆዩበት ረዥም የመሪነት ዘመናቸው የፈጸሟቸው ታላላቅ ተግባራት፣ ባለውና በሚመጣው ትውልድ ሲታሰቡ የሚኖሩ በታሪክ ሰፌ ምዕራፍ ያላቸው ናቸው።

የግርማዊነታቸውን ስምና ታሪክ ሲያስታውሱ የሚኖሩትም በመሪነት ደረጃ የተከናወኑት ብቻ አይደሉም።

በተፈጥሮ ደግነትና አስተዋይ ልቡና የተከናወኑት የጽድቅ ሥራዎችም እጅግ ብዙ ናቸው።

«እግዚአብሔር ጻድቅ ነው፣ የጽድቅን ሥራ ይወዳል» የተባለውን በማስተዋልና «እኔ ቅዱስ እንደሆንሁ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ» ተብሎ በተጻፈው የጽድቅና የቅድስና መንገድ በመመላለስ ሕይወታቸውን በመልካም ተግባር ተርጉመው አልፈዋል።

«በረከተ እግዚአብሔር ውስተ ርእሰ ጻድቃን

የእግዚአብሔር በረከት በጻድቃን ራስ ጸንቶ የኖራል» (ምሳ.፲፥፮) ተብሎ እንደተጻፈ ረድኤተ እግዚአብሔር ያልተለያቸው የተፈጥሮ ደግነትና አስተዋይ ልቡና ያላቸው በመሆናቸው ከእግዚአብሔር ያገኙትን ሀብትና በረከት ሁሉ በምግባረ ሠናይ አገልግሎት ላይ በማዋል ለቀሪው ትውልድ መልካም አርአያነት ያለው የበጎ መጋቢ ሥራ ሠርተውበታል።

መጠጊያ ያጡ ችግረኞች፣ የአካል ጉዳተኞችና ዓይነ ስውራን ልጆች የትም ወድቀው ተመልካችና ተንከባካቢ አጥተው እንዳይቀሩ እንዲሰበሰቡና ተምረው ራሳቸውን እንዲረዱ በማድረግ፣

- የችግረኞችና የአካል ጉዳተኞች መርጃ ተቋሞችን፣
- የሕፃናት ማሳደጊያና የዓይነ ስውራን አዳሪ ት/ቤቶችን፣
- የሕሙማን መርጃ ክሊኒኮችና ሆስፒታሎችን፣

በማደራጀት ዝክረ ስማቸውን በበጎ ሲያስታውሱ የሚኖሩ ተግባራትን ፈጽመዋል።

- በደብረ ሊባኖስ ገዳም ያቋቋሙት «ቤተሰሊሆም» የደካሞች መርጃ፣
- ቤተ ሳይዳ ሆስፒታል
- የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል እስከ ዛሬ ለብዙኃን ሰፊ አገልግሎት ሲያበረክቱ ኖረዋል።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ሰውን ሁሉ በሰውነቱ የማክበር፣ የማፍቀርና የተቻላቸውን ሁሉ የማድረግ በጎ ዝንባሌ ነበራቸው። ነዳያንን በዕለት ጉርስና ልብስ አዘውትረው ይጎበኙ ነበር።

ብሔራዊና ዓለም አቀፍ ችግሮችን በውይይት በመፍታትና በሰላማዊ የጉርብትና መንፈስ ለመኖር የሚያስችሉ መንገዶችን በመሻት በአፍሪካና በሌሎች አህጉር የተፈጠሩ የርስ በርስ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ በመፍታት ጦርነቶችን እያስወገዱ ለማኅበረሰብ ሰላምና ደኅንነት፣ ዕድገትና ብልጽግና ከፍተኛ እገዛ ያደረገ የማስታረቅ ተግባር አከናውነዋል።

እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር ፲፱፻፷፪ ዓ.ም አዲስ አበባ ተሰብስበው ለነበሩ የአፍሪካ አህጉር መሪዎች በሰላምና በቤተሰብ መንፈስ መኖር እንዳለባቸው ሲገልፁ:-

«ወንጀል ማብዛትና ቂምን ማስታወስ እንተው፣ ከንቱ በመሆኑ የመበቀል ስሜትን አጥፉ፤ እንደዚህ ያለው ስሜት መንፈሳችንን ከማድከምና ልባችንን ከመመረዝ የተለየ ጥቅም አይሰጥም» ብለዋል። (ዴል ፓፓሉ ኅዳር ፯ ቀን ፲፱፻፸ እኤአ (ጋዜጣ!)

በዚህ መስክ በፈጸሙት ታላቅ ተጋድሎ «የሰላም አባት የሕዝብ አስታራቂ» የሚል በጎ ስም አትርፈዋል።

«ሰውን ከሰው የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው» የሚለው ቃለ ወንጌል በግብር ተፈጽሞላቸዋል።

ግርማዊነታቸው በጎ ሰብእና ለሰው ስላላቸው ቅን አመለካከትና የተፈጥሮ ዝንባሌ ከሚገለጥባቸው ጠባያት ሌላው ገጽታ ለአረጋውያን፣ ለታናናሾች፣ ለደካሞችና ለሕፃናት ለእንስሳትም ጭምር ሳይቀር የነበራቸው ፍቅርና ርኅራኄ ነው።

በት/ቤቶች፣ በችግረኞች መርጃ ድርጅቶች፣ በሕፃናት ማሳደጊያ ተቋሞችና በሆስፒታሎች ጉብኝት



www.ethiopianorthodox.org

እያደረጉ ሁሉን እንደየባሕርዩ ማነጋገር፣ ማጽናናትና መርዳት የሁል ጊዜ ተግባራቸው ነበር። በቤተ መንግሥታቸው ተጠብቀው የሚኖሩ ልዩ ልዩ የቤት እንስሳትን፣ የዱር አራዊትንና አዕዋፍን ይመግቡ ነበር።

በረጅሙ የመሪነትና የአባትነት ዘመናቸው «አባባ ጃንሆይ» በሚል የአባትነት ደረጃ ይጠራቸው በነበረው ሕዝብ መካከል ያለውንም ፍርሀት፣ ጭንቀትና ሥጋት እየተመላለሱ ለሥራ በሚዘዋወሩባቸው ሥፍራዎች፣ ትምህርትና መመሪያ በሚሰጡባቸው አደባባዮችና ዙፋናዊ መድረኮች፣ በሚወጡባቸውና በሚገቡባቸው በሮችና መንገዶች ሁሉ መልካቸውን ለማየት፣ ድምፃቸውን ለመስማት ትንሹም ትልቁም ሲጋፋና ሲተናነቅባቸው ኖሯል። በጊዜው ከነበረው አዳጊ ትውልድ አመዛኙ ቁጥር

የቃል ኪደን ባለሟልነት የበቁት በዓለም ውስጥ ሳሉ የደረሱባቸውን ችግሮችና ፈተናዎች ሁሉ በትዕግሥትና በጽንዐት እየተቀበሉ እንደብርና ወርቅ በመከራ እሳት እየተፈተኑ በማለፋቸው ነው። ጻድቃን በዚህ ዓለም የሚቀበሉት ችግርና ፈተና ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ የማይጠፋውን ክብር ለማግኘት የሚጠቀሙበት የገድል መሣሪያቸው ነው።

ሰው በተሰጠው ዕድሜ ሕይወቱን በሥራ ካንቀሳቀሰ ባገኘው ዕውቀትና ሀብት በተመረጠበት ሥልጣንና ኃላፊነት አቅሙና ጊዜው የፈቀደለትን ያህል ከሠራ ከፍጡር በማይጠበቀው ፍጹምነት ምክንያት አይወቀስም። በመሆኑም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በዘመናቸው የፈጸሟቸው ታላላቅ ሥራዎች በታሪክ ሰፊ ምዕራፍ ያላቸው ስለሆኑ መታሰቢያቸው ለዘለዓለም



ግርማዊ ጃንሆይ ሥርዓተ ንግሥ የፈጸሙበት የገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን

የግል አባቱን ስም እየተወ «ኃይለ ሥላሴ ይሙት» በማለት በስማቸው ሲምልና ሲመካባቸው የልጅነት ፍቅሩን ሲገልፅላቸው ቆይቷል።

ግርማዊ ጃንሆይ በነበራቸው ብልህ አመራርና የማስተዋል ጸጋ በተመላበት የሕይወት ጉዟቸው ከሀገራቸውና ከዓለም ዙሪያ ብዙ ሽልማትና ምስጋና አግኝተዋል። ሰው እንደመሆናቸው ሐሜቶችና ነቀፋዎችም ደርሰውባቸዋል። የተለያዩ ችግሮችንና ፈታኝ ሁኔታዎችን ተጋፍጠዋል። ስደትን፣ ጦርነትን፣ በግል ቤተሰብና በዜጎች ኀዘን የደረሰውን ፈተና ሁሉ ተቋቁመው አልፈዋል። በመጨረሻም አሰቃቂ የሞትን ጽዋ ተቀብለዋል።

የደጋግ ሰው የሕይወት ጉዞ እንቅፋትና መሰናክል የመላበት በፈተና የታጠረ ነው። ቀደምት ቅዱሳን ነቢያት ጻድቃን ሰማዕታት ሁሉ ለዘለዓለም ሕይወትና ለማይለወጥ

አይጠፋም። ጠቢቡ «የጻድቃን ስም ከምስጋና ጋር ሲጠራ የኖራል» (ምሳ.10፥7) ሲል እንደተናገረ የግርማዊነታቸው ስምና ሥራ ከምስጋና ጋር ሲታሰብ የሚኖር ሕያው ነው። ቤተ ክርስቲያናችንም ታሪካቸውን በመጽሐፍ ስማቸውን በጸሎት ስታዘክር ትኖራለች።

ሰው ሁሉ በመሬታዊ ጠባዩ ሟች ተለዋጭ ነው። ስለሆነም በውሱን የቆይታ ዘመኑ፣ በሚሻር ሥልጣኑ በሚያልፍ ሀብትና ዕውቀቱ የሚቀር ክብሩና ሥጋዊ ሕይወቱ ስሙን በበጎ የሚያስጠራ ለትውልድ ትምህርትና ምሳሌ የሚሆን መልካም ሥራ ሠርቶ ማለፍ አለበት።

በዚህ ዓለም ሰውንና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ በጎ ሥራ የሠራ ሰው ዝክረ ስሙ አይረሳም፤ መታሰቢያውም ለዘለዓለም ሕያው ነው። ✣



www.ethiopianorthodox.org

# ልዩ ልዩ ቅኔያት

## ሀ. ፍልሰተ አፅማቸውንና ታላቅ መሪነታቸውን በተመለከተ በአሁኑ ጊዜ ካሉት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የተበረከቱ ቅኔያት

ከመልአከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁን

### ጉባኤ ቃና

አዕፅምቲሁ ለጌር ኃይለ ሥላሴ፣ አርእስቲክሙ አትኅቱ
እስመ በትሕትና ይትረከብ ልዕልና፣ በኀበ አጋዕዝት ሠለስቱ።

### ሥላሴ

ምድረ ርስት ከመይባኡ፣ ቤተ እስራኤል አዕፅምቲሁ፣ ለኃይለ ሥላሴ
ዘገብረ ፍኖቶ፣ ኃበ ምድረ ተስፋ ሐዳስ
ግርምተ ባሕረ ተዋርዶ ዐደው በየብስ
ወለምንት የሐውር በዐፅሙ፣ ኃይለ ሥላሴ ንጉሥ
ከመ ብእሲ ዘይጼነስ
እንዘ ምሉአ ክብር ውእቱ በሥጋ ወነፍስ
በኂሩቱ ለሕያው ክርስቶስ።

### ኵልክሙ

ተፈሥሒ ጽዮን ቤተ ክርስቲያን፣
በዘይሰመይ ወልድኪ ኃይለ ሥላሴ መፍቀሬ እሙ
ጽጌ ሃይማኖት ክብር ዕሴተ ብዙኅ ሕማሙ
ዮም እስመ አስተርአየ ሠሪጾ እምዐፅሙ
ወኢኮነ ዝክረ ስሙ፣
ታሕተ መቃብር ወሞት ለእመ ጸላኢ ይጸሙ።

### ለዓለም

ይምጽኡኬ ወይርአዩ ከመኢሞተ ቀዲሙ
ስሞ እለቀተሉ ወእለዘሞተ መሰሉሙ
ወእግዚአብሔር መሐለ ለአዕፅምቲሁ ኵሎሙ
ከመኢይደግም ለዓለም ጸላኢ አሕምሞቶሙ
እስመ ጥቡዓነ ኮኑ በውስተ ኵሉ ገድሎሙ
ከመኢይደግም ለዓለም ጸላኢ አሕምሞቶሙ።

❖❖❖

ከመጋቤ ምሥጢር ወልደ ሩፋኤል ፈታሒ

### መወድስ

እስከ ማዕዜኑ ዉእቱ ዘይትቤቀለነ
ኃይለ ሥላሴ ደምከ ዘተክዕዎ በአመፃ
እመ ለቃሕከነ ወርቀ እስመ ፈደይናከ ሆፃ
ወዕፃነ ኢያእመርነ፣ ለኢትዮጵያ እንዘ አንተ ዕፃ
ወክፍለ ዘመንከ አመ ሞፃ
እንዘ በበመትልው ይመልእ ለቤተ መቅደስ ሕፀፃ።

### ለዓለም

በምሴትሂ ለሕይወትከ ለእመተግሣጽ ሐወፃ
ወለሕዝበ ዚአከ አመፃሁ ለመንግሥተ ዚአከ አደንገፃ
በመንግሥተ ሰማይ ሐዳስ በይነ ዘሐነፀት ሕንፃ
ለመንግሥተ ዚአከ በሰማይ አልቦ ዘይጌሥጻ።

### መወድስ

መምለክያነ ዘርዕ ቅሩብ አአፅምተ ነጋሢ
ጊዜ ፍልሰቶሙ ቅድመ መጠነ ዓመታት ዐሥሩ
ለአፅመ ምኒልክ ምስሌሁ ድኅረ በዋሕድና ነበሩ
በታዕካ ነገሥት ማኅደሩ፣
ኆለቁ አእፅምተ ዘርዖሙ ወፍልጠተ ገብሩ
ከመአበዊነ ተናገሩ፣
እምነ ልጓም ዘርዕ እስመ ይስሕብ እምድሩ።

### ለዓለም

ለንጉሥሂ አእፅምቲሁ ምጽአተ ንጉሥ ያብሥሩ
መንገለ ቤቶሙ ለሥላሴ በትእዛዘ ጳውሎስ አመሐሩ
እንዘ ይብሉ ይባዕ ንጉሠ ስብሐት በክብሩ
አእፅምተ መነን መዘምራን ሰብሐ ወዘመሩ።



www.ethiopianorthodox.org

## መወድስ

አፅመ ነጋሢ ሕያው በትሩፋቲሁ፣ አመ ፈቀደ
ይኅድጋ ለታዕካ ነገሥት ዕቤርዩ
መጽሐፈ ኅዳጋት ጸሐፈ በዘኢኮነ ባሕርዩ
ይትፈለጥ እምኔሃ፣
ወዐዕይንቲሁ ካልእተ ይርአዩ
እስመ ለውእቱ ሰሐበቶ፣
በሐብለ ብዝኃ ብዕል ወፍቅር መንበረ ጸባዖት
ሐዳስዩ።

## ለዓለም

ሶበ መስየሂ ወተቈልቈለ ኃይለ ሥላሴ ፀሐዩ
መአልተ እለ ርኅቡ ሌሊተ ተሴሰዩ
ወይትፋትሆሙ አፅሙ ለኃይለ ሥላሴ አብድዩ
እለ ተለቅሑ ሠናያተ እመ እኩያተ
ይፈድዩ።

## መወድስ

ዘይቤ ዳዊት በቃለ መዝሙሩ
ኢያድኅን ምንተ እኁ እኅዋሁ
በላዕለ ዕፁብ ዕፁብ ሶበ ይመጽእ ላዕሌሁ
በኃይለ ሥላሴ ተፈጸመ ናሁ
ወተግህደ ትርጓሜሁ፣
እንዘ ባሕቲቶ ይነብር በቤተ መንግሥት ሥጋሁ።

## ለዓለም

አእፅምት አኃዊሁ፣ እስመ ቤተ መቅበርት አንጽሑ
በታኅተቤቶሙ ለሥላሴ ይንበሩ በኃቤሁ
ወምንት ዉእቱ ለተዘምዶ ሥጋ ረባሁ
ለነገረ ሥጋነ ዲበ ምድር እምዘ ከመዝሰ ፍጻሜሁ።

## መወድስ

ይቤሉ ንጉሥ ለመቃብሪሁ፣
እምስካበ ዚአከ ተንሥእ ወንቃሕ እምንዋም
እስመ እበውዕ ቤተከ ምስለ መባዕየ አፅም
እመኒ በአፍአ ሥጋየ ቅውም
እስከ ይትራከቡ በሰላም፣
ሥጋ ወአፅም በዐውደ ትንሣኤ ግሩም።

## ለዓለም

ዮምሰ ለእመርኅቡ ወለእመ ፀምዑ ዮም
አእፅምተ ንጉሥ ኃይለ ሥላሴ አልቦ ዘይዴመም
እስመ ትርጓሜሁ ወቃሉ በመጽሐፈ ዕዝራ ኅቱም
ዮም ከመአኮ ዘኃለፈ ትማልም።

## መወድስ

ምኒልክ ገብርኤል መልአከ አድኅኖ፣
ለታዕከ ነገሥት ድንግል ውስተ ቤተ መቅደስ አብሠራ
እንበለ ሩካቤ ወዘርዕ በድንግልናሃ ወክብራ
ከመትለድ አፅሞ ለሥጋከ በኵራ
ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ፣ ዘኵሉ ያውኢ ግርማ ገጽከ ገሞራ።

## ለዓለም

ግብተሂ አመ ወረደ ለኢትዮጵያ በምድራ
ለሕዝብከ አመፃሁ ማየ አይኅ ወመከራ
ጸሎትከ ኖኅ በሐመረ ድኂን ሰወራ
ለመነን አስፋው ታቦተ ሕግ እምኵሉ ዘታፈቅራ።

⁘⁘⁘

ከመጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

## መወድስ

ክብረ ወርቅ ወዕንቍ ለዘኢያእመረ
ጽሩይ ወርቅ ወክቡር ኢያስጺድ
ይመስልዎ አእባነ፤ ወአምሳለ ዉእቱ ዐብድ
ሀለዉ ዘበኢያእምሮ ተንሥኡ አይሁድ
ዘኃይለ ሥላሴ ጽሩየ ግብር
ወክቡረ ስም ክብረ እስመ ኢያእመሩ በልማድ

## ለዓለም

ትውልድሰ ድኅረ ኀለፈ እንተ ይመጽእ ትውልድ
ይንዕድ ምግባሪሁ ለኃይለ ሥላሴ ዘርዐ ናዖድ
ለብዙኅ ጥበብ አቡሁ እስመ ውእቱ ዋሕድ
ወውእቱ ተፍጻሜታ ለእሙ መንግሥተ ዘውድ።

## መወድስ

ኃይለ ሥላሴ ዐፅምከ መጽሐፈ ተግሣጽ
ኅቡአ ምሥጢር ኮነ ቅድመ ገጸ ሰብእ አእላፍ
ኢይትረአይሂ በዐይን ወኢይተነበብ በአፍ
ነበረ በተከብቶ፣
ዘይጌሥጽ ኵሎ ዐፅምከ መጽሐፍ
እስከ አመ ይትነበብ በውስቴቱ
ዘገብረ ሰብእ ላዕለ ሰብእ ዘየኀልፍ።

## ለዓለም

ደለዎሂ ለዳንኤል ጊዜ ተባርዮ ትሩፍ
ከመ ይፍታሕ ማኅተሚሁ
ለመጽሐፈ አፅምከ ዘዮሴፍ
በአጽባዕተ እድ ዘፋርስ እስመ ውእቱ ግሉፍ
መልአከ ሕዝባ ለባቢሎን ኢትዮጵያ ከመ ይዝልፍ።

⁘⁘⁘



www.ethiopianorthodox.org

ከሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታየ

## መወድስ

ለአፅመ ንጉሥ አብርሃም በከመ ይቤሉ፣
እግዚአብሔር ተፈለጥ እምነ
አዝማዲከ አእፅምት
እለ እምንግሥታት ኵሎን አስካለ ማርያም ቡርክት
ወእለ እምነገሥት ካልዐን፣
ምኒልክ ፀሐየ አፍሪካ ወፀሐይ ልዕልት
እምታዕካ ነገሥት ቤት አቡሁ፣
ወጽአ ይባዕ መንበረ ጽባዖት ምድረ ርስት።

## ለዓለም

ተካየደሂ ወመሐለ፣ እግዚአ ስብሐት
ዘምስለ አብርሃም ወይስሐቅ፣ ኃይለ ሥላሴ ወመሳፍንት
አምኃ ሥላሴ ያዕቆብ ወመስፍነ ሐረር ስፍሕት
የሀባ ለዘርዖሙ ለመንበረ ልዑል ጸባዖት።

## መወድስ

አመፃ ኅጉላን ፀሐይ እምከመ ሠረቀ
ወእምከመ ሀገር ውዕየ ውስተ ግበቢሆሙ
ይውዕሉ
አንበሳ ወነምር፣ አዕፅምተ ንጉሥ እሉ
አኮኑ ይውዕል ወይትቀነይ፣ እስከነ ይመሲ አብዮት ኵሉ
ወልደሰ ኃይለ ሥላሴ፣ ፀሮ መንግሥተ አግረረ በማስቀሉ።

## ለዓለም

ትውልድሂ አማፅያን፣ በንጉሦሙ መሐሉ
በአማን ኃይለ ሥላሴ፣ ይሙት እንዘ ይብሉ
ወመሐላ ደም አብዝኀ፣ ከመ ፃድቃነ ይምስሉ
እስመ ረስኡ ዘይብሉሙ ኢትምሐሉ በወንጌሉ።

✣✣✣

ከሊቀ ኅሩያን ጌታቸው ኀይሌ

## ጉባኤ ቃና

ማእምንት ይእቲ ታዕካ ነገሥት በአታ
እስመ ለሥላሴ ታገብእ ኃይለ ሥላሴ ማኅፀንታ።

## ኵልክሙ

መዋቲ ሥጋከ ለእመ ቀተሉ፣
ገበርተ ዓመፃ ወግፍዕ ወእመ ገደፉ አካለከ
በኅሱር መካን እንተ ኢይደሉ ለከ
ኢክህሉ ቀቲሎቶ፣
ለስምከ አምጣነ ረሰዮ ሕያወ ግብርከ
ወከመ ተብህለ በምሳሌ፣
መልዕልተ መቃብር ይውዕል ጽዉዐ ሥላሴ ስምከ።

## ለዓለም

በጽድቅሂ እመ ሐተትነ ግብረ መንግሥትከ
እምነገሥተ ዓባይ ኢትዮጵያ መኑ ይመስለከ
ወመኑ ስቡሕ በውስተ አፍሪካ ከማከ
ኃይለ ሥላሴ አበ ሰላም አፍሪካውያን ዘይቤሉከ
ለሕዝበ አፍሪካ ኵሎሙ እስመ ሰላመ አምጻእከ
ኃይለ ሥላሴ አበ ሰላም አፍሪካውያን ዘይቤሉከ።

✣✣✣

# ለ. ለቤተክርስቲያን ስለ አስገኙት መንፈሳዊ ነፃነት በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ከቀድሞ ሊቃውንት የተበረከቱ ቅኔያት

## መወድስ

እለ እስክንድሮስ ሊቅ ወቆስጠንጢኖስ
ሶበ ዲበ ምድር ዘርዑ ለተዋሕዶ ሥርናየ
ገራህተ ሥጋዌ ኤፌሶን ወገራህተ ትሥልስት ኒቅያ
እምክርዳድ እንዘ ይነጽሓ አዕላፈ ፈረያ
ወለፅምዕተ ቃል ቍስጥንጥንያ
ሃምሳ ወምዕተ ዕደ መንፈስ ቅዱስ አርወያ።

## ለዓለም

አዉአዩሂ ኃሠረ ሮሜ እንተ ሮማዊ ሐሰያ
በዓለ ማዕረር ኃይለ ሥላሴ ወባስልዮስ ሐዋርያ
እስመ አዋዲሆሙ ይብል ማዕከሌክሙ ነያ
ኦርቶዶክሳዉያን ዘትበዉኡ
መንግሥተ ሰማያት ኢትዮጵያ

አለቃ ነጋሽ ኃይሉ



www.ethiopianorthodox.org

## መወድስ

ዝናመ ጸጸሳት ሢመት ዘኢያስተርአየ፣ አስተርአየ ለነ በኢትዮጵያ ደመና
አምጣነ ኢትዮጲ ነበረት በዘፈጣሪ ሕሊና
እምቅድመ ሥርዋፁ ለአብርሃም
ዘኮነ አዕቃጹ ሢመቱ ለጴጥሮስ ሰኮና
ወእም ከርሠ እሙ እስክንድርያ፣
ኀሩየ ኀሩያን ባስልዮስ ለመንበረ ማርቆስ
ዕንቈ ብርሃና።

## ለዓለም

አንፈርዐጹሂ ወተፈሥሑ አድባረ ሊባኖስ ወሲና
አመ ቦአ ደብረ ዐስቦ ባስልዮስ ሆሣዕና
አኮኑ ይቤሉሙ አብ ኃይለ ሥላሴ ጸወና
እም ግብጽ ጸዋእክዎ ለወልድየ ጵጵስና።

ብላታ መኰሪያ ጎዳና

✣✣✣

## መወድስ

ምኵራበ ምኒልክ ዐነመት ጸምረ ተዋሕዶ
ወቤተ ክርስቲያን ተዐጽፈት በኃይለ ሥላሴ ዘመነ ሣህል
እስመ አናሚሁ ባስልዮስ ፀዋሬ መስቀል
ወውእቱ መስቴሁ ቴዎፍሎስ ቃል
ወእምአፍላጋት ፬ቱ፣ ኢትዮጵያ ትሰቀይ ፈለገ ትምህርቱ ለሚካኤል።

## ለዓለም

ጳውሎስሂ ኃይለ ሥላሴ እንተ አልቦቱ አምሳል
ተነግረ በመልእክቱ ወእስከ ጢሞቴዎስ ይትሌዐል
ያዕቆብሂ ዘሥሩግ በውስተ ድርሳኑ ዘይብል
ለዘጸጳሳት ፋሲካሆሙ ቀዳሚት ሕገ ወንጌል።

አለቃ ሥርግው ወልደ ጻድቅ

✣✣✣

## መወድስ

ባስልዮስ ጎህ ዐሠረ ብርሃን
ዕረፍት ይስሐቅ ትርጓሜ ስሙ ለኖኅ
ቴዎፍሎስ ቤዝ ኮከበ ጽባሕ
ሠረገላ ትዕግሥት ጢሞቴዎስ
ያዕቆብ ዘመነ ዕሪና ምልዓቱ ለወርኅ
በትረ ቀኖና ጎርጎርዮስ
ሐመረ ጸሎት ፊልጶስ ብሔረ ሕያዋን ዘታበጽሕ

## ለዓለም

ማርቆስ ምድረ ሲና፣ መሠረተ ሕጉ ለፍትሕ
መንበረ ገብርኤል ብሥራታዊ ገብርኤል ዐውደ ንጽሕ
ነቢየ ድንጋሌ ታዴዎስ ዘትንቢትከ ረባሕ
ሕጠተ ብዕልክሙ ጵጵስና በኃይለ ሥላሴ ለይትባዛኅ።

አለቃ ይትባረክ መርሻ

✣✣✣

## መወድስ

እፎ ታነክር ቤተ ክርስቲያን፣
ደመና ደብረ ታቦር ክብር ለባስልዮስ አመ ሰወሮ
እምሊቀ ምርፋቅ ዘዮም አምጣነ ነሥአት አንክሮ
እንዘ ኢየሐጽጽ አንክሮታ፣
ለኃይለ ሥላሴ መንግሥቶ ወክብሮ
በኩረ ትንሣኤስ ባስልዮስ፣ በብዝኀ ብርሃኑ ረቂቅ ለጽልመተ ሮሜ አዖሮ።

## ለዓለም

ይትነበብሂ በበዕለቱ ለእለ ቦሙ አእምሮ
መዝሙረ ዳዊት ኃይለ ሥላሴ ዘአፈ ባስልዮስ ይፌክሮ
ወእለ ሰምዑ ይቤሉ ነጐድጓደ ማርቆስ ሠምሮ
ወቦ እለ ይቤሉ መልአክ ተናገሮ።

አለቃ ገብረ ዮሐንስ የቦሩ ሜዳ ሥላሴ አስተዳዳሪ የነበሩ

✣✣✣

## መወድስ

ሐመረ መድኃኒት ባስልዮስ ማዕዶተ ግብጽ፣
አድያመ ዮርዳኖስ ያደ ከመ ይዜኑ ትዕግሥቶ
ለኃይለ ሥላሴ ንጉሥ ወእምዘርአ ዳዊት ምጽአቶ
እስመ ሀለወነ ፍቁራን፣
ከመ ንርአይ በዓይነ ሥጋዌ ዳግመ ልደቶ
ባሁቱ ሕዝበ ሮምያ፣ ሙሴ ዘርዕደ ስእነ ጠይቆቶ።

## ለዓለም

ባሕርሂ ግርምተ ሙሴ ለእመ ርእየቶ
ሰገደት በብረኪሃ ወበቃለ ሰላም አእኮተቶ
ከመ ተወፈየት እም ኢትዮጵያ መንግሥቶ
እሞ እስመ ረሰያ ወኮነት ወላዲቶ።

ቀኝ ጌታ ገብረ ሥላሴ ፀሐዩ ዘብሔረ የጁ

(ከመጽሐፈ ዜና ባስልዮስ የተወሰደ)



www.ethiopianorthodox.org

# የመጽሔቱ ዝግጅት ኮሚቴ አባላትና
# ጽሑፍ አቅራቢዎች

ብፁዕ አቡነ ገሪማ የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት፣ የውጭ ግንኙነት የበላይ ኃላፊና የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ሊቀ ጳጳስ የሥነ ጽሑፍ ዝግጅት ኮሚቴ ሰብሳቢ።

«እግዚአብሔር የዐቅብ ኵሎ አዕፅምቲሆሙ» ፡ በመልአከታቦር ተሾመ ዘሪሁን

የጠቅላይ ቤተ ክህነት ም/ሥራ አስኪያጅ

«ዝክረ ጻድቅ ለዓለም ይሄሉ» ፡ በመልአከ ሰላም ዳኛቸው ካሣሁን፣ የስብከተ ወንጌል መምሪያ ኃላፊ

«እስመ በጸሕኮ በበረከት ሠናይ» ፡ በሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታየ፣ የሊቃውንት ጉባኤ አባል

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ መብት ፡ በሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ ዓለማየሁ

የሰንበት ት/ቤቶች ማስተባበሪያ መምሪያ ኃላፊ

የግርማዊነታቸው መንፈሳዊ ሕይወት ፡ በመጋቤ ምሥጢር ወልደሩፋኤል ፈታሒ

የዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ

«ስምከ ሕያው ዘኢይመውት»ና የውጭ ግንኙነት ፡ በመጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

የሊቃውንት ጉባኤ አባል

የቅዱሳት መጻሕፍት ኅትመት ፡ በሊቀ ሥዩማን ራደ አስረስ፣ የሊቃውንት ጉባኤ አባል

ሕንፀተ ቤተ ክርስቲያን፣ መንፈሳዊ ት/ቤትና ስብከተ ወንጌል ፡ በሊቀ ኅሩያን ጌታቸው ጓዴ

የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ሊቀ ጳጳስ ልዩ ጸሐፊ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘመናዊ አስተዳደር ፡ በአቶ እሱባለው ወ/ሥላሴ


በልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን የዶክሜንቴሽንና የኢንፎርሜሽን አገልግሎት ኃላፊ

## አዘጋጆች

መጋቤ ምሥጢር ወልደሩፋኤል ፈታሒ

ሊቀ ኅሩያን ጌታቸው ጓዴ ተገኘ

www.ethiopianorthodox.org



www.ethiopianorthodox.org